
# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

5ኛ ዓመት ቁጥር 4 ሐምሌ/ነሐሴ 1989 ዓ.ም



©

www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን 

# ሐመር

5ኛ ዓመት ቁጥር 4
ሐምሌ/ነሐሴ 1989 ዓ.ም


## ይዘት


የማኅበሩ መልእክት
- «ታሪክ ዘዳግም»..............................2

ደብዳቤዎች..............................4

- ከሰሞኑ በረከት
- ወርኃ ክረምት በቤተክርስቲያን ትምህርት.......5

ትምህርተ ሃይማኖት
- ብሉይ ኪዳን በሐዲስ ኪዳን..............8
- የእግዚአብሔር ሕግ........................10

የጥያቄዎቻችሁ መልስ..............................12

ኪነ ጥበብ
- ኦርቶዶክሳዊ ሥነጽሑፍ.....................14
- ከሞት ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ........16

እናስተዋውቃችሁ
- ጉንዳጉንዲ..............................19
- እምነ ወለተ ጴጥሮስ......................20

ዓምደ ወራዙት
- ለመወሰን እንድንችል ምን እናድርግ?...........22
- «ትንሽ» የሚባለውን ሥራ ያላከበረ «ለትልቁ» አይበቃም....................24

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
- መፍትሔ «ለመፍትሔ አልባው»...................26
- ምንተ ንግበር..............................29

ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ
- የቤተክርስቲያን ታሪክ ....................30
- ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ....................32



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።


# ከአዘጋጁ

የሁላችን ውጤት የሆነችው ሐመር የዚህ ዓለም የፈተና ማዕበል ሳይበግራት ባሕረ ዓለምን እየቀዘፈች ለምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት መጎልበት የሚያስፈልገውን ምግበ ነፍስ ለማዳረስ ጥረቷን ቀጥላለች። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድም ይህን አገልግሎቷን ትገፋበታለች።

በዚህ እትምዋ ከባሕር ማዶና ከሀገር ውስጥ የተላኩትን የደብዳቤዎች መልእክት መሠረት አድርጋ የሚሻሻለውን አሻሽላ፣ የሚታከለውን አክላ፣ የጎደለውን ሞልታ፣መጠነ ሰፊ የሆነውን ድግስዋን ይዛ ብቅ ብላለች።

«የእግዚአብሔር ሕግ» በሚለው ዐብይ ርዕስ ሥር «የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ» የሚለውን ሕግ ተንትና አቅርባለች።

በእናስተዋውቃችሁ ዓምድዋ ደግሞ ከቅዱሳት መካናት ጉንዳጉንዲ ማርያምን፣ከቅዱሳት አንስት እምነ ወለተ ጴጥሮስን ታስተዋውቀናለች። በክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምዷ ጥያቄዎቻችሁን መልሳለች፤ መፍትሔ የለውም ለሚባለው ኤድስም መፍትሔዋን ይዛ ቀርባለች። እጅና እግሩን አጣምሮ መና ከሰማይ እንዲወርድለት የሚሻ ካለ ከክርስቲያንነት የወጣ ነው። እግዚአብሔር የሰነፎች አምላክ አይደለምና፤ በማለት ሰዎች የሚንቁትን ሥራ አክብረው የተሰማሩትን ሁሉት ወጣቶች በዓምደ ወራዙት ዓምድዋ አስተናግዳለች። ባለፈው በይቀጥላል የተላለፉ ጽሑፎች እና ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጠቃሚ የሆኑ ዝግጅቶችን የያዘች በመሆንዋ ከግብዣዋ ትቋደሱ ዘንድ እነሆ።


ዋና አዘጋጅ - ብርሃኑ ጎበና ካሣ
ም/ዋና አዘጋጅ-ዲ.ደጀኔ ሺፈራው

ስልክ 550099 Ext 46
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

## ታሪክ ዘዳግም

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ርትዕት ሃይማኖት ከቀና ምግባር ጋር ከማስተማር አልፋ የሰው ልጆች ኑሮ የተስተካከለ ይሆን ዘንድ በትምህርት፣ በቋንቋ፣ በሥነ ሥዕል፣ በሥነ ሕንፃ፣ በታሪክ፣ በፍልስፍና፣ በጤና ጥበቃ፣በማኅበራዊ ኑሮ ግንባታ፣ ወዘተ ያበረከተችው አስተዋጽዖ ብዙ ብቻ ሳይሆን የትየለሌም ነው።

ልጆቿ በሁሉም ወገን ምሉዕ ይሆኑ ዘንድ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ታዘጋጅላቸዋለች፤የሚያዘጋጁበትን መንገድም ትመራቸዋለች። በዚህም የተነሣ የሰውን ልጅ ደካማ ጐን ለጥፋት ተልዕኰው የሚጠቀምበት ጠላት ዲያብሎስ የቤተክርስቲያንን ልጆች ሁሉ ከእናታቸው ጉያ ነጥሎ ለመስረቅ ያደረገው ጥረት  ሳይሳካለት ቀርቷል።

አንድን ትውልድ በሚገባ ቀርጾ ለማውጣት፣ የነገዋን ሀገርና ቤተክርስቲያንን የሚረከብ ብቁ ዜጋ ለማፍራት፣ በሃይማኖቱ ነቅዕ የሌለበት፣ በምግባሩ የተመሰከረለት ሰው ለማግኘት ከሁሉም ነገር በላይ ትምህርት ጉልህ ድርሻ አለው። ቤተክርስቲያን ይህን ታላቅ ተግባር ለመሥራት አዲስ አይደለችም። ዙሪው ካስተማሩላት፣ ካፀደትና ደማቸውን ካፈሰሱላት ከሐዋርያት ጀምሮ በየዘመናቱ የተነሡ አበው በየአህጉረ ስብከታቸው መንፈሳዊ ጥበብ ከኑሮ ጥበብ ጋር የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች መሥርተው እንደነበር ታሪካቸው ያስረዳናል።

በሕንድ ቅዱስ ቶማስ፣ በአርመን ቅዱስ እንድርያስ፣በሶርያ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ በግብጽ ቅዱስ ማርቆስ፣ በአክሱም ከሳቴ ብርሃን ሰላማ፣በሐይቅ እስጢፋኖስ አባ ኢየሱስ ሞዓ፣ በደብረ ታቦር ኢየሱስ አለቃ ተክሌ... የመሠረቷቸው ታላላቅ ትምህርት ቤቶች ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው።

በተለይም በ3ኛው መ/ክ/ዘ በግብጽና ሶርያ ገዳማት እየተስፋፉ ሲመጡ የትምህርት ቤቶች በገዳማት መቋቋም ጀመሩ። ይህም በየዘመኑ የተነሡ መናፍቃንና አላውያን ነገሥታት ቤተክርስቲያንን ሊያጠፉ ሲዘምቱ የቤተክርስቲያንን መጻሕፍትና ሊቃውንት በቀላሉ እንዳያገኙዋቸው አድርጓል። ገዳማቱ የሚገኙት በበረሃ ነበርና።

በሀገራችንም ቅዱስ ላሊበላ፣ ደብረዳሞ፣ ዋሸራ ቅኔ ቤት፣ደብረ ሊባኖስ፣ የጣና ገዳማት ዘርአ ምባ አረጋዊ፣ ደብረ ዓባይ የቅዳሴ ት/ቤት፣ ቤተልሔም ድጓ ት/ቤት ወዘተ... የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን ጥንታዊና ትውፊታዊ ትምህርቶች ጠብቀው ለትውልድ ያቆዩ ገዳማትና አድባራት ናቸው።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የኑሮ ለውጥ ሲመጣ የሕዝቡ ኑሮ ከገጠር ወደ ከተማ፣የአኗኗር ዘይቤውም የምዕራባውያንን  ተከተለ። ወጣቱ ትውልድም እንደቀድሞው ሙሉ በሙሉ ወደ አድባራቱና ገዳማቱ ወርዶ፣ ጥሬ ቆርጥሞ፣ ኰቸሮ በልቶ ለመማር የዘመናዊ ኑሮ ሥርዓቱ አልፈቀደለትም።

ከዚህ አንጻር መወሰድ የነበረበት አንድ ዐቢይ ቁም ነገር በወቅቱ ተዘንግቶ ወይም አላስፈላጊ ነው ተብሎ የቀረ ይመስላል፤ የቤተክርስቲያን በዘመናዊው የትምህርት መስክ የጐላ ተሳትፎ ማድረግ። በርግጥ በአንዳንድ ቦታዎች ለቅምሻ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ተከፍተው ነበር።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የትምህርት እመቤትነት ለአብነት ቀርቶ ለቁጥር ሊገቡ አይችሉም።

ይህ ደካማ ጐን አያሌ የቤተክርስቲያን ልጆችን በአላስፈላጊ ፍልስፍናና በመናፍቃን ጥቁር ወተት እንዲያድጉ አድርጓቸዋል። የቤተክርስቲያን ውለታዋ ተዘንግቶ «የኋላ ቀርነት መንሥኤ» እየተደረገች መታየትም ጀምራ ነበር።

እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት የራሱ ጊዜ አለው። በአሁኑ ጊዜ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያኖቻችን ትውልዱን ኰትኩተው የሚያሳድጉ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ታጥቀው ተነሥተዋል። ሙሴ የእሥራኤልን ታሪክ እንደገና በኦሪት ዘዳግም እንዳስፈረው ሁሉ። ይህ ለቤተክርስቲያናችን «ታሪክ ዘዳግም» ሊባል የሚገባው ተግባር ነው። ፍጻሜውን ያሳምርልን እንጂ።

የትምህርት ቤቶቹ ግንባታ ለቤተክርስቲያን የሚሰጡት ጥቅም ባለብዙ ፈርጅ ነው። የመጀመርያው፣ልጆቿ በእናታቸው ቤት በሁለት ወገን የተሳሉ ሰይፎች ሆነው እንዲወጡ ያስችላቸዋል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ንጹሐን አእምሮ የሆኑ ሕጻናትን ከመናፍቃንና ከከሐድያን ብሎም ከምግባረቢሶች በሽታ ይጠብቃቸዋል። ከነዚህ በተጨማሪ ደግሞ ቤተክርስቲያን ጥላ ዘቅዝቃ ከመለመን በልማቱ ዘርፍ ተሠማርታ የራስዋን ገቢ እንድታዳብር ያግዛታል። ለልጆቿ የሥራ ዕድል መፍጠሩም ቀላል አይደለም።

አለፍ ብለን ለማየት ከሞከርን ደግሞ ቀን ሕጻናትና ወጣቶችን ሲያስተምር የሚውለው ት/ቤት በማታ ምእመናን ስለ ሃይማኖታቸው የሚማሩበት፣የአብነት ትምህርቶች /ዕድሉን አጥቶ ወይም አላመች ብሎት ላልተማረው ትውልድ/ የሚሰጡበት ባለ መንታ ጥቅም ተቋም ለመሆንም ይችላል።

በመሆኑም ምእመናን በዚህ የቤተክርስቲያናችን ታላቅ ተግባር ታሪክ የማይረሳውና ለክብር የሚያበቃ ድርሻችንን ልንወጣ ያስፈልገናል። እናቱ እንጀራ ስትጋግር አጠገብዋ የሚያንቀላፋ ልጅ አንድም እሳት ይባላዋል፣ያለበለዚያም እንጐቻዋ ያልፈዋል።

ይህን ታላቅ ሥራ ያልጀመርነው ወይም አስበንበት የማናውቅ ሰበካ ጉባኤያት የመንቂያችን ጊዜ አሁን ነው። ቀን ሳለ በብርሃን ተመላለሱ እንዲል። በበዓላት ቀን ከብት ለማረድ ከመጣደፍ፣የተንዛዛ ድግስ ከመደገስ፣በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ ለአጥር ማሠርያ ከመለመን፣የቤተክርስቲያኑን አጥር በር ለማሣመር ብቻ ዘወትር ከመጣር ይልቅ ለቤተክርስቲያን ቋሚ የሆነ ቅርስ ለሚጥሉ፣ራሷን እንዲትችል ለሚያበቁ፣ ትውልድን ዘላለም ለሚጠቅሙ ተግባራት መሰለፉ ይበጃል። ጢስ ፈርቶ ሽሮ እየበጠበጡ ከመብላት እሳት ደፍሮ ወጥ መሥራት ለጣዕምም ለጤናም ይበጃል።

ከዚህ ጋር ሊስተዋሉ የሚገባቸው ነገሮች አሉ። ትምህርት ቤቶቹ በራሳቸው የተፈለገውን ውጤት አያመጡም፣ ክፍሎቹ ቢበዙ፣ ሕንፃው ቢያምር፣ ገቢው ጠቀም ያለም ቢሆን ብቻቸውን የሚሰጡት ፋይዳ ግን የለም። አሠራራቸው፣ አመራራቸው፣የሰው ኃይል አመዳደባቸው ለተቋቋሙበት ዓላማ ግብ መምታት የሚያመች ሆኖ ካልተዘጋጀ በቀር።

ለቦታው የሚያስፈልገው ባለሞያ ካልተቀጠረ፣ ዕውቀቱ፣ ምግባሩና ሃይማኖቱ የተመሠከረለት ሰው ካልተመደበ፣ አሠራራችን ረዥምና አስልቺ ቢሮክራሲን ካላስወገደ፣ ከምናገኘው ገቢ በላይ በምግባር በሃይማኖት ትውልዱን መኰትኰታችንን ቅድሚያ ካልሰጠነው በዘመድ፣ በትውውቅና በይሉኝታ የሚሠሩ እኩይ ተግባራትን ካላስወገድን፣የሚፈለገው የሥነ ምግባርና የሃይማኖት ትምህርት ተገቢውን ቦታ ይዞ ካልተሰጠ፣ የምናፈራው ፍሬ የተገላቢጦሽ መሆኑ አያጠራጥርም።

በመሆኑም የቤተክርስቲያን አበው፣ የአጥቢያ ሰበካ ጉባኤያትና ምእመናን በነዚህ ነጥቦች ላይ ቀድመው መዘጋጀት፣ ተገቢና ግልጽ የሆነ መመርያ ማውጣት፣ ብሎም አፈጻጸሙን በቅርብ መከታተል ይገባቸዋል። አስቀድሞ ዘርቶ ዘሩን አፈር ያላለበሰ እና ሥር ያላስያዘ ገበሬ እየዘነበ ቢዘራው ጐርፍ ይወስደዋል እንጂ ፍሬ አያፈራለትም።

የቤተክርስቲያን አምላክ ሥራችንን ይባርክልን። አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## እናንተም እንዳይገጥማችሁ ጥንቃቄ አድርጉ

በቤተክርስቲያናችን አካባቢ እየታተሙ በሚወጡ አንዳንድ መጻሕፍት፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች እንዲሁም የመዝሙር ካሴቶች ላይ አልፎ አልፎ የሌሉ ወይም የተሳሳቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ያጋጥሙናል:: የታይፕ /የኅትመት/ችግር ሊሆን ይችላል፤ ቢሆንም በሌሎች ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሌለ የውሸት ትምህርት የምናስተምር ያስመስልብናልና እናንተ በመጽሔቷ ወይም በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ እንደዚህ ዓይነቱ ስህተት እንዳይገጥማችሁ ጥንቃቄ ብታደርጉ መልካም ነው:: እንዲሁም የመጽሔቷን የኅትመት ቁጥር ጨምራችሁ በበቂ ሁኔታ እንዲደርሰንና መኖሯን በዝና ብቻ የምንሰማትንና አልፎ አልፎ በበራሪ የምናገኛትንም ጋዜጣችሁን ወደ እኛ አካባቢ እድትደርስ ለማድረግ ሞክሩ::

*ሀብታሙ /ሆሳዕና/*

## የቅዳሴአችንን ትርጉም በአማርኛ አስተምሩን

ሐመር በጣም ብዙ ቁምነገሮችን እያስገበየችን፣ቤተክርስቲያናችንንም በሚገባ እንድናውቅ እያደረገችን ነውና በርቱልን:: በተረፈ የቅዳሴ ተሰጥኦን ብዙ ሰው ሲቀበል እንሰማለን:: ነገር ግን ትርጉሙን ዐውቆት የሚቀበለው ምን ያህል ነው? ቢባል እጅግ በጣም ጥቂት ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን:: ስለዚህ እንደጀመራችሁት የግ ዕዝ ትምህርት ዓይነት የቅዳሴአችንንም ትርጉም በአማርኛ በተከታታይ ብታስተምሩን ጥሩ ይመስለኛልና አስቡበት::

*ወለተ ኢየሱስ*
*/ጉፋ ገብርኤል ሰንበት ት/ቤት/*

## በተልእኮም አስተምሩ

በቅድሚያ ካለሁበት ቦታ መንፈሳዊ ሰላም ታዬ ይድረሳችሁ:: በመቀጠልም የተሰሙኝን አስተያየቶቼን እሰነዝራለሁ:: በ4ኛ ዓመት ቁጥር 2 /ልዩ ዕትም/ መጽሔታችሁ ገጽ 29 ላይ የቤተክርስቲያን የወንጌል አገልጋዮች ብዛት ካለው ሕዝበ ክርስቲያን አንፃር እጅግ በጣም አነስተኛ እንደሆነ ተገልጿል:: መፍትሔውን በተመለከተ እናንተና የመለከት መጽሔት ዝግጅት ክፍል በጋራ ሆናችሁ የተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል በተልዕኮ ትምህርተ ሃይማኖትን፣የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትንና አጠቃላይ የሆኑ የቤተክርስቲያን ትምህርቶችን ለማስተማር ብትሞክሩ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ችግሩን የሚቀርፍ ይመስለኛል:: እንዲሁም አዲስ አበባ አካባቢ እንደምታደርጉት በሌሎች አካባቢዎችም ትልልቅ መንፈሳዊ ጉባኤያትን እያዘጋጀችሁ ብታስተምሩና ሕዝቡ በሃይማኖቱ ጸንቶ እንዲኖር ብታደርጉ ትልቅ ለውጥ ያመጣልና አስቡበት::

*ኤርምያስ ማሞ /ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ/*
*በለጠች ቢማ /አምቦ/*

## የትውውቅ መድረክ ክፈቱልን

ውድ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች፤ እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛላችሁ:: ከውዳሴ ከንቱም ይጠብቃችሁ:: በመጽሔቷ የተለያዩ ዓምዶች እየሰጣችሁት ያለው ታላቅ ትምህርት ለቤተክርስቲያናችን ትምህርት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያደረገ ነው ብል ማጋነን አይሆንብንም:: በተጨማሪም በተለያዩ ቦታ ያሉ መንፈሳውያን ማኅበራት፣ እንዲሁም እኅቶችና ወንድሞች የምንተዋወቅበትን «የትውውቅ መድረክ» ብትከፍቱልን እርስ በርስ እንድንማማርና እንድንመካከር የሚያደርገን ይመስለኛልና ትኩረት ስጡበት ::

*/ወልቂጤ ደ/ጽ/ቅ/ማርያም ሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች*

### ከአዘጋጁ

አስተያየታችሁ ተገቢ ነው:: ነገር ግን የትውውቅ ዓምዱን በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣችን እያስተናገድን ስለሆነ ተከታተሉ::

## ከእናንት እንጂ ከሐመር አልተጣላሁም

የሐመር አዘጋጆች እንደምን አላችሁ? እኔ የአርያም ንጉሥ ክብር ምሥጋና ይግባውና ደህና ነኝ:: በእናንተ ላይ ትልቅ ቅሬታ አለኝ:: ይኸውም ይህች ማሳረጊያ ደብዳቤዬ አራተኛዬ ስትሆን ቅርጫታችሁ ቤርሙዳ ናት መሰለኝ እስከአሁን አንድ እንደደረሳችሁ እንኳን አልተገለጸልኝም:: ምንም ብታደርጉኝ ማንበቤን ግን አልተውም:: ከእናንተ እንጂ ከሐመር ጋር አልተጣላሁምና!

*ዲ.ዳንኤል አሥራት*
*/ሾኔ ቅ/ጊ/ቤ/ክ/*

## የማይወጣ ከሆነ ለራሴ መልሱት

ውድ አዘጋጆች የላክሁላችሁ አምስት ገጽ ግጥም እየተስፋፉ የመጣውን የእምነት ወረርሽኝ ሊዋጋ ይችላልና ያለመቀነስና ያለ መጨመር እንድታወጡት አሳስባለሁ:: በቦታ ጥበት ተቀንሶ ከሚታወክ ይልቅ ለራሴ ብትመልሱት ይሻላል:: እናንተም በጉባኤ ስለማውቃችሁ በመተማመን ልኬላችኋለሁ:: ሙሉ ገጽ እንድትሰጡትም የውግዘት ያህል አሳስባችኋለሁ:: ሌሎች ተከታታይ ትምህርቶችንም እንደምልክላችሁ ቃል እገባለሁ::

*ከበአታ ድንግል ጽጌ ማርያም*
*/አ.አ/*

## መድረሱን ብቻ አሳውቁ

ሐመሮች በእግዚአብሔር ስም ሰላምታዬን አቀርባለሁ:: የምንልካቸው ጽሑፎች ለምን አልወጡም፣ ለምንስ ጽሑፋችን ይታረማል፣ በጽሑፋችን ላይ አትጨምሩ አትቀንሱ ወዘተ... እያሉ የሚያስቸግሯችሁን ተሳታፊዎች በደብዳቤዎች ዓምድ ባታወጧቸው ጥሩ ነው:: ቦታ ስለሚሻማ መድረሱን ብቻ ብታሳውቁ ይበቃል:: ከዚህም ሌላ በ5ኛ ዓመት ቁ 1 እትማችሁ በክርስትና በማኅበራዊ ዓምድ የጥያቄዎች መልስ ጥያቄ ሐ. እልተመለሰምና መልሱልን::

*ኤልያስ ደስታ*
*/አ.አ/*

## ለማቆም ዳርዳር እያላችሁ ይሆን?

ሐዋርያትን መርጦ ለወንጌል እንዳሠማራ በዘመናችንም እግዚአብሔር መርጧችሁ አገልግሎታችሁን እየፈጸማችሁ መሆኑ በጣም ያስደስታል:: ይሁን እንጂ አንድ ነገር ያስፈራኛል:: ብዙ ወጣቶች መጀመሩ ላይ እንጂ እንዴትና የት መፈጸም እንዳ ለባቸው አይጨነቁም:: በዚህም የተነሣ አጀ ማመራቸውና ፍጻሜያቸው የተለያየ ሆኖ ማየት የተለመደ ሆኗል:: እናንተም ጉዞአችሁ እንደ አጀማመራችሁ አይደለም:: ለማቆም ዳር ዳር እያላችሁ ይሆን አይታወቅም:: የመጽሔቷ የመውጫ ጊዜ ዘወትር እየዘገየብን እያሳሰባችሁን ነው::ሥራ እንደሚበዛባችሁና ብዙ ችግሮች እንደሚኖሩባችሁ ይገባኛል:: ቢሆንም የጀመራችሁትን ከግብ ለማድረስ ያበለጠ ልትተጉ ያስፈልጋል:: ይህች እየዘገዩ ብቅ ማለታችሁ እስከነ አካቴው ለመጥፋት እንዳይሆን::

*ዲ. ኃይለ መለኮት ተፈራ*
*/ጨንቻ/*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ስለሌሉ ነው ወይስ ስንፍና?

ሐመሮች መጽሔቷን ማንበብ ከጀመርኩበት ጊዜ አንሥቶ በሚገባኝ ቋንቋ የሚያስፈልገኝን ቃለ እግዚአብሔር እየመገባችሁኝ ስለሆነ እግዚአብሔር ኃይሉንና ጽናቱን ይስጣችሁ:: በዚህ አጋጣሚ ልጠቁማችሁ የምፈልገው ነገር እስከዛሬ በእናስተዋውቃችሁ ዓምድ የምታስተዋቁን ቅዱሳት መካናት ብዙ ቢሆንም ትኩረት የሰጣችሁት በሰሜን ለሚገኙት ብቻ ይመስለኛል:: በሌሎች አካባቢዎች ስለሌለ ነው ወይስ ስንፍና? ለምሳሌ እኔ ብጠቁማችሁ «ምዕራባዊት አክሱም» የምትባለውንና የረጅም ዕድሜ ባለቤት የሆነችውን የጎሬ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያንን ታሪክ ለሌሎች ብታስተዋውቁ ጥሩ ይመስለኛል:: እንደዚሁ ለሌሎች አካባቢዎችም ትኩረት ስጡና አስተዋውቁን:: እግዚአብሐር አገልግሎታችሁን ይባርክ::

*ሥዩም አበራ /ጎሬ/*

## ባታስቀሩት መልካም ነው

ሐመሮች ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ ዓምድ ሥር ማስተማር የጀመራችሁት የግዕዝ ቋንቋ ትምህርት በጣም አስደስቶኛል:: የማናውቀውንም እንድናውቅ እያደረጋችሁ ነው:: የእግዚአብሔርን አጋዥነት የቅዱሳንን አማላጅነት አይለየን እያላችሁ ጽሑፎቻችሁን ትዘጉ ነበር አሁንአሁን ግን እየተዋችሁት ነውና መዝጊያውን ባታስቀሩት መልካም ነው::

*ተስፋዬ ረጋሳ /አዲግራት/*

## የነገውን ተረካቢዎች አትርሱ

የሐመር አዘጋጆች የመጽሔቷ አንባቢዎች አዛውንት፣ ወጣቶች፣ ሕጻናት በአጠቃላይ የዕድሜ ገደብ ሳይኖር ሁሉን ምእመን የምታስተናግዱ ይመስለኛል:: በመሆኑም ለሕጻናት አንድ ዓምድ ብትጨምሩና ለእነርሱም የሚመጥናቸውን መልእክት ብታስተላልፉልኝ መልካም ነው:: እንዲሁም ለመጽሔታችሁ የሚስማማ የካርቶን ሥዕል ብትጨምሩ በቀላሉ ትምህርት ይሰጣልና አስቡበት::

*መ/ር ዘነበ ተሜነ /ይርጋ ጨፌ/*

## በየወሩ አድርጓት

ሐመሮች በየሁለት ወሩ የምትወጣው መጽሔታችሁ እጅግ አስተማሪ በመሆኗ እየተከታተልኩ አነባታለሁ:: በተለይም ለወጣቶች በጣም ጠቃሚ ትምህርቶችን እያስተላለፈች በመሆኗ በየወሩ ብታደርጓት የተሻለ ይመስለኛልና:: የሚቻላችሁ ከሆነ አስቡበት::

*ዲ.አማረ ወ/ሥላሴ*
*/አ.አደ/አ/ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን*

## ሳትጨርሱ ለምን ትጀምራላችሁ?

ሐመሮች እንደምን ከርማችኋል? ቀድሞ የመጽሔቷን የተወሰኑ ዓምዶች ብቻ ነበር የማነበው:: አሁን ግን በሽፋኖች ላይ ያለው እንኳ ሳይቀረኝ ማንበብ ጀምሬ አለሁ:: አልፎ አልፎ አንዳንድ ጽሑፎችን ትጀምሩና በይቀጥላል አቁማችሁ በሚቀጥለው ይቀጥላል የተባለው ይረሳና ሌሎች አዳዲስ ጽሑፎችን እንመለከታለን:: ይህ ለምን ይሆናል? ሳትጨርሱ ለምን ትጀምራላችሁ? ከጀመራችሁ ደግሞ መጨረስ ይልመድባችሁ::

*ጽጌ ማርያም ታደሰ /አ.አ/*

## እግዚአብሔር ይስጥልን

በጅምር ላይ ስለሚገኘው የጽርሐ ጽዮን አብማ ማርያም ካቴድራል ሥራን በተመለከተ መንፈሳዊ የሆኑ ክርስቲያን ወገኖች ሁሉ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲለግሱ..ቢጋዜጣችሁ እና በሐመር 5ኛ ቁ 3 ሚያዚያ /ግንቦት 1989 ዓ.ም ከቤተክርስቲያኑ መመሥረት ጀምሮ እስካሁን ያለበትን ሁኔታ የሚገልጽ መልእክት በማስተላለፋችሁ በርካታ መንፈሳዊ ወገኖች የዐቅማቸውን ርዳታ እየለገሱን ነውና ላደረጋችሁልን ሁሉ እግዚአብሔር ይስጥልን::

*አለቃ ጌታሁን ተግባሩ*
*የአብማ ማርያም ደብር አስተዳዳሪ*

## ስሜ ለምን ሳይጠቀስ ቀረ?

ሐመሮች፡ በመጽሔታችሁ በ5ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትማችሁ «ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ» በሚል ርዕስ ለወጣቱ ክፍል የጻፍኩት ጽሑፍ በመውጣቱ ደስ ብሎኛል:: ነገር ግን ስሜ ባለመጠቀሱ ቅር ተሰኝቻለሁና ለምን እንዳልገለጻችሁት በመጽሔትችሁ አስታውቁኝ::

*ዲ.ሳሙኤል ኃ/ማርያም /ሊሙ.ሰቃ/*

__ከአዘጋጁ፡-__ ስምዎ ያልተጠቀሰው በስህተት በመሆኑ ይቅርታ እንጠይቃለን::

## ማንነታቸውን ግልጥ አድርጋችሁ አሳውቁን

ዘመናችን መናፍቃን እንደአሸን የፈሉበትና ብዙዎች የዋሐን ወገኖቻችንን የበግ ለምድ ለብሰው የሚናጠቁበት ወቅት እንደሆነ ይታወቃል:: እናንተ የሌሎችን ማንነትና ከእውነተኛይቷ ቤተክርስቲያን የሚለዩባቸውን ነጥቦች ግልጥ አድርጋችሁ ብታቀርቡ ብዙ ወገኖችን መታደግ ትችላላችሁና አስቡበት

*ፍሬ ጽድቅ ቅዱሳን /ደሴ/*

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው ተሳታፊዎች ጽሑፎቻችሁ፣ ጥያቄዎቻችሁና አስተያየቶቻችሁ ደርሰውናል:: አስተያየቶቻችሁን ተቀብለናል:: ጥያቄዎቻችሁ ጊዜያቸውን ጠብቀው ይመለሳሉ:: የአንዳንዶቻችሁ ጥያቄዎች የሚመለከታቸው ዓምዶች ትምህርት የተሰጠባቸው ስለሆኑ ተመልሳችሁ ከዚህ በፊት የወጡትን የሐመር መጽሔቶችንና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጦችን ብታገላብጡ መልካም ነው:: በተረፈ በተሳትፎአችሁ አትለዩን::

መ/ር አበበ ባቱ /ጋምቤላ/፣ ዲ.ሲሳይ በፍቃዱ /ኮተቤ/፣ መ/ር ደረጀ ተድላ /ሞላሌ/፣ ሀብታሙ ጌታቸው /አ.አ/፣ ኃ/ሚካኤል ግዛው/አሶሳ/፣ ሀብታሙ ይልማ /አሰላ/፣ ዲ.ንዋይ ካሣሁን /ቅ/ሥላሴ ኰሌጅ/፣ ሲሳይ ዓለማየሁ /አዲስ አበባ/፣ ስንታየሁ ዘላለም /አ.አ/፣ ብርሃኑ ደጀኔ /ጋምቤላ/፣ ዲ.በለጠ ኃ/ማርያም /በቆጂ/፣ ፍቅረ ማርያም /ጊምቢ/፣ ወለተኪዳን /ደንቢዶሎ/፣ ሕይወት ታደሰ /አ.አ/፣ መ/ር ወርቅዓለማሁ ንጋቱ /ነጌሌ ቦረና/፣ መ/ር ከንፉ በቃቢል /መርጡለማርያም/፣ ታየሽኝ ሳንተይደሩ /አዋሳ/ ዳኛቸው አምበርብር /ዘአሶሳ/፣ መስፍን አዱኛ /መካከለኛ አዋሽ/፣ ግዛው ሔሞ /አ.አ./፣ ገረመው መክብብ /አ.አ/፣ ድረስ ጋሹ/አ.አ/፣ ዕንቁ አሥራት /ማሻ/፣ ዳዊት ምትኩ /አሰላ/፣ መሰለ ገ/ሕይወት /ደሴ/፣ በቀለ /ቦንጋ/፣ ሳሙኤል ካሣ /ሞላሌ/፣ ሙሉነህ ተሾመ /ግራዋ/፣ ዲ.ሲሳይ ኃይሌ /ጊምቦ/፣ ፍቅሩ ጋሩማ /ኩሪት-ማጂ/፣ ሰሎሞን ዓባይ /ድሬደዋ/፣ ተማሪ ደጀኔ ወርቁ /አቃቂ/፣ ዲ.ወ/ሚካኤል ካሣ /ማሻ/፣ ተስፋዬ በየነ /ጎሐጽዮን/፣ ዲ.ኃይሉ ጥይቴ /አርጆ/፣ ካሣሁን በየነ /ነጆ/፣ ዓለም ወንድሙ /አ.አ/፣ ተ/ወልድ ነሪ /ሻኪሶ/ ተማሪ መልካሙ ደርሶ /አምቦ እርሻ ኮሌጅ/፣ ግርማ ሺፈራው /ዴኒቨር አሜሪካ/፣ የዓለማያ ዩኒቨርሲቲ መንፈሳዊ ተማሪዎች፣ ተማሪ ኪሮስ አባየ /መቀሌ/፣ አበበ ደሳለኝ /ሚዛን ተፈሪ/፣ ቴዎድሮስ ዳኘው /ሰ.ጐንደር-ድል ይብዛ/፣ አምለሰት ኃይሌ /ነጌሌ/፣ ፍሥሐ እንግዳወርቅ /ድሬደዋ/ ተመስገን አበበ /መተማ ሆስፒታል/፣ ኃ/ማርያም ወ/መድኅን /ይርጋጨፌ/፣ ማኅተም አያሌው /አዴት/፣ መሰለ አባተ/ደሴ/፣ አብርሃም አየለ /አአ/ ተማሪ ሐረጓ ካሣ /ማሻ/፣ ኪሩቤል ሞገስ /አሰላ/፣ ደረጀ ንጉሤ /የካ ሚካኤል/፣ ሞላ ረጋሣ /ሲዳሞ ለኩ/፣ ሰሎሞን ተሥገራ/ አሰበ ተፈሪ/፣ አሸናፊ ጥላሁን /ጎባ/፣ ኃ/ሚካኤል በለጠ /ጅማ/፣ ዐወቀ /ዱራሜ/፣ ተስፋዬ ባለሚል /አጋሮ/፣ ተማሪ ዘላለም ጥሩነህና ደረጀ አጥናፌ /አቃቂ/፣ ሳምሶን ዓለሙ /አ.አ/ ዲ.አማኑኤል አብዲሳ/ነጆ/፣ዲ. አብነት አረጋ/ማጂ/፣ የምሥራች በቀለ/በበቃ/፣ መ/ር ዘካርያስ እሸቱ /ጐሬ/፣ በእምነቱ /ደሴ/፣ ማሕሌት ኃ/ኢየሱስ /አ.አ/፣ ተማሪ እንዳለ ትባ /ቡታጅራ/፣ ሠይፈ ሚካኤል/አ.አ/፣ ኢየሩሳሌም መለሰ /ሙገር/ ተስፋዬ አበበ /ጎሬ/፣ መ/ር ነጋ ጣሴ /ወገዳ/፣ አቶ ጆቴ ቱሉ /ባቲ/ ኃ/ማርያም /ጌዶ/፣ መ/ር ዘመኑ አበራ /ደራ/፣ ተማሪ እንደሻው ሰሎሞን /ሚዛን ተፈሪ/ ፣ዲ. ዓልማየሁ /ደነባ -ጅማ/፣ መ/ር ጥላሁን ቦዴቲ /ሁምቦ/፣ ማንደፍሮ ተሾመ /አሰበ ተፈሪ/፣ ተማሪ አዳሙ አየለ /ባሕር ዳር/፣ ማርእሸት ዓለሙ /አ.አ/፣ ሥዩም እሥራኤል/በረኸት ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት/፣ ዲ.መልአኩ ግርማ /ሻሸሜኔ/ ፣መ/ር መለሰ መሸሻ/ጊምቦ/፣ ተማሪ መኮንን አበበ /ሸቦካ/ ፣መ/ር ምግባር ልየው/ ዓርብ ገበያ-ታች ጋይንት/፣መ/ር ኩምሻ ዩፎ /ሰሜን ኦሞ ደቦጭ/፣ምንተስኖት ዐወቀ/አሰላ/፣ ኃ/ኢየሱስ መርሻ /ኮተቤ መ/ት ኮሌጅ/፣ወለተ ኢየሱስ /ጎፋ ገብርኤል ቤ/ክ/፣ይርጋ ዓለም ከበደ /አምቦ/፣ አክሊሉ ይርዳው /ደሴ/፣ አቶ ይረጋ ክብረት /ጅጅጋ/፣ ሥዩም ባሕሩ /አ.አ/፣ እሥራኤል ተረፈ ጉዳና ተስፋዬ /ያቤሎ/ ፣ካሡች ዮሐንስ /አጋሮ/::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ክረምት የክርስትና ምሳሌ ሊሆን ይችላል:: ገበሬ በወርኃ ክረምት ብርዱንና ዝናሙን ሳይሰቀቅ ለሥራ ይሰማራል:: በበጋው የእጁን ፍሬ ያገኝ ዘንድ የክረምቱን መከራ ይታገሳል:: ክርስቲያንም በዚህ ምድር ላይ የሚደርስበትን መከራ ሁሉ በጸጋ የሚቀበለው በዚያኛው ዓለም ስለሚያገኘው ተድላና ደስታ ሲል ነው::

ነቢየ ልዑል ቅዱስ ዳዊትም «በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ፤» ብሏል:: በተጨማሪም «በሄዱ ጊዜ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሰማሩ፣ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ፤» በማለት የመንፈሳዊ ጉዞን ምሥጢር ከግብርና ሙያ አንፃር አመለከተ::/መዝ 125

የሚነበበውም ምንባብ ይህንኑ የተመለከተ ይሆናል:: በወቅቱ የመጣ ውደመና ታይቶ የሚያልፍ ሳይሆን ዝናፀ-ምሕረቱን ለምድር እንዲሰጥ «አዝዞሙ ለደመናት፣ ያውርዱ ዝናመ ዘቀዳሚ ወዘደኃሪ፤ የፊተኛውንና የኋለኛውንዝናብ ይሰጡ ዘንድ ደመኖችን እዘዛቸው» እያለች ትጸልያለች:: አያይዛም «ትልምዋን ታረካለህ ቦይዋንም ታስተካክላለህ፣ በነጠብጣብ ታለሰልሳታለህ፣ ቡቃያዋንም ትባርካለህ::» በማለት የእግዚአብሔርን ቸርነት ታመሰግናለች::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ «እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ::...ሌላውም በመልካም መሬት ወቀደ:: አንዱም መቶ፣ አንዱም ስድሳ፣ አንዱም

ቾግረው በኃጢአት ጨለማ የተያዘውን ዓለም በትምህርታቸው እንዲያበሩ የተላኩት የ72ቱ አርድእት ዝክረ ነገር ይወሳል:: /ሉቃ 10÷17–25/::

*3 ከማኅበር——አብርሃም /ነሐሴ 29/* ዘመነ ክረምት የሚጋመስበት ነው:: ዝናቡ ይቀንሳል፣ ምድሪቱም መቀዝቀዝና መጠንከር ትጀምራለች:: «ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት፣ ቡሄ ካለፈ የለም ክረምት» እንዲባል በክረምት ዝናብ ተደብቀው የነበሩ አዕዋፍ ከበአታቸው ይወጣሉ:: ጥበበኛው ሰሎሞን «አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ፣የዜማም ጊዜ ደረሰ የቁርዬውም ቃል በምድራችን ተሰማ::» መኃ2÷12:: ሲል እንደተናገረው የአዕዋፍ የምሥጋና ድምፅ ይሰማል::

# ወርኃ ክረምት በቤተክርስቲያን ትምህርት

እንግዲህ ስለመንግሥተ እግዚአብሔር ስንል የሚደርስብንን ጸዋትወ መከራ ሁሉ ለመቀበል መዘጋጀት ይገባል:: ሐዋርያውም «በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው:: ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና::» /ያዕ 1÷1–13/ እንዳለ በጾም፣በጸሎትና ንስሐ በመግባት እና ሥጋን ለነፍስ በማስገዛት እንትጋ:: «ኑ እናንተ የአባቴ ቡሩካን» የሚለውን ቃል ለመስማት እስክንበቃ ድረስ በጀመርነው መንፈሳዊ ጉዞ እንድንበረታ ቤተክርስቲያን ከወቅቱ ጋር አስማምታ ታስተምረናለች::

ዓመቱን በአራት ወቅቶች ጸደይ–የዘር ወቅት፣ ክረምት የዝናም፣ መጸው የነፋስ፣ሐጋይ /በጋ/ ርጥበት የሌለበት ደረቅ ወቅት ብላ በመክፈል በወቅቱ ከሚታየው የተፈጥሮ ሁኔታ ጋር ምእመናን ሕይወታቸውን እንዲመረምሩ፣ ለንስሐ እንዲበቁ አጥብቃ ትመክራለች::

ያለንበት ወቅትም ክረምት በመሆኑ በቤተክርስቲያናችን የሚነገረውን ትምህርት እንዲህ እናያለን:–

*1.ከበአተ ክረምት –ሐምሌ ቂርቆስ*

ከሰኔ 25 እስከ ሐምሌ 19 ያለው ጊዜ ነው:: ዘርእ፣ ደመና፣ምሳሌ ዘርእ፣ ጊሜ፣ ክረምት ይባላል::

ሠላሳ ፍሬ ሰጠ::» /ማቴ13÷3–8/ያለውን ኃይለ ቃል ጠቅሳ ልጆቿ እንደመልካሟ ምድር በጐ ምግባር እንዲኖራቸው ትመክራቸዋለች:: ከሃይማኖት ከምግባር የተዘናጉትንም «ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት ለሚያርሱአትም ደግሞ የምትጠቅምን አትክልት የምታበቅል ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለች:: እሾህንና ኩርንችትን ግን ብታወጣ የተጣለች ናት፤ ለመረገምም ትቀርባለች፤ መጨረሻዋም መቃጠል ነው::» እንዳለ ፍሬ አልባ ማሳዎች እንዳይሆኑ ታሳስባቸዋለች:: /ዕብ 6÷7–8/

*2 ከሐምሌ ቂርቆስ – ማኅበር /ሐምሌ 29/*

መባርቅት የሚበርቁበት፣ ባሕርና አፍላጋት የሚሞሉበት፣ ምድር ጠል የምትጠግብበት ወቅት ነው:: «ደመናት ድምፅን ሰጡ፣ ፍላጾችህም ወጡ፣ የነጐድጓድህ ድምፅ በዐውሎ ነበር:: መብረቆች ለዓለም አበሩ::» ሲል ቅዱስ ዳዊት የተናገረው ይሰበካል::/መዝ76÷17–18/ ደመኖች ታይተው፣ መባርቅት ባርቀው፣ የነጐድጓድ ድምጽ እንዲሰማ ጌታችን ከዓለም ጠርቶ፣ አስተምሮ ወንጌለ መንግሥትን

ቤተክርስቲያንም «የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል፣ አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ:: አንተ እጅህን ትከፍታለህ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ::» እያለች ቅዱስ ዳዊት «ለሥጋ ሁሉ ምግብን የሚሰጥ ምሕረቱ ለዘላለም የሆነውን የሰማይ አምላክ አመስግኑ::» እንዳለ እግዚአብሔርን ታመሰግናለች:: /መዝ 144÷15–16፣ 135÷25–26/

በተጨማሪም ከነሐሴ 27–29 ያለው ጊዜ «ሞተ–አበው» በመባል ይታወቃል: ከ22ቱ አርዕስተ–አበው የነ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብና ቤተሰባቸው ዕረፍት ይታሰባል:: «አዕረጐ አብርሃም ለይስሐቅ ወልዱ ከመ ይሡዖ፣ አውረደ ሎቱ ቤዛሁ በግዑ እኁዝ አቅርንቲሁ በዕፀ ሳቤቅ» ማለትም «አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ሊሠዋ ወጣ:: እግዚአብሔር ቤዛ አድርጐ ቀንዱ በዕፀ ሳቤቅ የተያዘ በግ አወረደለት፤» በማለት የአብርሃም ታዛዥነት፣ የይስሐቅ ቤዛነት ይወሳል:: የተቀበሉትም ቃል ኪዳን «ወተዘከረ ሣህሎ ዘለዓለም ዘሠርዓ ለአብርሃም፣ ወመሐለ ለይስሐቅ ወዐቀመ ስምዐ ለያዕቆብ፣ ያርኁ ክረምተ፣ ይገብር ምሕረተ እምሰማይ ይሁብ ወእምድር በረከተ ያጽግብ ነፍሰ ርኁበተ::» በማለት ይዘመራል::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

*4.ከአብርሃም-ዮሐንስ /ዘመን መለወጫ/*

የዓመቱ መገባደጃ ነው:: በሐምሌና በነሐሴ ደመና ተሸፍና የነበረችው ፀሐይ ፍንትው ብላ መውጫዋ የደረሰበት ጊዜ በመሆኑ ኅህ፣ ጽባሕ፣ መዓልት፣ ነግህ፣ ብርሃን ተብሎ ይጠራል:: የክረምቱ ጭፍን ጨለማ ሊያከትም ብርሃን ሊበራ የተቃረበበትመሆኑ በቤተክርስቲያን ይበሰራል:: በሊቀ መልአኩ በቅዱስ ሩፋኤል እጅ የጦቢያን ዓይን እንዳበራ የምእመናንን ዓይነ ልቡና እግዚአብሔር እንዲያበራ ይጸለያል::

ከዚሁ ጋር የክረምቱ ደመና ዝናብና ቅዝቃዜ ከብዶባቸው የዘመን መለወጫን የፀሐይ መውጫን ቀን በጉጉት ለሚጠባበቁ ምእመናን «ነፍሳችሁን ተመልከቱ፣ ሰውነታችሁን ንጽሕ አድርጉ» ስትል ለበለጠ መንፈሳዊ ትጋት ታነቃቃቸዋለች:: ክረምት ሊያልፍ የስማዩ ዝናብ የምድሩ ጭቃ ሊቀር እንደሆነ ሁሉ በዚህች ዓለም መከራ ተይዘው ላሉ ክርስቲያኖች ክርስቶስ በክብር የሚገለጽበት ዓለም የምታልፍበት ዕለት ባላሰቧት ጊዜ እንደምትመጣ እንዲገነዘቡና በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እንዲያብቡ «እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል:: አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም፤ እሳት በፊቱ ይነድዳል» መዝ 49÷2-3:: እያለች ትመክራቸዋለች::

*5. ከዮሐንስ /ዘመን መለወጫ/-ዘካርያስ /መስከረም 8/*

የዘመን መለወጫ፣ አዲስ ተስፋ በምእመናን ልብ የሚለመልምበት ጊዜ ነው:: የተተነበየው ትንቢት፣ የተቆጠረው ሱባኤ ተፈጸመ፤ ከዘመነ ፍዳ ወደ ዘመነ ምሕረት የምትሸጋገሩበት ጊዜ ደረሰ እያለ ያወጀው የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ዜና ይነገራል:: «ምሕረትና እውነት ተገናኙ፣ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ፣ እውነት ከምድር በቀለች::» /መዝ 84÷10-11/ እያለች ስለ እውነት ሊመሰክር የመጣውን የቅዱስ ዮሐንስን ሕይወት እናት ቤተክርስቲያን ለልጆቿ እንደ እርሱ እውነተኞች እንዲሆኑ ለእውነት እንዲተጉ ታስተምራለች::

ሰማዩ፣ውኃው የሚጠራበት ጊዜ በመሆኑ ልጆቿም ከብልየት እንዲታደሱ፣ በመንፈስ እንዲጐለምሱ ኰርኵሰት፣ ከጣዖታት፣ከቂም፣ ከበቀል እንዲጠሩ፣ እንዲነጹ «የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም፣ በስካርም፣ በዘፈንም ያለልክም በመጠጣት፣ ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና፤» /1ኛ ጴጥ 4÷3/ በማለት አሮጌውንና በርኵሰት የተሞላውን ሕይወታችንን ከዘመኑ ጋር አሳልፈን የምድር አበቦች እንዳበቡ በእምነት በምግባር እንድናብብ በሰፊው ታስተምረናለች::

*6. ከዘካርያስ ማግስት - ሕንፀት /መስከረም 16/*

ሳምንቱ ፍሬ በመባል ይታወቃል:: በሰኔ፣ በሐምሌ የተዘራው ዘር ለፍሬ መብቃቱ የሚታሰብበትና እንደ ቅዱስ ዳዊት «ምድር ፍሬዋን ሰጠች፣ እግዚአብሔር አምላካችንም ይባርከናል፣ እግዚአብሔር ይባርከናል» /መዝ 66÷6/ ተብሎ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ሳምንት ነው:: ፍሬውም ከቁር፣ ከበረዶና ከትል ተርፎ ለጐተራ እንዲበቃ ቅድስት ቤተክርስቲያን በሥርዓተ ቅዳሴዋ «በእንተ ፍሬ ምድር ናስተበቊዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦ ፍሬሃ ለምድር ለዘርእ ወለማእረር» ማለት «ለዘርና ለመከር ሊሆን እግዚአብሔር ለምድር ፍሬዋን ይሰጣት ዘንድ ስለምድር ፍሬ እንማልዳለን::» በማለት አምላኳን ትማጸናለች::

ምእመናንንም «ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ» /ማቴ 24÷20/ ሲል መድኃኔዓለም እንዳስተማረው የሃይማኖት ፍሬ ምግባርን፣ ትሩፋትን ሳይሠሩ በልምላሜ /በሃይማኖት/ ብቻ ሳሉ እንዳይጠሩ ለንስሐ፣ ለሥጋወደሙ የበቁ ይሆኑ ዘንድ ትጸልይላቸዋለች::»

*7. ከመስከረም 17-ፀአተ ክረምት /መስከረም 26/*

ነገረ መስቀለ ክርስቶስ የሚነገርበት ነው:: በቅናት ተነሳስተው አይሁድ የቀበሩት የጌታችን መስቀል በእሌኒ ንግሥት ትጋት ከሦስት መቶ ዓመት በኋላ ተቆፍሮ የወጣበት ዕለት ይታሰብበታል:: በቤተክርስቲያን የሚነገረውም ቃል የመስቀሉን ክብር የሚመለከት ሲሆን ቅዱስ ዳዊት «ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው፣ ወዳጆችህ እንዲድኑ::» /መዝ 59÷4-5/ ያለውም ይሰበካል:: ጊዜው የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ያፈሩበት፣ የመስቀሉ ብርሃን ለዓለም ያበራበት በመሆኑ «የመስቀሉ እንቅፋት ተወግዷልና» ምእመናን ይደሰታሉ:: /ቆላ2÷14-15/ የተወገደውን ጠላታቸውን ዲያብሎስንም በመስቀሉ ድል ይነሱታል::

ስለዚህ እናት ቤተክርስቲያን በጊዜ ውስጥ ላለነው ራሳችንን ከጊዜው ጋር እንድናነጻጽር ወቅቱን የተመለከተ ትምህርት አዘጋጅታ ልጆቿን ለሰማያዊ መንግሥት ዝግጁ እንዲሆኑ ታስተምራቸዋለች:: በዚህም በጊዜ ውስጥ ተፈጥሮን ዐይተን፣ አገናዝበን የምንማር፣ ለንስሐ የተዘጋጀን ስንቶቻችን ነን? «ቁም የእግዚአብሔርንም ተአምራት አስብም» እንዳለ /ኢዮ37÷14/ ያለንበትን ሕይወት አስበን ለንስሐ እንበቃ ዘንድ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን በረከት አይለየን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

*እስከ መቼ?*

እስከመቼ «ኪርያላይሶን»
እስከ መቼ «ተሰሃለነ»
በኃጢአት ልብ ነቅዞ
በቂም በቀል ተገንዞ
አንደበት ሲወሰልት
ልጅነት ውሉን ሲስት
እስከመቼ «እግዝእትነ»
ፍቅር ባጣ ባልፀና ልብ በባከነ
በሐሰት ለምጽ ተሸፍኖ
በኃጢአት ፍም ከሥሎ ደብኖ
ኅሊናችን ሳይመለስ
የድንጋይ ልብ ተሸክመን
የበደል ቀንበሩ ከብዶን
እስከመቼ «እግዚ.እትነ»
ባልፀና ልብ በባከነ
እስከመቼ ኪርላይሶን
በኃጢአት ላይ ተኮፍሰን

*ዲ.አትናቴዎስ ተፈራ*
*/ከአዳባ ቀራንዮ መድኃኔዓለም ሰ/ት/ቤት/*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ብሉይ ኪዳን

ዲ. ደጀኔ ሽፈራው

ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን አምሳል እና መርገፍ መሆኑን ባለፉት እትሞቻችን በሚገባ ተማምረናል:: በዚህም ብሉይ ኪዳን መነሻ እና ንባብ፣ሐዲስ ኪዳን መድረሻ እና ትርጓሜ መ፤የናቸውን ዐውቀናል:: በተጨማሪም ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን፣ሐዲስ ኪዳንም ለብሉይ ኪዳን ምስክሮች ናቸው፤ ከሚለው ግንዛቤ ደርሰናል:: በዚህ እትማችን ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን እያገናዘበ እና እያነጻጸረ የጻፈውን መልእክት ለመመልከት እንሞክራለን::

## 1ኛ የድንጋይ ጽላት እና የልብ ጽላት:-

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን «ሰዎች ሁሉ የሚያውቁት እና የሚያነቡት በልባችን የተጻፈ መለእክታችን እናንተ ናችሁ:: እናንተም በሕያው በእግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም:: ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደሆናችሁ የተገለጠ ነው::» በማለት ጽፎላቸዋል:: ከዚህም ጽሑፍ በመነሣት የሚከተሉትን ነጥቦች እናያለን::

### ሀ/ የድንጋይ ጽላት

ከእብነ በረድ የሆነውን ጽላት ለነቢያት አለቃ ለሙሴ የሰጠው፣ ኋላም ጽላቱ በተሰበሩ ጊዜ አንተ እንደ ፊተኞቹ ዓይነት አድርገህ አዘጋጅ ፣ትእዛዛቱን ግን እኔ እጽፍበታለሁ ብሎ በሙሴ እጅ እንዲዘጋጅ ያደረገ እግዚአብሔር ነው:: ዘጸ 34÷1–28:: በአዲስ ኪዳንም ለሚወደው ደቀመዝሙሩ ለቅዱስ ዮሐንስ ሰማያዊውን ቤተ መቅደስ ከፍቶ የታቦቱን ክብርና ኃይል አሳይቶታል:: ራእ 11÷19::

ሐዋርያው በዚህ መልእክቱ ምእመናንን «በልባችን የተጻፈች መልእክታችን እናንተ ናችሁ::» ብሏቸዋል:: ይህም «በልባችን ታውቃችኋል፤» ማለቱ ነው:: ቀጥሎም «እናንተም በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም::» ማለቱ ጽሕፈቱን ተናግሮ መጻፊያውን አልተናገረም ነበርና ነው:: ስለሆነም የተጻፋችሁት /በልቡናችን የታወቃችሁት/ በጥቁር ቀለም አይደለም፤ የሕያው እግዚአብሔር ሕይወት በሚኾን በመንፈስ ቅዱስ ቀለምነት ነው እንጂ አላቸው::

«ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻተፈ» ሲል ደግሞ በድንጋይ ሰሌዳነት አይደለም:: የሥጋ ልብ /ሕይወት/ በምትኾን በምታስብ በምትናገርና ሕያው በሆነች ነፍስ ሰሌዳነት ነው እንጂ ሲላቸው ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ ልቡናቸውን በጽላት መስሎት እንዲህ አድርጎ ያስተማረው ቃሉን በልቡናቸው በማሳደራቸውና ልክ እንደ ጽላቱ ቀርጸው በማስቀረታቸው ነው እንጂ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ጽላተ ሙሴ ለመንቀፍ ፈልጎ አይደለም:: ከዚህም በማያያዝ «በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደሆናችሁ የተገለጠ ነው፤» ብሏል:: ይህም እኛ የፋቅናት የራመምናት እኛ የዳመጥናት የክርስቶስ የመልእክቱ መጻፊያ እንደኾናችሁ የታወቀ ነው::» ማለቱ ነው:: ትርጓሜውም «እኛ ያስተማርናችሁ ያጠመቅናችሁ እና ያቆረብናችሁ የክርስቶስ ማደሪያ ናችሁ» ማለት ነው:: እዚህም ላይ ልቡናቸውን በመልእክት መጻፊያ ወረቀት /ብራና/ መስሎታል::

## 2ኛ ፊደል ይገድላል፤ መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል::

ፊደል የተባለ ኦሪት/ንባብ/ ሲሆን መንፈስ የተባለችው ደግሞ ትርጓሜ ኦሪት የሆነችው ወንጌል ናት:: ይኸንንም ሐዋርያው «በክርስቶስም በኵል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ እምነት አለን:: ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ በገዛ እጃችን እንደሚኾን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም፤ እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይኾን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንኾን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል::» በማለት ገልጦታል:: የዚህንም ምሥጢር በሚገባ ለመረዳት እንድንችል እያንዳንዱን እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን::

ሀ.«በክርስቶስም በኵል ወደ እግዝአብሔር እንዲህ ያለ እምነት አለን::» ሲል «ወልድ ዋሕድ ብለን በክርስቶስ በማመናችን ስሙም ሕይወት መድኃኒት ነው ብለን በማስተማራችን እንዲህ ያለ ተስፋ አለን፤» ሲላቸው ነው:: ተስፋውም «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፤ እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር::» የሚለው ነው::ዮሐ14÷6:: መንገድ የተባለው ሃይማኖት ነው፤ ምክንያቱም ሃይማኖት ፍኖተ እግዚአብሔር ነውና:: ኤር 6÷16::
ጌታችን «እኔ መን ገድ ነኝ፤» ሲል «እኔ ሃይማኖታችሁ ነኝ፤» ማለቱ ነው:: «ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፤» ሲል ደግሞ እርሱን ክዶ «አብን አምኛለሁ፤» ማለት እንደማይቻል ሲነግራቸው ነው:: ምክንያቱም ወልድን የማያከብር የላከውን አብንም አያከብርምና ዮሐ 5÷23:: አንድም ወልድ የተናገራትን ወንጌል ያላመነበት እና የወልድን ሥጋና ደም በእምነት ያልተቀበለ ሰው መንግሥተ ሰማያትን አይወርስም ማለት ነው::

ለ.«ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳን ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም፤» ሲል ደግሞ «ብቃታችን ማለትም ኃይላችን ከእግዝአብሔር ዘንድ መኾኑን ልናስብ እንጂ በክንዳችን ወይም በጉልበታችን እንደኾነ አድርገን ራሳችንን ልናመሰግን አይገባም::» ሲል ነው:: «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ::» እንዲል:: ፊል4÷13::

ሐ.«እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይኾን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንኾን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል::»



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በሐዲስ ኪዳን

የሚለውም ትርጉሙ እንደሚከተለው ነው:: «አገልጋዮች ያደረገን በሕገ ነፍስ በወንጌል፣በትርጓሜ ነው እንጂ በሕገ ኦሪት በንባብ አይደለም:: ፊደል /ንባብ/ ትርጉሙ እስካልታወቀ ድረስ ያደናግራል፤ ይህም በመጀመሪያ ለመናፍቅነት ያጋልጣል፣በኋላም ለዘለዓለም ሞት አሳልፎ ይሰጣል:: መንፈስ ማለትም የንባቡ ትርጓሜ ግን ይጠቅማል- ለአክሊለ ሕይወትም ያበቃል» ማለት ነው::

*3ኛ/ የሞት /የኩነኔ/ እና የመንፈስ /የጽድቅ/ አገልግሎት*

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ኩነኔ እና ስለ ጽድቅ አገልግሎት ሲናገር «ዳሩ ግን የእሥራኤል ልጆች ስለ ዚያ ስለተሻረው ስለ ፊቱ ክብር የሙሴን ፊት ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም? የኩነኔ አገልግሎት ክብር ከሆነ፣ ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት በክብር አብዝቶ ይበልጣልና:: ያ የከበረ እንኳ እጅግ በሚበልጠው ክብር ምክንያት በዚህ ነገር ክብሩን አጥቷልና:: ያ ይሻር የነበረው በክብር ከሆነ ጸንቶ የሚኖረውማ እጅግ ይልቅ በክብር ሆኗልና::» ብሏል::

ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከደብረ ሲና ሲወርድ ሁለት የምስክር ጽላት በእጆቹ ነበሩ:: ከእግዚአብሔር ጋር ስለተነጋገረም የፊቱ ቁርበት እንጸባረቀ:: ሕዝቡም ተሸፈንልን አሉት:: በኋላ ግን በፊቱ ላይ ተሥሎ የነበረው ኃላፊ ብርሃን ቀርቶ /ተሽሮ/ ያለችግር ፊት ለፊት ያዩትና ያነጋግሩት ነበር:: ቅዱስ ጳውሎስም ይኸንን አስታውሶ «እሥራኤል፡- በፊቱ ኃላፊ ብርሃን ስለተሣለበት፣የሙሴን ፊት ማየት የማይቻላቸው እስኪኾን ድረስ በደንጊያ ስሌዳነት የተጻፈች እና ምሳሌ ለምትኾን ለዚያች ለሕገ ኦሪት ክብር ከተደረገላት፣ አማናዊት ለኾነች ለወንጌልማ ምን ያህል ክብር ይደረግላት ይኾን?» አለ::

ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ የተጠቀሰውን ማለቱ አማናዊት ሕግ ለሆነች ለወንጌል የክብሯን ታላቅነት ሲናገር እንጂ ጽላትን ለማንቋሸሽ አይደለም:: ምክንያቱም ጽላቱን በቅድሚያ ያዘጋጀ ኋላም ሙሴ በተሰበሩት ምትክ እንዲያዘጋጅ የፈቀደ እግዚአብሔር ነውና:: ዘጸ 34÷1-28:: እንዲያውም በመጀመሪያ ጽላቱን አንተ አዘጋጅ እኔ ደግሞ ትእዛዛቱን እጽፍበታለሁ ብሎት ነበር:: በመጨረሻ ግን ሙሴ ራሱ እንዲጽፍ ፈቅዶለታል:: ከዚህም በሙሴ እጅ ቃሉን የቀረጸ እግዚአብሔር መሆኑን እናስተውላለን::

በጽላቱ ላይ የተቀረጹት አሠርቱ ትእዛዛት የእግዚአብሔር ቃሎች ናቸው:: እነርሱም 1ኛ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ 2ኛ የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ 3ኛ የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ:: 4ኛ አባትህንና እናትህን አክብር፤ 5ኛ አትግደል 6ኛ አታመንዝርና 7ኛ አትስረቅ 8ኛ በሐሰት አትመስክር 9ኛ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ 10ኛ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ:: የሚሉት ናቸው:: የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ የተሻረ አይደለም:: ሮሜ 9÷6:: ቃሉ ሕያውና ዘለዓለማዊ ነው:: በመሆኑም የተሻረውና ያለፈው በሙሴ ፊት ላይ ተሥሎ የነበረው ኃላፊ ብርሃን ነው:: ቅዱስ ጳውሎስም ቀረ፣ አለፈ፣ ተሻረ ያለው ከክብሩ የተነሣ ያገኘውን ይኼንኑ የፊቱን ብርሃን ነው:: ምሳሌነቱንም የጨረሰው በኦሪቱ የነበረው ሥርዓት ነው:: ለምሳሌ የመሥዋዕቱ ሥርዓት ማለትም የበግ የፍየል እና የጊደር ደም ማፍሰስ አልፏል:: ምክንያቱም የአዲስ ኪዳን በግ ማለትም አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ የተሠዋው የዘላለሙ መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና:: በመሆኑም ተሻረ የሚለውን ቃል ትርጓሜውን በመረዳት ምሥጢሩን ማስተዋል ከስህተት ይጠብቃል::

ጌታችን በወንጌል «ብፁዓን፣ ብፁዓን» እያለ ያስተማረውን ትምህርት አይሁድ ሰምተው «ይህስ ኦሪትንና ነቢያትን ሊያሳልፋቸው መጥቷል፤» እንዲሉት ዐውቆ «እኔ ሕግንና ነቢያትን ልፈጽም /ፍጹማን ላደርጋቸው፤» ነው እንጂ ልሽራቸው /ላሳልፋቸው/ አልመጣሁም::» ብሏቸዋል:: ማቴ7÷17:: ለምሳሌ አት ግደልን፣ በአትቆጣ፣ አታመንዝርን ደግሞ በፈጽሞ አትመኝ::» አጽንቷቸዋል:: ይህንንም «ለቀደሙት አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉፍርድ ይገባዋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያንጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል::» በማለት ገልጦታል:: ይህም የኦሪትን ሕግ ይበልጥ እንዳጸናት እንዳልሻራትም ያስተምራል::

*ሀ የሞት /የኩነኔ/ አገልግሎት*

የሞት /የኩነኔ/ አገልግሎት የተባለችው ሕገ ኦሪት ናት:: የሞት አገልግሎት መባሏም ስለ ሁለት ነገር ነው::

*1ኛ.* ኃጢአትን ቆጥራ ቆጥራ ትናገር ሞትንም ታስፈርድ ስለነበረ ነው:: ይቅርታ አልነበራትም፤ ምክንያቱም የገደለ ይገደል ነበር:: ዘሌ 24÷17:: በሌላ በኩል ደግሞ ምን ቢፈጽሟት በኃጢአተ አዳም ምክንያት በዘር ይተላለፍ ከነበረው ሞት ከሞተ ነፍስ አታድንም ነበር:: የፈጸሟትም ሁሉ ሞተ ነፍስን ሞተው ወደ ሲኦል ወርደዋል:: ይኸንን በተመለከተ ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ለሮም ምእመናን ሲጽፍላቸው «ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ ...ሞት ነገሠ» ብሏል:: ሮሜ 5÷14::

*2ኛ.* በቀደመው ታቦት ላይ ይሠዋ የነበረው በግ ቢበሉት የዘለዓለምን ሕይወት የማይሰጥ እና እርሱም ራሱ ዘለዓለማዊ ያልሆነ ሟች ስለነበረ ነው:: ይኸም የሆነው የአዳም ኃጢአት የሚሰረየው በጌታችንና በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ብቻ ስለነበረ ነው::

ስለሆነም አንድ ማስተዋል የሚገባን ነገር ቢኖር ሕገ ኦሪትንም አስቀድሞ በሙሴ አድሮ የሠራ ፣ኋላም በሥጋ ተገልጦ ያጸና እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ የወንጌልን ክብር ለመግለጥ ብሎ የተጠቀመበትን ቃል ምሥጢሩ ሳይገባን የማይገባ ነገር ከመናገር መጠበቅ አለብን:: ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ «የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ ደግሞ እንደተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፣በመልእክቱም ሁሉ እንደተናገረ ስለዚህ ነገር ተናገረ:: በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎች መጻሕፍትን እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ:: እንግዲህ እናንተ ወዳጆች ሆይ ይኸንን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ በዓመፀኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ::» ያለው ለዚህ ነው:: 2ኛ ጴጥ 3÷15-17

ይቀጥላል...



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የእግዚአብሔር ሕግ

በዲያቆን እሸቱ ታደሰ

ካለፈው የቀጠለ

ባለፈው እትም ስለ ስመ እግዚአብሐር ክብርና በዚያው አንፃር የሰው ልጆችን ግዴታ ለማስቀመጥ ሞክረናል። በዚህ እትማችን ደግሞ የቀረውን የትእዛዙን ክፍል አቅርበናል።

**«የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት» ሲባል ምን ማለት ነው?**

የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም የከበረ በመሆኑ እንደተገኘ የሚጠሩት፣እንደአጋጠመ የሚናገሩት አይደለም። ይልቁንም በመፍራትና በመንቀጥቀጥ በትኅትና ሆነው ሊጠሩት የሚገባ ክቡር ስም ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ በነገራቸው ሁሉ ውስጥ ሲያስገቡት፣ሥፍራም ጊዜም ሳይመርጡ እንደፈለጉት ሲጠሩት ይስተዋላሉ። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች እምነትና ፈሪሃ እግዚአብሐር አላቸው ለማለት አያስደፍርም፤ ምክንያቱም የሚያምኑና እግዚአብሔርንም የሚፈሩ ቢሆኑ ኖሮ ለስም አጠራሩ የሚገባውን ክብር ይሰጡ ነበር።

ከዚህ ቀጥለን ሰዎች ስሙን በከንቱ የሚጠሩባቸውን ሁኔታዎች ባጭር ባጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን።

<u>ሀ/ መሐላ</u>፦ መሐላ ስመ እግዚአብሐር በከንቱ ከሚጠራባቸው መንገዶች አንዱ ነው። በዘመነ ብሉይ የአምልኮ ጣዖትን ከንቱነት ለመግለጥ እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡ በስሙ እንዲምሉ ያዝዝ ነበር። ዘዳ 6÷13።ኢሳ 45÷23 በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በእግዚአብሔር መማል ብቻ ሳይሆን መሐላ በጠቅላላው የተከለከለ መሆኑን መጻሕፍት ይናገራሉ። ይህ የሐዲስ ኪዳን ዘመን አረማዊነትና አምልኮ ጣዖት ጠፍቶ ወንጌል የተሰበከበት፣ ክርስትና በዓለም ሁሉ የታወቀበት ነውና መማል አላስፈላገም። ስለዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከቶ አትማሉ፤...ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፣ከዚህም የወጣ ከክፉው ነው» በማለት መሐላን ከልክሎአል። ማቴ 5÷34–37። ስለሆነም በየሰበቡ የእግዚአብሔርን ስም፣የቅዱሳንን ስም፣ የመላእክትን ስም ሁሉ እየጠሩ መማል የተከለከለ ነውና ከዚህ መቆጠብ ይገባል። በተለይም በየአጋጣሚው ስመ እግዚአብሔርን እየጠሩ መማል የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት መሆኑን በሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል። /ስለ መሐላ በሌላ ጊዜ ሰፊ ትምህርት የምናቀርብ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ለአንባብያን ለመግለጥ እንወዳለን።/

ለ. <u>/የእግዚአብሔርን ስም ማቅለል:</u> ይህም የእግዚአብሔርን ስም በሚገባው ክብር ሳይሆን እንደዋዛ መጥራት ነው። የእግዚአብሔርን ስም ከስድባቸውና ከእርግማናቸው፣ ከቀልዳቸውና ከጨዋታቸው፣ ከብስጭታቸውና ከዛቻቸው ጋር አስተባብረው የሚያነሡ ሁሉ በከንቱ እየጠሩት ነው። በዚህ መልክ ያቃለሉትን ስም በዚያው አንደበታቸው በጸሎትጊዜ ደግሞ «ስምህ ይቀደስ» ይሉታል። ማር ይስሐቅ ስለ ስመ አጠራሩ ሲናገር «የእግዚአብሔርን ስም በሚነድ እሳት ፊት እንደቆምን ሁሉ በሚገባው ክብርና ልዕልና፤ በመፍራትና በመንቀጥቀጥም ልንጠራው ይገባል» ብሏል። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ስም መቼ፣ የትና እንዴትም ሆነን ልንጠራው እንደሚገባን ማስተዋል የክርስቲያኖች ሁሉ ግዴታችን ነው፤ እርሱ ስሙን በከንቱ የሚጠራውን አይተወውምና።

በእርግጥ የእግዚአብሔርን ስም አክብረን ብንጠራው ለእርሱ ክብር የሚጨመርለት ሆኖ አይደለም፦ እርሱ በባሕርዩ የከበረ ስለሆነ የምንከብረው እኛ ነን እንጂ እርሱ አይደለም። ይሁን እንጂ ይህን ስም እቃ በወደቀባችው፣ውሻ በጮኸባቸው ቁጥር የሚጠሩ ሁሉ እያቃለሉትና በከንቱም እየጠሩት መሆናቸውን በመረዳት ከዚህ መቆጠብ ያሻል። በዚህ መልክ ስሙን መጥራት ወደ እርሱ ለመቅረባችን ወዳጁም ለመሆናችን ማስረጃ ተደርጎ ተቆጥሮ ከሆነም ስህተት ነው፤ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ማለት የእርሱን ባሕርይና የዚህን ክብር ወደ ማወቅ መድረስና በትሕትና ሆኖ በተገቢው ጊዜ መጥራት እንጂ ስሙን ከክብሩ በመለየት እንደተፀውዖ ስም /ሎቱ ስብሐት/ በየአጋጣሚው ሁሉ የመዘንጠል መብት ማግኘት ማለት አይደለም።

ስለሆነም አንደበትን ከልማድ በመቆጠብ የእግዚአብሔርን ቸርነቱን ከኃያልነቱ፣ትሕትናውንም ከባሕርይ ክብሩ ጋር እያነፃፀሩ በማስተዋልና በትሑት ልቡና ሆኖ ስሙን መጥራት ያስፈልጋል።

<u>ሐ/ እግዚአብሔርን ማማረር</u>፦ አንዳንድ ሰዎች በተቸገሩና ፈተናም በገጠማቸው ጊዜ እያንጐራጐሩ በእግዚአብሔር ላይ ያመካኛሉ እርሱንም ይከሳሉ በፊቱ ቆመው ላለመጸለይና ከእርሱም ለመለየት መወሰናቸውን እያወሱ ስሙን ይጠራሉ። ይህ ሁሉ ተገቢ ካልመሆኑም በላይ ስመ አምላክን በከንቱ መጥራት ነው፦በዚህ መልክና ሁኔታ ግን ክቡር ስሙን እንድንጠራ አልተፈቀደልንም። በመጽሐፍ እንደተነገረ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ የገሃነም እሳት የሚፈረድበት ከሆነ በእግዚአብሔር ላይ የሚያጉረመርም ደግሞ ምንኛ የባሰ ቅጣት ይጠብቀው ይሆን? /ማቴ 5÷22።/ ለክርስቲያኖች በሚሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ከማመስገንና ሥራውን ከማድነቅ በስተቀር ማማረርና ሌሎችም እንዲያማርሩት ምክንያት መሆን አልተፈቀደም። በዚህም ስሙን በከንቱ ከመጥራት መቆጠብ ይኖርብናል።

<u>መ/ ኑፋቄ</u>፦ ይህም የእግዚአብሔርን ክብር በማቃለልና መለኮታዊ ባሕርዩን ካለማወቅ የተነሣ በሚመጣ ትዕቢት ስሙን በከንቱ መጥራት ነው። ለምሳሌም– እንደ አርዮስና የዘመኑ ውሉደ አርዮስ የይሖዋ ምስክሮች ነን ባዮች ክርስቶስን ፍጡር /ሎቱ ስብሐት/ ማለት፣እንደ መቅዶንዮስና የዘመኑ መቅዶንዮሳውያን መንፈስ ቅዱስን ሕፁፅ /ሎቱ ስብሐት/ ማለት፣ እንደሉተርና የዘመኑ ሉተራውያንና መሰሎቻቸው ክርስቶስን አማላጅ /ሎቱ ስብሐት/ ማለት የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ ካለማወቅ፤ምሥጢረ ሥላሴንም ካለመጠንቀቅ የመጣ ከንቱ አምልኮ ነው። በዚህ መልክ ስሙን መጥራት በከንቱ ስመ አምላክን ከመጥራት የሚቆጠር ነውና ከዚህ ይሰውረን።

<u>ሠ/ጥንቆላና መሰሎቹ</u>፦ ልብን ለአጋንንት ሰጥቶ–ለዲያብሎስ ግብር ገብቶ በሰው ፊት ግን ስሙን በመጥራት ማታለል የዋሁን ሕዝብ ማሞኘት ነው። በእግዚአብሔር ስም የሚፈጸመውም ይህ ኃጢአት ስሙን በከንቱ መጥራት ነው። በራሳቸው ፍጡራን ወደሆኑትና በአጋንንት እየተገዙ ወደሚኖሩት ወደጠንቋዮችና መሰሎቻቸው ሁሉ በመሄድ አንዳች መፍትሔ የሚያገኙ የሚመስላቸው ሁሉ በስመ እግዚአብሔር ከለላ የሚፈጽም የዚህ ኃጢአት ተባባሪዎች



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ናቸው:: ስለሆነም በመጽሐፍ «...ሟርተኛም፣ሞራ ገላጭም፣ አስማተኛም፣ መተተኛም፣ በድግምት የሚጠነቁልም፣መናፍስትንም የሚጠራ፣ ጠንቋይም፣ ሙታን ሳቢም፣ ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው፤» እንደተባለ እያስታወስን በዚህ ተሳትፈን ስመ አምላክን በከንቱ ከመጥራት ልንቆጠብ ይገባል:: ዘዳ 18÷9–12::

ረ/ዘፈን:–አንዳንድ ዘፋኞችም በግጥሞቻቸው ውስጥ የእግዚአብሔርን ስም በመጨመር ተወዳጅነትን ያገኙ እየመሰላቸው የዘፈናቸው ማሻሻጫ ያደርጉታል:: የእግዚአብሔር ስም ግን ከክብሩ የተነሣ በመፍራት በመንቀጥቀጥ የሚጠራ እንጂ ለዘፈኛ አይደለም:: እነዚህን በመከተል አብረው የሚያቀነቅኑና የሚከተሉአቸውም ሁሉ የኃጢአታቸው ተባባሪ ናቸው:: ዘፋኝነት በራሱ ኃጢአትስለሆነ ኃጢአት በሆነ ዘፈን ቅዱሱን ስመ እግዚአብሔር መደባለቅ ደግሞ የከፋ ኃጢአት ነው:: ገላ5÷21:: የሚዘፍንም የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም ተብሏልና ከዚህ ራሳችንን ለማራቅ መጣር ይገባናል::

ሰ/ማስታወቂያዎች:– ብዙ ሰዎች በተለይ በከተማዎች አካባቢ ሱቆቻቸውን፣ ድርጅቶቻቸውንና የንግድቤቶቻቸውን በእግዚአብሔር ስም ይሰይማሉ:: ምናልባት ይህን ማድረጋቸው «የእግዚአብሔር ወዳጆች መሆናቸውን» ለማሳወቅ ወይም ደግሞ በንግዱ ብዙ ትርፍ እንዲያገኙ በማሰብ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሥራቸውን እንዲባርክላቸው ከመጸለይ በስተቀር በዚህ መንገድ ለመጠቀም መፈለጋቸው ትክክል ካለመሆኑም በላይ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ነው:: ለምሳሌ መድኃኔዓለም ሥጋ ቤት፣መድኃኔዓለም ጠጅ ቤት ክርስቶስ ብረታ ብረት፣አልፋና ዖሜጋ የቁንጅና ሳሎን ፣ወዘተ... የሚሉትን መመልከት ይቻላል:: በአብዛኛው ማስታወቂያው መንፈሳዊ ሁኖ በውስጥ የሚሠራው ሥራ ግን ሌላ ነው:: ዝሙቱ፣ስካሩ፣ማጭበርበሩ፣ውሸቱ ኑፋቄው አያድርስ ነው:: እንግዲህ ክርስቲያኖች ሁሉ ክርስትናችን በልቡና እምነትና በምግባር የሚገለጥ ሊሆን ከሚገባው በቀር በዚህ ዓይነት ተግባር እንዳይሆን መጠበቅ ያስፈልጋል:: ሌላው ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው ደግሞ የክርስቶስን ስም በተለያዩ አልባሳት ላይ በመጻፍና በማተም ለማስታወቂያ መጠቀም የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ከመጥራት ጋር የሚደመር ነው:: ስለሆነም ከዚህም መቆጠብ አለብን::

ሸ/መጠሪያ ስም:– አንዳንዶች ደግሞ የልጆቻቸውን ስም የሚሰይሙት ባለማስተዋልና በግድ የለሽነት ነው:: ሰው በእግዚአብሔር ስም ሊጠራ አይገባውም፣ የእግዚአብሔር ስም የእርሱ ብቻ ነውና:: ነገር ግን የልጆቻቸውን ስም ለምሳሌ አማኑኤል፣ ኤልሻዳይ፣ አዶናይ፣ ኢየሱስ ወዘተ... በማለት የሚሰይሙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ እየጠሩት ናቸው:: «አማኑኤል» ማለት የወልደ እግዚአብሔር የተዋሕዶ ስሙ ነው:– «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው:: የሚገልጠውም እግዚአብሔር ሰው የመሆኑን ምሥጢር ነው:: ታዲያ ይህ ስም ልንጠራበት ይገባናል? ፈጽሞ:: «ኤልሻዳይ» ማለት ሁሉን ማድረግ የሚችል ማለት ነው:: ይህም የእግዚአብሔርን ከሐሊነት የሚያመለክት ነው:: ማነው «ከሐሌ ኩሉ» በዚህ ስም ሊጠራ የሚደፍር? ማንም ከቶ ሊኖር አይገባም አዶናይም እንዲሁ:: ወልደ አማኑኤል /የአማኑኤል ልጅ/ ገብረ ኢየሱስ /የኢየሱስ አገልጋይ/፣ገብረ እግዚአብሔር /የእግዚአብሔር አገልጋይ/ እያሉ መሰየም ግን ስመ ክርስትና በመሆኑ ተገቢና የሚደገፍም ጭምር ነው:: እንግዲህ በስማችን ኃጢአት እንዳንሠራ፣ የእግዚአብሔርንም ስም በከንቱ እንዳናስጠራ መጠንቀቅ ተገቢ ነው::

ቀ/ ፍልስፍናና ሥነ ጽሑፍ:– አንዳንድ ፈላስፎች ነን ለማለት የሚቃጣቸው ሰዎች፣ ዐወቅን ተጠበብን፣ የሚሉበትን ፍልስፍናቸውን ተደማጭና ተቀባይነት ያለው ለማድረግ:– የሰሚን ወይም የአንባቢን ቀልብ ለመሳብ ሲሹ «እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎአል» እያሉ የእርሱን ሕያው ትምህርት ምውት ለሆነ ፍልስፍናቸው ይጠቀሙበታል:: ይህንኑ ፈሊጥ ብለውት በተራ ዲስኩራቸውና የፓለቲካ መነባንባቸው እንደቀልድ ስመ እግዚአብሔርን የሚጠሩ የእርሱንም ቃል የሚጠቅሱ ዘመነኞችም በየሬድዮው ይናገራሉ:: በየጋዜጣው ይጽፋሉ:: እነዚህም ሁሉ ስመ እግዚአብሔርን በከንቱ እየጠሩት ናቸው::

በሥነ ጽሑፍ ዓለም የምናውቃቸው አንዳንድ ደራሲያንና ገጣሚያንም የሚጽፉአቸው ድርሰቶችና ሥነ ጽሑፎች ጀሮ ገብና ተነባቢ እንዲሆንላቸው ከሚያውቋቸው መጻሕፍት የተቈነፀሉ ጥቅሶችን ከቃለ እግዚአብሔር ይጠቅሳሉ፣ስመ እግዚአብሐርንም ለማሾፊያና ለመሳለቂያ ሲጠቀሙበት ይስተዋላሉ:: ይህም ሁሉ እንግዲህ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ነውና ሳያስጠይቅ አይቀረም:: በራሱ ባሕርያዊ ውበትና ማራኪነት የሌለውን ደረቅና ባዶ ጽሑፍ በቃለ እግዚአብሔርና በስሙም ለማጣፈጥና ለማስዋብ መሞከር ስመ እግዚአብሔርን በከንቱ ከመጥራት የሚመደብ ነውና::

እስከዚህ ድረስ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ምን ማለት መሆኑን ተመልክተናል:: በመቀጠል ደግሞ ውጤቱ ምን እንደሆነ እንይ::

## የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ቅጣት አለው

ሰማይ ዙፋኑ፣ምድርም የእግሩ መረገጫ በመሆናቸው በሰማይም፣ በምድርም እንዳንምል የታዘዝን ከሆነ በእግዚአብሔር ስም መማል ደግሞ የበለጠ በመሆኑ የማይገባና ቅጣትም የሚያስከትል ነው:: በፍጥረቱ እንዳይምል የተከለከለ ሆኖ ሳለ በፈጣሪው በእግዚአብሔር ስም የሚምል ሰው የሚቀጣ መሆኑን መጻሕፍት ይናገራሉ:: ለምሳሌ «የእግዚአብሔርንም ስም የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል፤» በሚ ለው ምንባብ እንደተገለጠው ክብር ምሥጋና የሚገባውን ቅዱስ ስም በማይገባ ሥፍራ መጥራትና ልዕልናውን ዝቅ ማድረግ ስሙን በከንቱ መጥራትና እንደስድብም የሚቆጠር ነው::

በነቢዩ በሕዝቅኤል «እግዚአብሔር ስለ ቅዱስ ስሙ ይቀናል» የተባለውም የፈጣሪአችንን ስሙ በከንቱ እንዳንጠራ የሚያስተምር ነው::ሕዝ 39÷25:: እግዚአብሔርም «ወደመጡባቸውም ወደ አሕዛብ በመጡ ጊዜ ቅዱስ ስሜን አረከሱ፤ እኔ ግን የእሥራ ኤል ቤት በመጡባቸው በአሕዛብ መካከል ስለአረከሱት ስለ ቅዱስ ስሜ ስለራራሁላቸው፤... በአሕዛብ መካከል ስለአረከሱት ስለ ቅዱስ ስሜ ነው» በማለት ስለ እሥራኤል ልጆች የተናገረው ለዚህ ነው:: ሕዝ 36÷20:: የእግዚአብሔርን ስም ማርከስ ማለትም ሊሰጠው የሚገባውን ክብር መንሳትና ማቃለል ነው:: ከዚህ መራቅና ስሙን በከንቱ ጠርቶ ከመከሰስ ለመዳን ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልጋል:: በነቢዩ በዘካርያስም «በሐሰት የሚምል ሁሉ ይጠፋል፣ ...እኔ አስወጣዋለሁ» ያለው የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የሚጠሩ ሁሉ የሚቀጡ፤ ቅጣቱም ከገጸ ምድር የሚያጠፋ መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: ዘካ 5÷3:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ እኛ ይህን ስም እንዴት እንደምንጠራው ራሳችንን ልንመረምርና የእግዚአብሔርን ስም በተገቢው ክብር መጥራትን ልንለ ምድ ያስፈልጋል::

ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር «ለስሜ ክብርን ትሰጡ ዘንድ ባትሰሙ፤ በልባችሁም ባታደርጉት እርግማን እሰድባችኋለሁ:– በረከታችሁንም እረግማታለሁ» በማለት አስጠንቅቋል:: ሚል2÷2:: ይህም የእግዚአብሔር ስም ክቡርና ገናና በመሆኑ በከንቱ የሚጠራውን ሰው እግዚአብሔር እንደሚቀጣው የሚያመለክት ነው:: ስለዚህ ስሙን በማክበር የሚገኘውን በረከት እንዳናጣና እንዳንቀጣ እንዳንጠፋም፤ በጊዜው ሁሉ የእርሱን ስም በማክበር እንኑር:: በዚህ ጸንተን ክብሩን ለመውረስ እንዲያበቃን የልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን:: አሜን

ወለእግዚአብሔር ስብሐት





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## እግዚአብሔር ዐይንና ጆሮ አለው?

*ጥያቄ፦* «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በእውነትና በመንፈስ ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።» ይላል ዮሐ 4፥24። ታዲያ እግዚአብሔር እንዴት አካል ማለትም ዓይን፣ ጆሮ፣ እጅ፣ እግር አፍንጫ ወዘተ… አለው። ይባላል?

*/እኅተ ዮሐንስ/ ከአሜሪካ*

*መልስ፦* ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲካር ወደምትባል የሰማርያ ከተማ በመጣ ጊዜ አንዲት ሳምራዊት ሴት ውኃ ለመቅዳት መጣች በዚያ የያዕቆብ ጉድጓድ ነበረ። ሳምራውያንም በአይሁድ ዘንድ እጅግ የተናቁ ነበሩ። ይሁን እንጂ ጌታችን አነጋገራት፤ እርሷም በጣም ገረማት።

ጌታችን ለዚህች ሴት ስለ ሕይወት ውኃ አስተማራት። ይኸንን የሕይወት ውኃ ስጠኝ ብላ በለመነችውም ጊዜ «ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ነይ፤» አላት። እርሷ ግን ባል የለኝም አለችው። ጌታችንም «ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤ አምስት ባሎች ነበሩሽና አሁን ከአንቺ ጋር ያለውም ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ።» አላት

ሳምራዊቷ ሴት ምሥጢሯን ስለነገራት ተደነቀችና «አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ አባቶቻችን በዚህ ተራራ /በሞርያ ተራራ/ ሰገዱ፤ እናንተም ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ።» አለችው። ጌታችንም «አንቺ ሴት እመኚ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አላት። ይህም «ስግደቱ በዚህ ብቻ ተወስኖ አይቀርም፤ በአራቱም ማዕዘን ይሰገድለታል» ማለት ነው። ቀጥሎም «እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን።» አላት ይህም እርሱ መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ከነገደ ይሁዳ በመወለዱ ነው። በመጨረሻም ይኸንን የመሳሰሉ ሌሎች ነገሮችንም ካስተማራት በኋላ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።» ብሏታል።

«እግዚአብሔር መንፈስ ነው።» ማለቱ ረቂቅ ስለሆነ እንጂ አካል ስለሌለው አይደለም። ምክንያቱም መለኮታዊ አካል ረቂቅ፣ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ፣እሳታዊ እና ምሉዕ ነውና። «በመንፈስ ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።» የሚለው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ልጆች ሁነው አንድም በአብራከ ነፍስ ሁነው በንጽሕ ጠባይ ጸንተው ሊሰግዱለት ይገባል ማለት ነው።

ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔር ዓይኖች፡ጆሮዎች እና ፊት ማለትም አካል እንዳለው ሲገልጥ «የእግዚአብሔር ዓይኖቹ ወደ ጻድቃን ጆሮቹም ወደ ጩኸታቸው ነው። የእግዚአብሔር ፊት ክፉን በሚያደርጉት ላይ ነው።» ብሏል። መዝ 33፥15። እጆችና እግሮች እንዳሉትም «እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም» መዝ118፥73። «አምላካችን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርጉት ቅዱስ ነውና ወደ እግሩ መረገጫ ስገዱ» መዝ 98፥5። ብሏል። እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎችም ጥቅሶች አሉ። ለመልስ ያህል ግን ይኸው ይበቃል። በመጨረሻም ልናስተውለው የሚገባን ነገር ቢኖር መለኮታዊ አካል እንደ ሥጋዊ አካልውሱን አለመሆኑን ነው። ለምሳሌ ዓይን አለው ስንል ያያል ጆሮ አለው ስን ልም ይሰማል ማለታችን ነው።

## ካልቆረቡ ማስቀደስ አይቻልም?

*ጥያቄ፦* «እመቦ ብእሲ እምእመናን ዘቦአ ቤተክርስቲያን፣ በጊዜ ቅዳሴ ወኢሰምዓ መጻሕፍተ ቅዱሳት ወኢተአገሠ እስከ ይፌጽሙ ጸሎተ ቅዳሴ፤ ወኢተመጠወ እምቁርባን ይሰደድ እምቤተ ክርስቲያን፤ እስመ አማሰነ ሕገ እግዚአብሔር ወአስተሀቀረ ቁመተ ቅድመ ንጉሥ ሰማያዊ ንጉሠ ሥጋ ወመንፈስ፣ ከመዝ መሐሩነ ሐዋርያት በአብጠሊሶሙ» «በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር ቅዱሳት መጻሕፍትን የማይሰማ፣ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ድረስ ባይታገስ፣ ከቁርባንም ባይቀበል ከቤተክርስቲያን ይለይ። የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፣ የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምን አቃሏልና፤ ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንዲህ አስተማሩን» የሚለውን እየጠቀሱ ካልቆረባችሁ በቀር አታስቀድሱ እያሉ የሚያስተምሩ አሉና እናንተስ ምን ትላላችሁ?

*/ዲ.ወንድወሰን ሦርሳ ከወላይታ ሶዶ/*

*<u>መልስ፦</u>* በቅዳሴ ጊዜ የምንቆመው በእግዚአብሔር ፊት ነው። «አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ፤» እያልን በአንድነት እና በሦስት የምናመሰግነውም እግዚአብሔርን ነው። በቅዳሴው ላይ የሚነበበው የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን የምንቆርበውም ቁርባን የጌታችን ሥጋና ደም ነው። በመሆኑም የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥጢር እና የቅዱስ ቁርባንን ክብር በማቃለል የቅዳሴው ጸሎት ሳይፈጸም መውጣት እግዚአብሔርን መድፈር ነው። ይህም «የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፤ የነፍስና የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምን አቃሏልና፡» በሚለው ቃል ተገልጧል። ከዚህም የምንረዳው ቃሉ የተነገረው ቅዳሴውን እንደ ተርታ ነገር በመቁጠር አቋርጠው ለሚወጡ ሰዎች መሆኑን ነው።እንዲያውም «እትው በሰላም፣ ወደየቤታችሁ በሰላም ግቡ።» ሳይባል ቅዳሴውን አቋርጦ መሄድ ይሁዳን መሆን ነው። ይሁዳ ጌታው ሳያሰናብተው ወጥቶ ሄዷልና። ከላይ በዝርዝር ለመመልከት እንደሞከርነው «ከቤተክርስቲያን ተወግዞ ይለይ።» የተባለው የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥጢር፣ የቅዳሴን ክብር እና የቅዱስ ቅርባንን ሕይወትነት ለማያምን ሰው ነው። ውግዘቱም ከምእመናን ወገን ለነበሩ ኋላ ግን ወደ መናፍቅነት ለተሳቡ ለከሃድያን እንጂ ቃሉን አምነው ቅዳሴውን አክብረውና የቅዱስ ቁርባንን ሕይወትነት ዐውቀው በትህትና ደጅ ለሚጠኑ ምእመናን አይደለም።

ነገር ግን ምሥጢሩን አዛብተው «ይህ የተነገረው ለምእምናን ስለ ሆነ የማትቆርቡ ከሆነ አታስቀድሱ።» እያሉ የሚያስተምሩት ሰዎች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ካባ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የለበሱ መናፍቃን ናቸው፡፡ ምእመናንን ዛሬ ከሥርዓታቸው ነገ ደግሞ ከሃይማኖታቸው ለመለየት በበጎች መካከል ያደቡ ተኩላዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም ቃሉ የተነገረው የሚፈተተው ሥጋና ደም «አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው፡፡» ብለው አምነው ለማይቀበሉ መናፍቃን መሆኑን ዐውቀን ከሐሰተኞች መምህራን መጠበቅ አለብን፡፡ ምእመናንማ ዛሬ ባይቀበሉ ነገ ተነገወዲያ ንስሐ ገብተው ይቀበላሉ፡፡ እስከዚያ ግን «ዕድሜ ለንስሐ አትንፈገን ለሥጋህ ለደምህ አብቃን፡፡» እያሉ በጸሎተ ቅዳሴ ደጅ ይጠናሉ፡፡ ለንስሐ የተሰጣቸውንም ቀኖና እስኪጨርሱ ድረስ አይቀበሉም፡፡ በቅዳሴ ላይ ዲያቆኑ «በንስሐ ውስጥ ያላችሁ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ፡፡» የሚለውም ለዚህ ነው፡፡ በቅዳሴ ጊዜ የሚቆርቡና የማይቆርቡ ምእመናን ቁመው ማስቀደስ ይገባቸዋል፡፡ የተቻለው ሲቆርብ ያልተቻለው ቁሞ ማስቀደስ ይገባል ሲባል የቆረበው በሐዋርያት ይመሰላል፣ሳይቆርብ አስቀድሶ የሚወጣው ደግሞ በቅፍርናሆሙ መቶ አለቃ ይመሰላል ይህ ሰው ግን ልጁ ታሞበት አድንልኝ በማለት ወደ ጌታችን መጣ፡፡ ጌታም «እነሆ መጥቼ አድንልሃለሁ» ቢለው «ጌታ ሆይ ከቤቴ ጣራ በታች ትገባ ዘንድ አይገባኝም፡፡ ከዚህ ሳለህ በቃልህ እዘዝና ልጄ ይድናል፡፡» አለው፡፡ በዚህን ጊዜ ጌታችን «ከእስራኤል ወገን እንደዚህ ያለ እምነት ያለው ሰው አላገኘሁም፡፡» ሲል የሃይማኖቱን ጽኑነት መሰከረለት፡፡ ስለሆነም የመቶ አለቃው በማመኑ እንደተጠቀመ ሁሉ ቆሞ የሚያስቀድስ ካልተቻለው ባይቆርብም ኃጢአቱን እያሰበ ቆሞ ካስቀደሰ አለመቻሉንና ትሕትናውን አይቶ ወደፊት ለቁርባን ያበቃዋልና ሳልቆርብ ቆሜ ባስቀድስ አልጠቀምበትም ብሎ አለማስቀደስ አይገባም፡፡

## ትርጓሜያቸው ምንድን ነው?

__ጥያቄ__፦ በቤተክርስቲያን መጻሕፍት ላይ ሚጠት፣ ውላጤ፣ ቱሳሔ፣ ትድምርት የሚሉ ቃላት አሉ፡፡ ለመሆኑ ትርጓሜያቸው ምንድነው?

/ተክለወልድ ከአ.አ/

__መልስ__፦ ሚጠት ማለት መመለስ ማለት ነው፡፡ ይህም እንደ በትረ ሙሴ እንደ ማየ ግብፅ ነው፡፡ በትረ ሙሴ ፊት በትር ነበረች፤ ቢጥላት ዕባብ ሆነች፣ መልሶ ቢያነሣት ደግሞ ተመልሳ በትር ሆነች፡፡ ማየ ግብፅም ቀድሞ ውኃ ነበር፣ ኋላ ደም ሆነ እንደገናም ውኃ ወደመሆን ተመለሰ፡፡ ዘፀ4÷1–5፣ 7÷20–25 በምሥጢረ ተዋሕዶ ግን ሰው የሆነ እግዚአብሔር አምላክ ከጊዜ በኋላ ወደ አምላክነቱ ተመለሰ አይባልም፡፡ ምክንያቱም በተዋሕዶ ሰው የሆነው አምላክነቱን ለቅቆ አይደለምና፡፡

__ውላጤ__፦ ማለት መለወጥ ማለት ነው፡፡ ይህም እንደ ሎጥ ሚስት እንደ ማየ ቃና ነው፡፡ የሎጥ ሚስት ፊት ሰው ነበረች ኋላ የጨው ሐውልት ሆነች፤ ማየ ቃናም ቀድሞ ውኃ ነበር፣ ኋላ ወይን ሆነ፡፡ ዘፍ 19÷26፣ዮሐ2÷7–9፡፡

በምሥጢረ ተዋሕዶ ግን «ቃልም ሥጋ ሆነ፤» ዮሐ 1÷14፡፡ ሲል መለኮት አምላክነቱን ለቅቆ ተለውጦ ሰው ሆነ አይባልም፡፡ ምክንያቱም በተዋሕዶ ጊዜ መለኮት አልተለወጠምና ፡፡

__ቱሳሔ__፦ ማለት ቅልቅል ማለት ነው፡፡ ይህም እንደ ማር እና እንደ ውኃ ነው፡፡ ማርና ውኃ ቢቀላቀሉ ስም ማእከላዊ፣ መልክ ማእከላዊ እና ጣዕም ማእከላዊ ይገኝባቸዋል፡፡ __ስም ማእከላዊ__፦ የዕለቱ ብርዝ የሰነበተው ጠጅ ይባላል፡፡ __መልክ ማእከላዊ__፦ እንደ ማር ሳይነጣ እንደ ውኃ ሳይጠቁር መካከለኛ መልክ ይይዛል፡፡ __ጣዕም ማእከላዊ__፦ እንደ ማር ሳይከብድ እንደ ውኃም ሳይቀል መካከለኛ ጣዕም ይኖረዋል፡፡ ወተትና ቡናም ሲቀላቀል እንዲሁ ነው፡፡ እንደ ወተት አይነጣም እንደ ቡናም አይጠቁርም፡፡

በምሥጢረ ተዋሕዶ ግን መለኮትና ሥጋ እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ ተዋሕዱ እንጂ ተቀላቀሉ አይባልም፡፡

__ትድምርት__ ማለት መደረብ መደመር ማለት ነው፡፡ ይህም እንደ ልብስ እና እንደ እንጀራ ማለት ነው፡፡ ልብስ ቢደርቡት ይደረባል፣ ቢነጥሉት ይነጣላል፤ እንጀራም ቢደርቡት ይደረባል፣ ሲነጥሉት ደግሞ ይነጠላል፡፡

የመለኮት ሥጋን መዋሐድ ግን እንደዚህ አይደለም፤ በማይመረመር ምሥጢረ ተዋሕዶ ከሁለት አካል አንድ አካል፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆን አምላክ ሰው፣ ሰው አምላክ ሆነ ማለት ነው፡፡

## ጥምቀት ያለሜሮን ይቻላል?

__ጥያቄ__፦ በአንዳንድ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በተለያዩ ምክንያቶች ምሥጢረ ሜሮን ለተጠመቁ ሕፃናት አይፈጸምም፡፡ ታዲያ ይህ ምሥጢር ያልተፈጸመለት ሰው በክርስትናው ላይ የሚያመጣው ጉድለት አለ? /መምህር ዘመኑ አበራ–ከሰሜን ሸዋ/

__መልስ__ ምሥጢረ ሜሮን ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ ነው፡፡ ምሥጢረ ሜሮን ከጥምቀት በኋላ የምንቀባው ቅዱስ ዘይት ነው፡፡ ቤተክርስቲያናችን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁትን ጥሙቃን የምታከብራቸው በቅብዓ ሜሮን ነው ይህም ስለ አንብሮተ ዕድ ፈንታ የሚፈጸም ነው፡፡ ጥንት ቅዱሳን ሐዋርያት ይህንን ምሥጢረ ቤተክርስቲያን የሚፈጽሙት እጅን በመጫን ነበር፡፡ የሐዋ 8÷14–17፡፡፣19÷5–6፡፡ ክርስትና እየተስፋፋ፣ ሃይማኖት እየሰፋ በሄደ ጊዜ ግን ጳጳሳቱ በየቦታው እየሄዱ እጅን በመጫን ማዳረስ ስለማይችሉ ይህ ሥርዓት በአንብሮተ ዕድ ፈንታ ተተክቷል፡፡

ምሥጢረ ሜሮን ተጠማቂው በጥምቀት የተሰጠውን ልጅነት ለማጽናት የሚችልና የመንፈስ ቅዱስን ልዩ ስጦታ የሚያገኝበት ምሥጢር ነው፡፡ ይኽንን በተመለከተ ቅዱስ ዮሐንስ «እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል ሁሉንም ታውቃላችሁ፡፡» ብሏል፡፡ 1ኛ ዮሐ 2÷20፡፡

ይህ ቅዱስ ዘይት ከወይራ ዘይትና ለዘይቱ ከሚሆኑ እውነተኛ እንጨቶች ይሠራና በፓትርያርኩና በጳጳሳቱ ጸሎት ተጸልዮበት ይባረካል፡፡ የተጀመረውም በዘመነ ሐዋርያት ነው፡፡ በዚህ ምሥጢረ ቤተክርስቲያን ለተጠማቂው ሰባት ስጦታዎች ይሰጡታል፡፡ 1ኛ ጥበብ 2ኛ ልብ ማድረግ 3ኛ ምክር 4ኛ ኃይል 5ኛ ዕውቀት 6ኛ አምልኮተ እግዚአብሔር 7ኛ ፈሪሃ እግዚአብሔር ናቸው፡፡ ስለሆነም ከጥምቀት በኋላ ቅብዓ ሜሮን አለመቀባት ትልቅ ስሕተት ነው፡፡ ምእመናን ግን እንደ እምነታቸው ይደረግላቸዋል፡፡

## ንስሐ

ትከሻ ሸክም ወረደለት
አንገትም ቀንበር ቀረለት
ሽፋሎች ዕንቅልፍ አገኙ
ልብም ሐሳቡ ሄደለት
ጥርስም አይነክስ ከንፈሩን
ሕሊናም ወቀሳን ሸኘ
ግራዬም ለቀኝ ተገዛ
ነፍሴም ሰላም አገኘ፡፡

ወለተ ሥላሴ/አ.አ/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቴአትር

ባለፉት ሁለት ተከታታይ እትሞቻችን ግጥምንና ልቦለድን ከቤተክርስቲያናችን ሥርዓትና ትውፊት አንጻር ምን መምሰል እንዳለባቸው ለማየት ሞክረናል:: በዚህ እትም ደግሞ ወደ ቴአትር ጥበብ እናመራለን::

ቴአትር:- የተዋንያኑን ንግግር፣ መብራት፣ መጋረጃ፣ የመድረክ ሥዕል፣ ዜማ ወዘተ... አጠቃልሎ የሚይዘው ጥበብ መጠሪያ ሲሆን ድራማ ደግሞ ሥራው ያለቀለት ለእይታ የቀረበው የውጤቱ ስያሜ ነው::

ዘመናዊ የቴአትር ጥበብ ወደ ሀገራችን ከገባ ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ አልሆነውም:: ከሰንበት ት/ቤቶቻችን ጋር ያለው ግንኙነት ግን ከዕድሜያቸው አንጻር የረዥም ጊዜ ትውውቅ ነው ለማለት ይቻላል:: በአንዳንድ የሰ/ት/ቤቶች የዛሬ 20 እና 25 ዓመት የተሠሩ ድራማዎችን ለማየት ችለናል:: ይህም የቴአትር ጥበብ በሰንበት ት/ቤቶች መታየት የጀመረው ገና ከምሥረታው መሆኑን ሊጠቁም ይችላል::

ለዚህ እንደዋና ምክንያት ሊቀርብ የሚችለው አብዛኞቹ የሰ/ት/ቤት አባላት «የተማረው ክፍል» ከሚባለው ወገን መሆናቸው ነው:: በኢትዮጵያ የቴአትር ጥበብ የተወጠነው በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነው:: የሰ/ት/ቤቶቻችን አባላትም በብዛት የተገኙት ደግሞ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመሆኑ ይህን ጥበብ ወደሰንበት ት/ቤት በቀላሉ ለማምጣት ጊዜ አልፈጀባቸውም::

የቴአትርን ጥበብ የተሳካ የሚያደርጉት ቢያንስ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ሲሟሉለት መሆኑን ባለሙያዎች ይናገራሉ::

## ሀ- ተውኔት

የቴአትሩ መነሻ ሐሳብ፣ ንግግሩ፣ ታሪኩና አካባቢው የተቀረጸበት ድርሰት ተውኔት ይባላል:: ይህ የቴአትር ሁሉ መነሻ ነው:: ባለፉት እትሞቻችን አንድ ኦርቶዶክሳዊ ሥነ ጽሑፍ ሊያሟላቸው የሚገባቸው መስፈርቶች እዚህም ላይ ይደገማሉ::

ደራሲው ቴአትሩን ሲጽፍ ከኦርቶዶክሳዊነት አንጻር ሊያስተውላቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉት:: ቋንቋው የቤተክርስቲያን ነውን? ይዘቱ /ጭብጡ/ ከቤተክርስቲያን ትምህርት ያልወጣ ነውን? ይህ ቴአትር በመድረክ መቅረብ አለበትን? ወዘተ...::

በአንዳንድ ሰ/ት/ቤቶች ከነዚህ ጥያቄዎች አንጻር የሚስተዋሉ ችግሮች አሉ:: በልዩ ልዩ ቴአትሮች ላይ የተመለከቱትን በቋንቋ የመፈላሰፍ ብሂል ለመድገም ሲባል ተውኔቱ ኦርቶዶክሳዊ ለዛውን ለቆ ፍጹም ዓለማዊ የሚሆንበት ጊዜ ያጋጥማል:: ይህም ብቻ አይደለም «ሁሉን ነገር ማሳየት» የሚል የአንዳንድ ጸሐፍትን ፍልስፍና በመያዝ መታየት የማይገባውን ለማሳየት ሲሞከርም ተስተውሏል:: ለምሳሌ በአንድ ተውኔት ላይ «እመቤታችን ለመውለድ ስታምጥ»፣ በሌላ ተውኔት ደግሞ «ከኤልሳቤጥ ጋር ሲጐራረሱ»፣አንዱ ደግሞ «ካህኑ ቁርባን በሰው ፊት ሲፈትት» ወዘተ... የታየበት ወቅት ነበረ:: የመጀመሪያው አባባል የእመቤታችንን ማንነት ያላወቀ ሰው የጻፈው ካልሆነ በቀር እመቤታችን ጌታን ለመውለድ ፈጽሞ አላማጠችም:: ሁለተኛው ደግሞ ለሕዝቡ ምንም መልእክት የማያስተላልፍ ነገር አሳይቶ የእመቤታችንን ክብር «ዝቅ» ከማድረግ ውጭ የሚሰጠው አንዳች ፋይዳ የለም:: ሦስተኛውም የምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን አፈጻጸም ካለማወቅ የመነጨ ነው:: እመቤታችንን እና ጌታችንን ወክሎ በቴአትር ላይ መሥራትም የፈጣሪንና ሁሉን የያዘ አምላክን የወለደች እመቤት በሰዎች አእምሮ ውስጥ ያለውን ክብር ስለሚቀንስ በድምጽና በትረካ ብቻ መታለፍ አለባቸው::

በመሆኑም ጸሐፊ ተውኔቱ ችሎታው ስላለው፣ወይንም ደግሞ የቴአትር ጥበብ ሥልጠናን ስለወሰደ ብቻ መንፈሳዊ መልእክት ያለው ቴአትር ማዘጋጀት እንደማይችል መታወቅ አለበት:: የቤተክርስቲያንን ትምህርት፣ ሥርዓትና ትውፊትም ዘልቆ፣ጠልቆ ማወቅንም ይጠይቃል:: ዛሬ ዛሬ እርሱ /ሷ/ አማተር ነው /ናት/መባል ብቻ ብቁ ያደርጋል ተብሎም ይታሰብ ተጀምሯልና ::

# ኦርቶዶክሳዊ

አንዳንድ ጊዜ የዘመኑ ፍልስፍና ተጠቂ ከመሆን የተነሣ «ጭብጥ» አልባ ቴአትር ሲቀርብም ይስተዋላል:: በአንድ ከተማ አንድ ቴአትር በሰ/ት/ቤት አባላት ተዘጋጅቶ ነበር:: ልጅቱ ሃይማኖቷን ትታ መናፍቅ ሆነች፣ማተብ በጠሰች፣የማይገባ ነገር ሁሉ አደረገች:: ወላጆቿ ተጨነቁ፣ተጠበቡ:: በድራማው መጨረሻ ግን ልጅቱ መናፍቅ እንደሆነች ወላጆቿም እንደተጨነቁ ቀሩ:: ይህ እንግዲህ ለአንድ ኦርቶዶክሳዊ ተመልካች ምንም መልእክት የሌለው አየር ላይ የቀረ ድራማ ነው:: በዚያ ወቅት አንድ አባት «ታዲያ ምን አስተማራችሁን?» ነበር ያሉት:: ይህ እንግዲህ ማሳየት /to reflect/ የሚለውን ፍልስፍና ከመከተል የመነጨ ነው::

ሌላው ችግር ያላስፈላጊ ትዕይንቶች ጉዳይ ነው:: ሰዎች መጠጥ ቤት ሲገቡ፣ ሲጨፍሩ፣ ጫት ሲቅሙ፣ ሲጋራ ሲያጤሱ፣ ዕብድ ዘባተሎውን ለብሶ ሲለፈልፍ፣ ባለዛሮች መድረኩን ሞልተው ሲያጓሩ፣ ወዘተ... የሚታይባቸው ክፍሎች በዝተው ረዝመው ሲያሰለቹ፤ ብሎም ተመልካቹ መልእክቱንና ማንነቱን ረስቶ ዓለማዊ ስሜቱ እስኪቀሰቀስበት ደምቀው ሲታዩ ይስተዋላል:: እነዚህ ነገሮች በቴአትር ውስጥ ካሉ በመድረክ ሥዕል፣ በመብራት ፣ በትረካ፣ በትውስታ፣ በንግግር ወዘተ... መግለጹ ይመረጣል:: ያለበለዚያ ግን ተመልካቹን ወደ አላስፈላጊ ትምህርት መምራታቸው አይቀሬ ነው::

የቴአትሮች መርዘምና መንዛዛትም አንዱ ችግር ነው:: መጋረጃ በመክፈትና በመዝጋት፣ ዕቃ በማጓጓዝ፣ በመድረክ ላይ ወጥቶ ሲናገሩ በመዋል መቅረት የሚችለውን ነገር ሁሉ ሰብስቦ በማስገባት የአራት ሰዓት መንገድ በመድረክ ላይ የሚጓዙ፣ ምሳቸውን እያስጨመሩ የሚበሉ፣ተኝተው ከቅዠት-ሕልም የሚያዩ-የሰ/ት/ቤት ፕሮግራም እያሳየን ነው ብለው እንዳለ ፕሮግራሙን የሚያቀርቡ፣ ወዘተ...አጋጥመውናል:: በሰ/ት/ቤት የሚቀርብ ድራማ እጥር፣ ምጥን፣ ቅልብጭ ያለ ቢሆን የተሻለ ነው::





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሥነ ጽሑፍ

ያለበለዚያ ዓላማውን ይስትና መል
እክቱ ይረሳል:: ተመልካቹን ያልመ
ጠነ ቴአትሯም ትምህርት ከማስተላ
ለፍ ይልቅ አደናጋሪነቱ የባሰ ነው::

ድራማ ማለት ማሳቅ ማለት
ነው ብለው የሚያስቡም ያጋጥ
ማሉ:: በሁሉም ነገር ውስጥ ለማሳቅ
ይፈልጋሉ:: በቅዳሴ ጊዜ፣በጸሎት
ሰዓት፣በትምህርት ወቅት፣ሰማዕታት
መከራን ሲቀበሉ፣ ወዘተ...ያስቃሉ::
ይህ ግን ቤተክርስቲያንን ካለማወቅ
የመነጨ ነው:: በቤተክርስቲያናችን
ሳቅ ስላቅ–ዋዛ ፈዛዛ ስፍራ የለ
ውም:: ተመልካቹ ነገሩ እንዳያስለ
ቸው፣ የተያዘ ስሜቱ ለቀቅ እንዲል
ጣል ከሚደረግ ነገር በቀር ድራማ
ውን ሁሉ በሳቅ በጨዋታ መጨረሱ
ሰውን ከማዝናናት በቀር የሚያበረ
ክተው መንፈሳዊ ጥቅም የለም::
እንድያውም በሰ/ት/ቤቶቻችን የሚ
ቀርቡ ተውኔቶች በተቻለ መጠን
«ቁም ነገር ላይ» ያተኮሩ ሊሆኑ
ይገባል:: ሌላው የትም ይገኛልና::

ለ ተዋንያን

ተዋንያን ተውኔቱን በመድ
ረኩ የሚያቀርቡት ሰዎች ናቸው::
አንድን ነገር መስለው ወይም ወክ
ለው ይቀርባሉ:: በተዋናይ ምርጫ
ጊዜ በሰ/ት/ቤቶቻችን ሊደረግ የሚ
ገባው ጥንቃቄ አለ::

ድራማ ከሌሎች የሥነ
ጽሑፍ ዘርፎች ይልቅ ብዙ ሰው
ስለሚያሳትፍና ለብዙዎችም በመድ
ረክ ላይ ታይቶ የመታወቅ ዕድል
ስለሚሰጥ በርከት ያሉ ወጣቶች
መሳተፉን ይወዱታል:: እንዲያውም
የሰ/ት/ቤት አባል መሆን ለድራማ
ተዋናይነት መብቃት ነው የተባለ
ይመስል አባል ሆኖ ድራማ
ያልሠራ ሰው በጣት ተቆጥሮ የማይ
ገኝባቸው ቦታዎችም አሉ:: ወደ
ሰ/ት/ቤቶችም ድራማ ሲኖር ብቻ
ብቅ የሚሉ አያሌ ናቸው::

ታዲያ ብርቱ ጥንቃቄ
መደረግ ያለበት ለዚህ ነው:: አንድ
ሰው በሰ/ት/ቤቶች የሚቀርቡ ተውኔ
ቶችን ለመሥራት ቢቻል የሚከተ
ሉትን ነጥቦች ቢያሟላ ይመረጣል::

*1. ችሎታ፡–* የተመደበበትን ክፍል
/ገጸ ባሕርይ /ወክሎ ለመሥራት
ችሎታው ምን ያህል ነው?
በአካል፣ በንግግር፣ በአለባበስ
ወዘተ... ይመስለዋል ወይ?

*2. ጠባይ–* በክርስቲያናዊ ኑሮው
ለሌሎች አርአያ የሚሆን፣ ራሱን
የማያሳጣ፣ በሠራው ሥራ ትዕቢት
የማይዘው፣ለድራማ ሲል ወደ ሰ/ት/
ቤት ያልመጣ፣ ወዘተ... የአብዛኞቹ
ችግር የሚመነጨው እዚህ ላይ
ነው:: ችሎታ አለው፣ አላት ተብሎ
የገቡ ተዋንያን በመድረክ ላይ
ሕዝብ ዐይቷቸው፣ ፀሐይ ሞቋቸው
ከመድረክ ሲወርዱ ግን የሰ/ት/ቤት
አባል ቀርቶ አንድ ዓለማዊ ሰው
እንኳን የማይሠራውን የሥነ ምግባር
ጉድለት ሲፈጽሙ ከታዩ ሕዝቡ
ስለሰ/ት/ቤትና ስለ መንፈሳዊ ሰው
ያለው አመለካከት ይቀየራል::

አንዳንድ ሥልጠናዎችን
ስለወሰደ ብቻ «ድራማ ሥራልን፣
ድራማ ሥሪልን» እያልን የምንጋብ
ዛቸው ሰዎችም ትክክለኛ የሰ/ት/
ቤታችን አባላትና በሥነ ምግባራ
ቸው የታወቁ፣ ከራሳቸው አልፈው
ለሌላው ጥሩ አርአያ የሚሆኑ ካል
ሆኑ በቀር፤ ነገ ከሰ/ት/ቤት አልፈው
ቤተክርስቲያንን ማስነቀፋቸው አይ
ቀርም:: ከዚያም በላይ ደግሞ በማ
ያውቁት ሕይወት ገብተው በራሳ
ቸው ሥጋዊ ስሜት ሰ/ት/ቤቱን
ልምራው ማለታቸው አይቀሬ ነው::
መንፈሳዊ የሆነ ሥራ ከሚበላሽባ
ቸው ምክንያቶች አንዱ በዓለማዊ
ሰው ሲሠራና ሲመራ መሆኑ መዘን
ጋት የለበትም:: /1ጢሞ 3÷6::

በአንድ ሰንበት ት/ቤት
ቴአትር ይሠራ የነበር አንድ ወጣት
እንደዘመነኞቹ ጸጉሩን አስረዝሞ፣
የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍን ወክሎ
ሲሠራ ተመለከትኩና ከቴአትሩ
ፍጻሜ በኋላ«ለምን ጸጉርህን አትቆ
ረጠውም? አንተኮ የኦርቶዶክሳዊት
ተዋሕዶ ልጅ ነህ» ብየ ጠየቅሁት::
እርሱ ግን «በሚቀጥለው ሳምንት
ጃማይካ ስለምሄድ አልቆረጠውም::
ዛሬ ቴአትር የሠራሁትም ሰው የለ
ንም ብለው ስለጋበዙኝ ነው፤» ያለ
ኝን አልረሳውም::

በሃይማኖት ካለመብሰል
የሚመጣ ሌላም ችግር አለ::
ሰ/ት/ቤትን–የቴአትር መድረክ አድ
ርጐ ማየት:: ቴአትር ከሌለ ፕሮግ
ራም የሌለ፣ስብከት ያልቀረበ፣
ሕዝቡ ያልተማረ፣ ሥራ ያልተ
ሠራ፣ አባላት የቀነሱ፣ ወዘተ...
አድርገው የሚያዩ ተዋንያን አያሌ
ናቸው:: እነዚህ አባላት ቴአትር
ከሌለ ወይ አይመጡም ያለበለ
ዚያም አይደሰቱም፤ ትምህርተ
ወንጌል፣ መዝሙር፣ እንደው በጠ
ቅላላው አንድ ቦታ ረግተው የሚ
ማሩት ትምህርት አይጥማቸውም::
በዚህም የተነሣ መምህሩ መጽሐፍ
ገልጦ፣ ስመ እግዚአብሔር ጠርቶ
እያስተማረ፤ ሲወጡ፣ ሲገቡ፣
ሲነሡ፣ ሲቀመጡ፣ ሲያፈጡ፣ ሲቁ
ነጠነጡ፣ አጠገባቸው ካለው ጋር
ሲያወሩ፣ በየደቂቃው ሲያዛጉ ይስ
ተዋላሉ:: ትልቁ መለያቸውም
ቢሞቱ ማስታወሻ ደብተር አለመያ
ዛቸው ነው::

ቴአትር ከመሥራት ውጭ
ጽድቅ ያለ የማይመስለው «ተዋ
ናይ» አጋጣሚ ሆኖ በቴአትር
ውስጥ ቦታ ካልተሰጠው አንድም
ያኮርፋል፤ አለያም ሰ/ት/ቤቱን ጥሎ
ይሄዳል:: ምክንያቱም እርሱ ያልጋ
ገረው እንጀራ ይስቀሰቃል፣ እርሱ
ያልሠራው ወጥ ይጐረናል:: ይህ
ደግሞ ታላቅ የመንፈስ ድክመት
ነው – ከኔ በላይ ነፋስ ማለት
ያመጣልና::

*3. ታዛዥነት፡* አንድ ተዋናይ
ታዛዥ ካልሆነ በቴአትሩ ባይሳተፍ
እጅጉን ይመረጣል:: እኔ የፈለግ
ኹት ካልተሰጠኝ፣ያልኩት ካልሆነ
ማለት ከጀመረ ከዚያ በኋላ ምንም
ቢሆን ምክርና ተግሳጽ አይቀበ
ልም:: አንዳንድ ጊዜ አባቶቻችን
ይኼ ቢሆን ይሻላል በሚሉበት
ሰዓት ምክር ሰምቶ፣ ተወያይቶ፣
አስረድቶ ካልሆነም በአባቶች ቃል
ከመመራት ይልቅ ለቁጣ፣ ለኩር
ፊያ ብሎም ለዱላ የሚጋበዙ ወጣ
ቶች ይስተዋላሉ:: ይህን አርሚ፣
ይኼንን አስተካክል፣ አንተ አትሆ
ንም ወይም አንቺ አትሆኝም ሲባ
ሉም ማን ያዘኛል፣ ማን ይመክረ
ኛል፣ ከማን አንሳለሁ ባዮችም
አሉ:: ዘወትር ዋና ገጸ ባሕርይ ካል
ሆንኩ ቴአትሩን አበላሸዋለሁ የሚ
ሉም ያጋጥማሉ::

እንደዚህ ያለው ተዋናይ በመ
ጀመሪያ ለራሱ ያልታረመ በመሆኑ
ወደመድረክከመውጣቱ በፊት እራሱን
በሕግ፣ በሥርዓት፣ በምግባር ማስገዛት
አለበት:: አስቀድሞ ያልበሰለን ምግብ
ሆድ ያበስለዋል ተብሎ አይበላምና::
ከዚህም አልፎ ሰንበት ት/ቤትን ወደ
ፊት በቴአትር ቤት ለመቀጠሪያ
የሥራ ልምድ የሚጠቀሙበትም እየበረ
ከቱ መጥተዋል::
የቴአትር መድረክ ምን ይመስላል?

*ይቀጥላል*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከሞት ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

*ከባስልዮስ ዘቂሣርያ*

**ሞ**ትን ታውቁታላችሁ? እኔማ ባለፈው ሳምንት አገኘሁትና እባክህ ቃለ መጠይቅ ላድርግህ ብዬ ብጠይቀው አሻፈረኝ አለ:: ብለው ብሠራው ወይ ፍንክች:: በመጨረሻም «በዮሐንስ አፈወርቅ? ብዬ ስለምነው «ያኔ አሥራ ሁለት ዓመት ገትሮ አቁሞኛል:: አሁን ደግሞ 24 ዓመት ያደረገብኝ እንደሆነ መከራ ታሳየኛለህ» አለና እሺ አለኝ:: እኔም የነገረኝን ጻፍኩላችሁ:: እንዲህ ስል::

⌖ *ስለትውልድና ዕድገትህ ብታጫውተኝ?*

ሞት:–እያቴ ምኞት፣አባቴ ቃየል፣እናቴ ደግሞ ኃጢአት ይባላሉ:: የተወለድኩት በ5500 ዓ.ም ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው:: ከዚያ ወዲህ በመላው ዓለም እየተዘዋወርኩ የሰውን ልጅ ከዚህ ዓለም ወደዚያኛው ዓለም ሳጓጉዘው እኖራለሁ::

⌖ *ለመሆኑ «ሞት» የሚለው ስምህ ትርጉሙ ምንድን ነው?*

ሞት:– ትርጉሙ አንድ ብቻ አይደለም:: እንደየሰዉ ማንነት ይለያያል:: ለግንዛቤ ግን 3 ዓይነት ትርጉሞቼን ልንገርህ

የመጀመሪያው በቅዱሳን ትርጓሜ «መንገድ» ማለት ነው:: መቼም መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ እንደተማርከው አልጠራጠርም:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ::» በማለት ተናግሮአል:: «መንገድ» ያለኝ እኔን ነው:: ምን ያህል እንዳቀለለኝ ተመልከት:: ለቅዱሳን ከዚህ የመከራ ዓለም ወደሚወዱትና ወደሚወዳቸው አምላካቸው የሚጓዙብኝ መንገድ ነኝ በቃ!

በሁለተኛው ትርጉሜ ደግሞ 'መገላገያ' እባላለሁ:: ኑሮ የመረረው፣አልሳካ ያለው፣ የደዌዳኛ የአልጋ ቁራኛ ያሰቃየው «በገላገልከኝ» ይለኛል:: ይሁን እንጂ ብዙዎቹ ይህን ከተናገሩኝ በኋላ ስመጣ ይፈሩኛል::

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ 'መቅጫ' የሚያደርጉኝ አይጠፉም:: የዚህ ዓለም ደስታ፣ ፈንጠዝያ፣ ጭፈራ፣ ሥጋዊ ርካታ፣ወዘተ የማይጠግባቸው፣ እለሌ መለሌ እንደሆኑ መኖር የሚፈልጉ ሰዎች ቀጪኝን፣ ልትቀጨኝ ነው፣ ቀጬው ሲሉ እሰማቸዋለሁ::

ሌላም ሌላም ብዙ ትርጉም አለኝ:: ብቻ እዚህ ላይ ቢበቃኝ መልካም ነው::

⌖ *ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚገርምህን ብትነግረኝ?*

ሞት:– ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚገርመኝ ሞኝነቱ ነው:: ተመራመርኩ፣ ዐወቅኩ፣ መጠቅኩ፣ ጨረቃ ደረስኩ፣ እንዲያውም አሁን አሁንማ ነፍስ ልሠራ ነው እያለ የሚፎክረው ሰው ራሱን ሳያውቅ ቀርቶ መሞኙቱ ይገርመኛል:: ከአጠገቡ ጓደኛውን ስወስደው እኔ መኖሬ ትዝ የማይለው በአጥቢያው የጌታው ሥጋና ደም ሲፈተት ልቀበል ብሎ የማያስብ፣ አምላክ እንዳለው የሚረሳ፣ በዓለም ሁሉ ወንጌል የተሰበከ ሲያልፍ የማይነካው፣ እንዲህ ያለ ፍጡር ሞኝ አይደለም? እናንተስ በዚህ ምድር የምትኖሩት አርባ፣ ሃምሳ፣ ስድሳ ቢበዛ ደግሞ ዘጠና ነው:: እስቲ ከዚያ በኋላ የት እንደምትሄዱ ንገረኝ? በዚህ ዓለም የምትኖሩት ጥቂት በወዲያኛው ዓለም የምትኖሩት ግን እልፍ– አእላፋት ውትእልፊት...... ምኑ ተቆጥሮ? ታዲያ እንዴት ሰውን ያህል «ዐዋቂ» ፍጡር ዘመን የማይቆጠርለትን ደስታ ዘመን በሚቆጠርለት ጊዜያዊ ነገር ይለውጣል?

እግዚአብሔር የለም እያለ ሲያሾፍ የነበረውን ስንት ትዕቢተኛ እያጣደፍኩ ወስጄ ለሰማያዊ ፍርድ ሳቀርበው የነበረው ጭንቀትና የነበረው ውጥረት፣ የነበረው ለቅሶ–ኤዲያ ሰው ማለት ማሽላ ነው:: ይስቃል–ያራል:: ለምን ትሞኛላችሁ:: የፈለጋችሁትን ያህል ተደሰቱ፣ ብሉ ጠጡ፣ አጊጡ፣ ሥልጣን ያዙ፣ ግዙ፣ ንዱ እንጂ ከኔ እጅ አታመልጡ፤ጭብጥ ጭብጥብጥ፣ ኩምትር ኩምትርትር አድርጌ አፋፍሼ ስወስዳችሁ በኋላ ቀጭውን እንዳየ ሕጻን ልጅ ልትቁለጨለጩ ምንድነው ኩራቱ ትዕቢቱ!

አሁን ያ አጋግ /1ሳሙ 15÷32/ እንዲያ ሕዝቡን ሁሉ መከራ ሲያሳይ፣ በእግዚአብሔር ላይ ሲቀልድ ኖረና በእጄ የገባ ጊዜ «በውኑ ሞት እንደዚህ መራራ ነውን?» ብሎ ዐረፈው፣ ፊሪ ሁሉ! ቀድማችሁ አትዘጋጁም! ብቻ ብዙ አስለፈለፍከኝ::የሚገርመኝ ሞኝነታችሁ ነው::

⌖ *ለመሁኑ መኖሪያህ የት ነው?*

ሞት:– የት ይመስልሃል? እንደናንተ እንደናንተማ ሩቅ ነኝ:: ሞኝ ሁሉ! ከጐናችሁ ነኝ:: ካጠገባችሁ ነኝ:: አንዳንዱማ ሬሳ ላይ ወይም መቃብር ሥፍራ ብቻ ያለሁ ይመስለዋል::አይ ሞኝ! ስትበሉ፣ ስትጠጡ፣ ስትጸልዩ፣ ስትጾሙ እታዘባለሁ:: እኔ ከሰው ርቄ አላውቅም:: እናንተ ግን ትረሱኛላችሁ:: መኖሬም ትዝ ስለማይላችሁ ዘላለም በዚህች ምድር ትኖሩ ይመስል ካለ ሥጋ ፈቃድ ሌላ አይታያችሁም አንዳንድ ጊዜ ታሳዝኑኝና በበሽታ፣ በጓደኛ ሞት፣ ወዘተ አስደነግጣችኋለሁ ምን ያደርጋል? «ታሞ የተነሣ እግዜርን ረሳ» ነው፣ ወዲያው ትረሱኛላችሁ:: ሰው ሞትን ይረሳል እንጂ ሞት ሰውን አይረሳም::

⌖ *በጣም የተደሰትክባቸው ቀናት ካሉ ብትጠቅስልኝ ?*

ሞት:– አሉ:: እጅግ በጣም:: ቃየል አቤልን ሲገል፣የሰው ልጅ በኃጢአቱ በንፍር ውኃና በእሳት:: ተቃጥሎ ሲጠፉ፣ ከእሥራኤል በአንድ ቀን 24 ሺህ ሰው ሲረግፍ ... ምኑን ልዘርዝርልህ ያን ቀን እየፈነደቅኩ ሳግዝ ነው የዋልኩት::

⌖ *ዛሬ ዛሬስ በምን ትደሰታለህ?*

ሞት:– አሁን አሁንማ ከማዝንበት የምደሰትበት ይበዛል:: በኑፋቄና በክህደት ስትያዙ፣በዝሙት፣በአሽሼ ገዳሜ፣ በስርቆት ወዘተ... ስትዋጡ ፌሽታ ነው ደስታ:– ብቻ ይችን ምሥጢር ለማንም ትንፍሽ አትበል::

⌖ *ወገን፣ወገን አለህ ወይስ አንድ ብቻ ነህ?*

ሞት :– አለኝ::



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

⌖ እስቲ ዘርዝረህ ንገረኝ?

ሞት፡- ሁለት ዓይነት ዘር አለኝ። የመጀመሪያው ሞተ ሥጋ ይባላል። ሁለተኛው ደግሞ ሞተነፍስ፤ ሞተ ሥጋ ለማንም የማይቀር ቅዱሳን እንኳን የሞቱት ሞት ነው። የነፍስ ከሥጋ መለየት ማለት ነው። ሞተ ነፍስ ግን በራሱ ሁለት ወገን አለው። አንደኛው በዚህ ዓለም በኃጢአት የምትሞቱት ሞት ነው። ሰው ኃጢአት ከሠራ ሞተ ማለት ነው። ለአንበሳ መምተር አትበለ ኝና፡- የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ሲመለስ «ይህ ልጄ ሞቶ ነበር ደግ ሞም ሕያው ሆነ» ሲል አባቱ ተና ግሮአል። /ሉቃ 15÷24/ ነገር ግን በአካለ ሥጋ አልሞተም ነበር። ኃጢአት ስለሠራ ከአባቱ ቤት ስለኰበለለ ግን እንደ ሞተ ተቈጠረ ። ከንስሐ፣ከሥጋወደሙ በጠቅላላው ከነገረ ቤተክርስቲያን መራቅ የቁም ሞት ይባላል። ሞኝ ሁላ! እናንተ ሙታን ሙት ልትቀብሩ ጥሩንባ ነፍታችሁ ደረት እየደቃችሁ «ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ?»ትላላችሁ። በና ንተ ቤት እናንተ ሕያው ሆናችሁ ሙት ትላላችሁ። መቅበራችሁ ነው? ማቴ8÷22። እናንተ ራሳችሁ ከሞታችሁ ስንት ዘመን ዐለፈ። ይልቅ ጉበዝ ከሆናችሁ፣ጥሩንባ አስ ነፋና ወዳጅ ዘመድ ሰብስባችሁ ለራሳችሁ አልቅሱ። /ሉቃ 23÷29/ ዝንጀሮ የራሷ መላጣ አይታያት በሰው መላጣ ትስቃለች አሉ፤ እኔኮ የእገሌ ሀገር ሕዝብ ሠላሳ ሚሊየን፣ አርባ ሚሊየን፣ አሥር ሚሊየን ስትሉ ትገርሙኛላችሁ? እንኳን ሠላሳ እና አርባ አንድ ሚሊ ዮን ሰው ይገኛል? ዕድር ያላወ ቀው፣ ሠፈር ያልቀበረው አሁንም ከራሽን ያልተሠረዘ ስንት ሟች አለመሰለህ አለ?

ሁለተኛ ሞተ ነፍስ በገሀነም ነው። በዚህ ዓለም እያለ በቁሙ የሞተ ሰው የተሰጠውን ጊዜው ተጠ ቅሞ ወደዚያ ወደጠላቴ ወደ ንስሐ ካልቀረበ የዘላለም ሞት አይቀርለ ትም፤ በሰማይ የሚያጸድቅ በምድር ያስታውቃል' እያላችሁ ትገጥሙ የለ የዘላለም ሞት፣ ለቁም ሞት ታላቅ ወንድም ነው።

እነ ማርያም እንተ እፍ ረት፣ እነ መግደላዊት ማርያም፣ እነ ቅዱስ ጳውሎስ፣እነ ማርያም ግብጻዊት፣እነ ሙሴ ጸሊም፣ እነ ሐዋርያው ናትናኤል፣ እነ ፈያታዊ ዘየማን አመለጡኝ። ከቁም ሞት ወደ ዘላለም ሞት ልወስዳቸው ነው ስል፣በንስሐ መንገድ ሾለኩብኝና ወደ ሕያዋን መንገድ ገቡ። ወይ ነዶ!

⌖ ሰዎችን እንዴት ትመለከታቸዋለህ?

ሞት ፡- ሰው ማለት በሰው ሀገር ድርቅ ያለ ፍጡር ነው። የናንተ ሀገር እኮ በገነት በመንግሥተ ሰማያት ነው። ወደዚህ የመጣችሁት በኃጢአታችሁ በግዞት ነው። ድርቅ ስትሉ ትገርሙኛላችሁ። አንድ መንገደኛ በሰው ቤት ገብቶ በእንጀራውም በወጡም ልዘዝበት፣ በሰው ገንዘብ ልዝናና ልደሰት፣ አርፌ ልተኛ አትቀስቅሱኝ ቢል ምን ትለዋለህ? እናንተም ወደዘለዓለማዊ ቦታችሁ የምትሄዱ መንገደኞች ናችሁ። ይህ ኑሮአችሁ የእንግድ ነት ኑሮ ነው፤ /ዘፍ47÷9/ ግን «እን ግዳ ሆነሽ ትመጭ ባለቤት ሆነሽ ትቆጭ»




እንደሚባለው መንገዳችሁን ትታ ችሁ እዚህችው እንቅር ስትሉ ታስ ገርማላችሁ። ሳይቀርላችሁ ዕዳ ምናለ አጉል ባትባክኑ። ስደተኛ መጻተኛ ቤት ልሥራ፣ዘር ልዝራ አይልም። ከአንዱ ተጠግቶ ቀን እስ ኪያልፍ ይቆያል። የሥጋ ቤት ልሥራ የኃጢአት ዘር ልዝራ ማለ ታቸውን ትተው ሥጋቸውን ለነፍ ሳቸው አስጠግተው ስንቶቹን አምል ጠውኛል፤ ወይኔ ያባቢላ ልጅ! ለዚህ ነው ሰው ማለት በሰው ሀገር መጥቶ ድርቅ ያለ ፍጡር ነው ያልኩህ።

⌖ ሰዎች ለምን ይፈሩሃል?

ሞት፡-እግዚአብሔርን ስለማይፈሩ

⌖ -ሞትን ቀምሰህ ታውቃለህ?

ሞት፡- አዎ።

⌖ መቼ?

ሞት፡-ወልደ አምላክ በሞቱ ገድሎኛል።

⌖ ታዲያ አሁን እንዴት ትኖራለህ?

ሞት፡- ጥንት የነበረው አባቴ እን ደፈለገ የሚገዛ የሚነዳ ነበር። ሰውን ሁሉ ወደ ሲዖል ሲያግዘው ኖረ። በኋላ ግን ወልደ አምላክ በሞቱ ከገደለው በኋላ ያለሁት ሞት ልታሸንፉኝ የምትችሉ ደካማ ፍጥረት ሆኜ ቀረሁ። እናንተም የተሸናፊ ተሸናፊዎች ናችሁ።

አሁን ታዲያ ያሸነፍኩትን ስገዛ፣ ያሸነፈኝም ሲገዛኝ እኖራለሁ። /1ቆሮ15÷54–55/

⌖ እስቲ ከአስቂኝ ገጠመኞችህ አጫ ውተኝ?

ሞት፡- አንድ ንፉግ ሰው በአንድ ሀገር ውስጥ ይኖር ነበር። አራጣ እያበደረ ድኻ እያስቃየ፣ደካማ እየቀማ ሀገሩን አስጨነቀው። በመጨረሻ ሰው ሁሉ ተሰብስቦ ይህ ሰው ካልሞተ ጤና አናገኝም አሉና፣ የሬሳ ሳጥን ገዝተው ሰውየ ውን ተጋግዘው ገንዘው ከከተቱት በኋላም «አቶ እገሌ ሞቷልና አቃ ብሩን» ተብሎ በጥሩንባ እየተለፈፈ ሠፈርተኛው ግልብጥ ብሎ ወጣ። ደረት እየደቁ፣ሙሾ እያወረዱ ወደ ቀብር ቦታ።

ሰውየው ሳጥኑ ውስጥ ሆኖ «እረ አልሞትኩም ውሸታቸውን ነው» ቢል ማን ሰምቶት፣፡ መንገድ ላይ ሦስት የመንደር ዳኞች ችሎት ሲያስችሉ ለቀስተኛውን አዩና «ማን ሞተ» ብለው መጠየቅ። «ኑፉጉ ሰውየ» አለ ሠፈርተኛው። «እረ ውሸታቸውን ነው አልሞትኩም»





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አለ ሰውየው ሳጥኑ ውስጥ ሆኖ:: ዳኞቹም ግራ ገባቸው::

«በሉ አንተም ላለ መሞትህ፣ እናንተም ለመሞቱ አስመስክሩ» ተባለ:: ሠፈርተኛው አንድ ሆኖ «ሞቷል» አለ:: ሰውየው ግን ምስክር ከየት ያምጣ:: ዳኞቹም «እንግዲያማ ሞተሃል ማለት ነው» ብለው አስቀበሩት ይባላል::

«ሳይያዙ ነው ሳይያዙ፣
ከተያዙማ ብዙነው መዘዙ::»
የተባለው ለዚህ ነው::

⌖ *አሳዛኝ የምትለው ገጠመኝስ አለህ?*

<u>ሞት</u>:- አዎ::
ወልደ እግዚአብሔር ሞቶ ከሥልጣኔ የሻረኝ ጊዜ ::

⌖ *ባንተ መዝገበ ቃላት ሃይማኖት፣ ንስሐ፣ ኃጢአት እና ገንዘብን እንዴት ትፈታቸዋለህ?*

<u>ሞት</u>:-

<u>ሃይማኖት</u>:- የኔን መራርነት ለቅዱሳን የሚያጣፍጥላቸው ወይን ነው

<u>ንስሐ</u>:- ከዘለዓለም ሞት የሚያመልጡበት በር ነው::

<u>ኃጢአት</u>:- ዓለም ከተባለው ዘማዊ ሰው እኔን በዲቃላነት የምትወልድ ጋለሞታ ናት

<u>ገንዘብ</u>:- ላላወቁበት ሰዎች እኔን በድካማቸው ውጤት የሚሸምቱበት መሣሪያ ነው::

⌖ *የወደፊት ዕጣ ፈንታህ ምንድነው?*

<u>ሞት</u>:- ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በክበበ ትስብእት በግርማ መለኮት እስኪመጣ ሰውን ሳግዝ እኖራለሁ:: ከዚያ በኋላ ግን እኔም ለመጨረሻ ጊዜ እሞታለሁ::

⌖ *ከመሰናበታችን በፊት ለሰዎች ምክር ብጤ አለህ?*

<u>ሞት</u>:- በሰው ሀገር አትድረቁ፣ አለማወቃችሁን ዕወቁ፣ ሞኝነታችሁን አርቁ::

አመሰግናለሁ::

## የግእዝ ቅኔያት

*ሥላሴ*

/ዘመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ/

ሰአልዎ እስራኤል
ለሙሴ ይትገለበብ በሰንዱናት
ኀጡተ ብርሃን ኅቱቲት በገጹ አመ ነጸርዎ
ፈርሁ::
ይእዜሰ እምኀበ ኢኮነ ብርሃኑ ከማሁ
እግዚአ ሙሴ ክርስቶስ ለዘሀለዉ ምስሌሁ
በምንት ይትገለበብ ገጸ ዚአሁ?
እስመ ከመ መብረቅ በረቀ አልባሲሁ
እስከ ስዕኑ ነጽሮ ኪያሁ::

*ትርጉም*

እስራኤል ትንሽ
የብርሃን ቅንጣትን በፊቱ
ማየትን ቢፈሩ በጨርቅ /ጉጭ ልብስ/ ፊቱን
ይሸፍን ዘንድ ሙሴን ለመኑት
ዛሬ ግን ብርሃኑ እንደርሱ ካልሆነ ዘንድ
የሙሴ ጌታ ክርስቶስ ከርሱ ጋር አብረው ላሉት
ፊቱን በምን ይሸፍን?
እርሱን ማየትን እስኪሳናቸው ድረስ
ልብሱ እንደመብረቅ በርቋልና::

*ምሥጢር*

ሙሴ ፊቱ ቢያበራ እስራኤል ማየት ስለተሣናቸው ፊቱን በልብሱ ይሸፍን ነበር:: የሙሴ ጌታ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ፊቱ እንደመብረቅ ባበራ ጊዜ በምን ይሸፍነው? ልብሱ ራሱ ያበራል ያንፀባርቃልና!

የግእዝ ቅኔያት፣2ኛ ክፍል ገጽ 16

## በመንገድህ ላቅና

በሃይማኖት ጉዞ ፍቅርህን ሰንቄ
በእምነት ጋሻና ጦር ወገቤን ታጥቄ
ተስፋን ተላብሼ እውነት ተመርኩዤ
ድንግል እመቤቴን አማላጄን ይዤ
ቃልህ እየመራኝ በመንገድህ ላቅና
አንተን የፈለገ አያጣህምና::

ወንድወሰን ተፈራ
/ሲዳሞ–ለኩ/

## ማስታወቂያ

ማኅበራችን የ1990 የቀን መቁጠሪያ የያዘ የአዲስ ዓመት ፖስት ካርድ ማሳተሙን ለአንባብያን በደስታ ይገልጣል::

የማኅበረ ቅዱሳን
የልማት ክፍል

## እኔስ ሰው አማረኝ

ጸንቶ የተገኘ ያለፈ ፈተና
ፍቅርና ትኅትናን አንድ አርጐ የያዘ
በዓለም ፍቅር ታሥሮ ልቡ ያልናወዘ
ትእዛዙን ሁሉ ሠርቶ የሚያሳየኝ
እሱ ተቆጥቦ አታድርግ የሚለኝ
እራሱ ተምሮ ለሌላው የሚመክር
እኔስ ሰው አማረኝ እውነተኛ መምህር
እንደበቱ ያረፈ ከተንኮል ከሐሜት
ልቡናው የነጻ ከክህደት ከትዕቢት
የእምነት ሰው ሆኖ መንገድ የሚመራኝ
የሃይማኖት ጀግና እኔስ ሰው አማረኝ::

ከመስፍን ወንድሙ /ድሬዳዋ/

## በተዋሕዶ ጽና

የዓለም ፍቅር ስቦት እንደጠፋ ዴማስ
በመንፈስ ጀምረህ በሥጋ እንዳትጨርስ
ሰዶምን አስታውሰህ የኃጢአትን ከተማ
እንደሎጥ ሚስት አንተም ልብህ ሳያቅማማ
በወረት ጀምረህ በከንቱ እንዳትቀር
በልብህ ላይ ይሳል የክርስቶስ ፍቅር::
እምነት ፋሽን አይደል አይለዋወጥም
የጸና ይድናል ቃሉ አይታበልም
እናም እልሃለሁ ዛሬም ትናንትና
ያለማወላወል በአንዲቷ ጐዳና
እስከመጨረሻው በተዋሕዶ ጽና::

መ/ር አማረ ጠናጋሻው
/ሒርና/

## በተነጠቅን ጊዜ

ተርቦ ሊበላ ጴጥሮስ ሽቶ ሳለ
አራት ማዘን ሸማ ፊቱ ከተፍ አለ
እጅግ ተጠግቶ በተመስጦ ሲያየው
ልዩ ልዩ እንስሳት የያዘ ሸማ ነው::
«ጴጥሮስ ሆይ! በል ተነሥ እረድና ብላ»
የሚል ቃል ሲሰማ ልቡን ፍርሃት መላ
«ጌታሆይ ይቅርብኝ..ይቅርብኝ አይሆንም
የሚያፀይፍ ነገር ነክቼ አላውቅም»
ሦስቴ ተለመነ አርዶ እንዲበላ
እርሱ ግን ወይ ፍንክች ልክ እንደመሐላ
ሦስተኛው ልመና ወዲያው እንዳለቀ
ያ ታላቁ ሸማ ሔደ ተነጠቀ
ረሀቡ በዝቶ ውስጡ እንደታመቀ::
እኛም ዛሬ ያው ነን
ብሉኝ ጠጡኝ ብሎ ራሱን ሲሰጠን
ግብዣውን አቃለን አልቀበል ካልነው
በተነጠቅን ጊዜ እጃችን ባዶ ነው::

ኀብሩ ቀለሙ /አ.አ.ዩ/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

*ከኃይለ አብ ትኩእ-/መቐሌ/*

በምሥራቅ ትግራይ ከዕደጋ ሐሙስ ከተማ ምሥራቃዊ አቅጣጫ 23 ኪ.ሜ ርቀት በመኪና፣ ለ4ሰዓት ያህል ደግሞ በእግር ከተጓዙ በኋላ በረሃ ውስጥ የሚገኝ ገዳም ነው:: ገዳሙ የተገደመው በ14ኛው መ/ክ/ዘመን ሲሆን፣ የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የታነፀው ደግሞ በ15ኛው መ/ክ/ዘ መሆኑ ይነገራል::

ይህን አስቸጋሪ በሆነው በረሃ ውስጥ የሚገኘውን ጥንታዊ ገዳም ለመሳለም ጽኑ ሃይማኖታዊ ጥንካሬን ይጠይቃል::

የጉንዳጉንዲ ገዳም በተለያዩ ዘመናት የተሠሩ ሕንፃዎችን በአንድነት አጠቃሎ የያዘ ነው:: በመቅደሱ ባለ 4 ዓምደ ወርቅና በተያያዥነት የተሠሩ በርከት ያሉ ሠረገላዎችም ይታያሉ:: በመቅደሱ ውስጥ የገዳሙ አባቶች ለቅዱሳት መጻሕፍት፣ ለንዋያተ ቅድሳትና ለጥንታውያን ቅርሶች የማያደርጉት እንክብካቤ ለሌሎች ገዳማት አርአያነት ያለው መሆኑ ይነገራል::

ከዛሬ 20 ዓመታት በፊት በገዳሙ ውስጥ እጅግ ብዙ መነኩሳት እንደነበሩ በሥፍራው ያሉና በልዩ ልዩ ጊዜ ገዳሙን ጎብኝተው የነበሩ ሰዎች ያስታውሱታል:: በ1967 ዓ.ም የገዳሙ መሬት ከተወረሰ በኋላ ግን በየጊዜው በሚከሰተው ረሃብ የተነሣ ዛሬ በገዳሙ የሚገኙት ከ10 ያልበለጡ መነኩሳት ብቻ ናቸው::

ያንን ታላቅ በረሃ አቋርጦ በእምነት ወደ ማርያም ጉንዳጉንዲ ገዳም የሚዘልቀውን ምእመን ድንጋጤላይ የሚጥልና አለሁ ወይስ የለሁም? ምን እየሠራሁነው? የሚያሰኝ አደጋ በገዳሙ ላይ አንዣቦ ይታያል::

## ጉንዳጉንዲ

### /በአደጋ ላይ ያለ ቅርስ/

የእሳተ ገሞራ ፍሕም የሚገኝ ሲሆን መነኰሳቱ ለማዕጠንት እሳት የሚጭሩት ከዚሁ እሳተ ገሞራ ነው:: የሕንፃው ጠቅላላ አሠራር በተንቤን ከሚገኘውና ከዐለት ተፈልፍሎ ከተሠራው ከአባ ዮሐኒ ገዳም ጋር ይመሳሰላል:: ይህን የቤተመቅደስ ሕንፃ ያሠሩት አባ ዕዝራ የተባሉ አባት ናቸው::

ከመቅደሱ ቀጥሎ ሁለተኛው ክፍል መቅደሱን በአራት ማዕዘን ከቦ፣እያንዳንዱ ዓምድ በነሐስ እንዲገናኝ ተደርጐ የተሠራው ቅኔ ማኅሌቱ ወርዱና ቁመቱ ከመጀመሪያው ሕንፃ ከፍ ይላል:: የተሠራውም መቅደሱ ከተሠራ ከ30 ዓመታት በኋላ አባ መዝገበ ሥላሴ በተባሉ አባት ነው::

በዚህ ጥንታዊ ገዳም ከ200 በላይ ታሪካውያን ቅዱሳት መጻሕፍት በልዩ ጥንቃቄ ተቀምጠዋል::

በአባ መዝገበ ሥላሴ የተሠራው ቅኔ ማኅሌት እዚህም እዚያም ተሰነጣጥቋል:: ግድግዳው ዞር ብሎ ላተኛበት የሚል ይመስል ጋደል ብሏል:: ወደ ቅኔ ማኅሌቱ የሚገባ ሰው እምነቱ ጠንካር ያለ ካልሆነ በቀር አሁን ካሁን በላዬ ላይ ይወድቃል ብሎ መስጋቱ አይቀሬ ነው:: የገዳሙ አበው ከዛሬ ነገ ሕንፃው ተንዶ ታሪኩ ይጠፋል ብለው ኑሮአቸው ሁሉ ሥጋት እና ሐዘን የተቀላቀለው ነው::

ቤተክርስቲያን በአርባና በሰማንያ ቀን ከመንፈስ ቅዱስ የወለደቻቸው ልጆችዋ እንዲህ ከመሰለው የከፋ አደጋ ይህንን ታላቅና ጥንታዊ ገዳም መታደግ ካልቻሉ-አለበነበረ እየተተካ የአባቶቻችን ሃይማኖትና ታሪክ ወራሾች መሆናችን ይቀርና ቀባሪዎች እንሆናለን::

ምንጭ-የትግራይ ቱሪዝም ቢሮ

ከአዘጋጁ- በየቦታው የምትገኙ የቤተክርስቲያን ልጆችና የቱሪዝም ቢሮዎች እንደዚህ ዓይነቱን የቅዱሳት መካናትን ታሪክ ለዝግጅት ክፍሉ በመላክ ለምእመናን በማስተዋወቁ ሥራ የበኩላችሁን አስተዋጽዖ ብታበረክቱልን ለማስተናገድ ዝግጁዎች ነን:: ለዛሬው ኃይለ አብ ትኩእን እና የትግራይ ቱሪዝም ቢሮን እናመሰግናለን::

## ብሂለ አበው

### «ከወዴት አገኘሽው....?

አንድ 78 ዓመት የሆናቸው ኢትዮጵያዊ አባት ትምህርት ቤት ገብተው ሲማሩ አንድ ተማሪ «አባቴ ከአሁን በኋላ ተምረው ሊሾሙ ነው ወይስ ሊከበሩ በትና ሊታዩበት?» ብሎ ቢጠይቃቸው «አይ የኔ ልጅ! እሾምበት፣ እታይበትና እከብርበት ብዬ አይደለም:: ነገር ግን ያ የማይቀረው ሞት ሲመጣ ፣መልአከ ሞትም ይዞ ወደ ፈጣሪዬ ሲያቀርበኝ «ወዴት አገኘሽው?» ተብሎ ሲጠየቅ «ከአትሮኖሱ እግር አገኘሁት» ብሎ እንዲመሰክርልኝ ብዬ ነው::» ሲሉ መለሱለት::

የሚገኝበትን ቦታ ያስተካከለ ሰው ዐዋቂ ነው:: የኛስ የዘወትር መገኛችን ወዴት ይሆን?

ከዲ. ከፍያለው ጥላሁን
/ቅ/ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እምነ ወለተ ጴጥሮስ

/17ኛው መ/ክ/ዘመን/



እምነ ወለተ ጴጥሮስ /ኢትዮጵያዊት/

አባትዋ ባሕር አሰግድ እናትዋ ደግሞ ክርስቶስ ዕበያ ይባላሉ:: ትውልድዋ ከዳዋሮ /ምሥራቅ ኢትዮጵያ/ ወገን ነው:: ወንድሞቿ ዮሐንስና ዘድንግል በንጉሥ ሱስንዮስ ዘንድ ታላላቅ ባለሥልጣናት ነበሩ::

እናትና አባትዋ በሕግ በሥርዓት ካሳደጉዋት በኋላ ለአንድ ትልቅ መኰንን ዳርዋት:: ነገር ግን አጼ ያዕቆብ /1588–1595/ ባልዋን በግፍ ስለገደሉባት ሥዕለ ክርስቶስ የተባለ የሱስንዮስ የጦር አበጋዝ ቢትወደድ አግብታ 3ልጆች መውለድዋን ገድሏ ይናገራል:: 1ቆሮ 7÷39 /ይህ ቢትወደድ ይኖርበት የነበረው ግንብ ቤት ፍራሽ እስካሁን ድረስ በጋይንት–ስማዳ ይታያል/

ወለተ ጴጥሮስ ከቢትወደድ ሥዕለ ክርስቶስ ጋር በሰላም በመኖር ላይ እያለች በመካከላቸው የማይታረቅ ቅራኔ ተፈጠረ:: ንጉሡ አጼ ሱስንዮስ የተዋሕዶ ሃይማኖቱን ቀይሮ በሮማውያን በመታለል ካቶሊክነትን ተቀብሎ ዐወጀ:: በዚህ ዐዋጅ የተነሣ በንጉሡ ደጋፊዎችና የቀደመ ሃይማኖታችንን አንለውጥም ባሉት መካከል ታላቅ ጠብ ሆነ:: የንጉሡ ሠራዊትም በተዋሕዶ ምእመናን ላይ ዘመተ::

ቢትወደድ ሥዕለ ክርስቶስ ከዘመቻ ሲመለስ የጳጳሱን የአቡነ ስምዖንን ልብስ እንደ ግዳይ ሰልባ ለንጉሡ ይዞለት መጣ:: የሃይማኖትዋን መናቅ፣ የአባቶቿን መደፈር የተመለከተችው ወለተ ጴጥሮስ እንደ ዚህ ካለው ከሃዲ ጋር በአንድ ቤት መኖር አያስፈልግም ብላ ቆረጠች:: የምትጠፋበትን መንገድ በድብቅ ከጣና መነኰሳት ጋር መላላክ ጀመረች:: የጣና ቂርቆስ ገዳም አበምኔት አባ ፊትለ ሥላሴም ወለተ ጴጥሮስን ይዘዋት እንዲመጡ ሁለት መነኰሳትን ላኩ:: /በዚያ ጊዜ ልጆቿ ሁሉ ሞተውባት ነበር:: /ወለተ ጴጥሮስ ከመነኰሳቱ ጋር መጥፋቷን ያወቀው ቢትወደድ ሥዕለ ክርስቶስ ይዘው ያመጡለት ዘንድ አያሌ ሠራዊት ከኋላዋ ሰደደ:: ነገር ግን ወለተ ጴጥሮስና ሁለቱ መነኰሳት እልም ባለ ዱር ውስጥ ተደብቀው ስለነበር ሊያገኙዋቸው አልቻሉም:: ይህ ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ «ሳጋ» ወለተ ጴጥሮስ» ይባላል:: በኋላ ዘመንም በስሟ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበታል::

ከዚህ በኋላ ወደ ደብረ ዕንቁ ገዳም ገባችና ምንኩስናን ተቀበለች:: ታላቁ ገድሏ የተጀመረውም ከዚህ በኋላ ነው::

እምነ ወለተ ጴጥሮስ ከምንኩስናዋ በኋላ በመላዋ ሀገሪቱ እየተዘዋወረች ሕዝቡ በተዋሕዶ ሃይማኖቱ እንዲፀና፣ በቅዳሴም ጊዜ ሃይማኖቱን የለወጠው የንጉሡ የሱስንዮስ ስም እንዳይጠራ ታስተምር ጀመር:: ብዙ ሰዎችም በትምህርትዋ ተስበው በሃይማኖታቸው እየጸኑ ሰማዕትነትን መቀበል ያዙ::

ይህንን የእምነ ወለተ ጴጥሮስን ተጋድሎ የሰማው ንጉሡ ሱስንዮስ ተይዛ በፊቱ ለፍርድ ትቀርብ ዘንድ ብዙ ወታደሮችን በየአካባቢው አሰማራ:: በመጨረሻም በሠራዊቱ ተይዛ በሱስንዮስ ፊት ቀረበች:: መሳፍንቱ፣መኳንንቱና ለእንጀራቸው ሲሉ ሃይማኖታቸውን የሸጡ ሊቃውንት በተሰበሰቡበት ትመረመር ጀመር::

ከሳሽዋ «ንጉሡን ካድሽ፣ እግዚአብሔርን ካድሽ፣ ትእዛዙን እምቢ አልሽ፣ሃይማኖቱን ዘለፍሽ፣ ሌሎች ሰዎችም ሃይማኖቱን እንዳይቀበሉ ልባቸውን አሻከርሽ» ሲል ከሰሳት:: እምነ ወለተ ጴጥሮስ ግን እንደፈጣሪዋ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በከሳሾቿ ፊት ዝም አለች:: ንጉሡም ርቃ እንዳትሄድ ነገር ግን ከቅርብ ዘመዶቿ ጋር ብቻ እንድትኖር /የቁም እሥር/ ፈረደባት::

ሃይማኖት ተንቃ፣ ቤተክርስቲያን ተዋርዳ የመናፍቃን መጫወቻ ስትሆን ማየት የሃይማኖት ፍቅርዋ ያላስቻላት እምነ ወለተ ጴጥሮስ በግዞት መልክ ከተቀመጠችበት ቦታ ጠፍታ ዘጌ ገዳም ገባች:: አብረዋትም ወለተ ጳውሎስ እና እኅተ ክርስቶስ የተባሉ እናቶች ነበሩ:: በዚያም በገዳሙ የነበሩ መነኰሳትንና የአካባቢውን ምእመናን ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው እያስተማረች በእምነታቸው እንዲጸኑ እየመከረች ጥቂት እንደቆየች የሚያሳጧትና የሚከሷት ስለበዙ ቦታውን ለቃ ወደ ዋልድባ ገባች:: ዋልድባ ገብታ ሱባዔዋን ከፈጸመች በኋላ በገዳሙ የነበሩ አባቶችንና እናቶችን በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆዩ ትመክራቸው ጀመር::

አጼ ሱስንዮስ የእምነ ወለተ ጴጥሮስ ተጋድሎ መነኰሳትንና ምእመናንን በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ፣ ከክህደታቸው እንዲመለሱ ማድረጉን ሲረዳ ብዙ ተከታታዮች ይልክባት ነበር:: በዋልድባ እያለችም የንጉሡ ሠራዊት ሊያኖሯት ስላልቻሉ ወደ ጸለምት አመራች::

በጸለምት የወለተ ጴጥሮስ ትምህርት እንደ ቸቦ እሳት ተስፋፋ:: ምእመናን እየወደዷትና እየተቀበሏት ራሳቸውን ለሰማዕትነት አዘጋጁ:: ይህንን የሰማው ሱስንዮስ ይህች ሴት እኔ ብተዋት እርስዋ አልተወችኝም፣ እኔ ብምራት እርስዋ ይቅር አላለችኝም አለና የጸለምቱን ገዥ ባላምባራስ ፊላታዎስን





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ወለተ ጴጥሮስን እንዲያመጣለት አዘዘው፡፡

እምነ ወለተ ጴጥሮስ በጸለምቱ ገኘ ተይዛ ወደ ሱስንዮስ መጣች፡፡ አስቀድመው ሃይማኖቷን እንድትለውጥ ሊያግባቡዋት ሞከሩ፡፡ እርስዋ ግን ጸናች፡፡ ሦስት የካቶሊክ ቀሳውስት መጥተው ስለሃይማኖትዋ ተከራከርዋት፡፡ ወለተ ጴጥሮስ ግን የሚገባቸውን መልስ ሰጥታ አሳፈረቻቸው፡፡ በየቀኑ የካቶሊክ ቀሳውስት ሃይማኖትዋን ትታ ካቶሊክ እንድትሆን በምክርም በትምህርትም ሞከሩ፡፡ ይሁን እንጂ ወለተ ጴጥሮስ በዐለት ተዋሕዶ ላይ ተመሥርታ ነበርና ፍንክች አላለችም፡፡

በመጨረሻ አንዱ የካቶሊክ ቄስ «እርስዋን እቀይራለሁ ማለት በድንጋይ ላይ ውኃ ማፍሰስ ነው» ሲል ለንጉሡ አመለከተ፡፡ ሱስንዮስ ይኼንን ሲሰማ ሊገላት ቆረጠ፡፡ አማካሪዎቹ ግን «አሁን እርስዋን ብትገል ሰው ሁሉ በሞትዋ ይተባበራል፡፡ ደግሞ ሰው ሁሉ ካለቀ በማን ላይ ትነግሣለህ፡፡ ይልቅስ ታሥራ ትቀመጥ» ብለው መከሩት፡፡ ንጉሡም ገር በል ወደተባለው በረሃ ሊልካት ወሰነ፡፡

መልክዐ ክርስቶስ የተባለው ዋነኛ የካቶሊኩች አቀንቃኝ ወደ ሱስንዮስ ፊት ቀርቦ «ንጉሥ ሆይ በፊትህ ሞገስን ካገኘሁ ክረምቱ እስኪያልፍ ድረስ እኔ ዘንድ ትክረም፡፡ እኔም እመክራታለሁ፡፡ የፈረንጆቹ መምህር አልፎንስም ሁልቀን መጽሐፉን ያስማታል፡፡ ይህ ሁሉ ተደርጎ አሻፈረኝ ካለች ያን ጊዜ ግዞት ላካት» ሲል ለመነው፡፡ ንጉሡም ተስማማ፡፡

መልክዐ ክርስቶስ ወለተ ጴጥሮስን የካቶሊኩች ጳጳስ ከሚኖርበት ጐንደር አዘዞ ወሰዳት፡፡ ሁለቱ ተከታዮቿ ወለተ ክርስቶስና እኅተ ክርስቶስ አብረዋት ሰነበቱ፡፡ ወለተ ጳውሎስ ዛጌ ቀርታለች፤ አልፎንሱ ሜንዴዝም ዘወትር እየሄደ የልዮንን ክህደት ያስተምራት ነበር፡፡ ንጉሡም ወለተ ጴጥሮስን ወደ ካቶሊክነት መቀየር በየጊዜው ይጠይቃል፡፡ የሚያገኘው መልስ ግን ሁልጊዜ አንድነው «በፍጹም»፡፡

ክረምቱ አለፈ፡፡ ኅዳርም ታጠነ፡፡ ወለተ ጴጥሮስ በትምህርትም በማባባልም ከተዋሕዶ ሃይማኖትዋ ንቅንቅ አልል አለች፡፡ ስለዚህም ወደ ስደት ቦታዋ ገርበል በረሃ በሱስንዮስ ወታደሮች ተጋዘች፡፡ ወለተ ጴጥሮስ ብቻዋን ገርበል ወረደች፡፡ በእርጅና ላይ ያለችው እናቷ ይህንን ነገር ስትሰማ አንዲት አገልጋይ ላከችላት፡፡ ቆራጢ ተከታይዋ እኅተ ክርስቶስም ወዲያው ወደርስዋ መጣች፡፡

ገርበል በረሃ ለ3 ዓመት ስትኖር ብዙ ጊዜ ትታመም ነበር፡፡ ነገር ግን መከራውን ሁሉ ስለ ሃይማኖቷ ቻለችው፡፡ ከ3 ዓመት በኋላ ዮሐንስ የተባለው ወንድሟ ከንጉሡ ልጅ ከፋሲለደስ ዘንድ ቀርቦ እኅቱ ትፈታ ዘንድ ለንጉሡ እንዲማልደው ነገረው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በመካከላቸው ታላቅ ቅያሜ እንደሚነግሥ አሳሰበው፡፡ በፋሲል አማላጅነትም ሱስንዮስ መፈታትዋን ፈቀደ፡፡

ከተፈታች በኋላ ደንቢያ ውስጥ ጫንቃ በተባለ ቦታ ተቀመጠች፡፡ በስደቱ ምክንያት ቆባቸውን አውልቀው የነበሩት አያሌ መነኰሳትም ስደቱ መለስ ሲል በዙርያዋ ተሰበሰቡ፡፡ በኋላም ወደ ጣና ቂርቆስ ተጉዛ በአንድ መነኩሴ ቤት መኖር ጀመረች፡፡ በዚያ መኖር ለወለተ ጴጥሮስ ደስ አላሰኛትም፡፡ ስለዚህም ከንጉሡ አስፈቅዳ ምጽሌ ወደተባለው ደሴት ተጓዘች፡፡ በዙሪያዋም አያሌ መነኰሳት ተሰበሰቡ፡፡ ነገር ግን መከራ ያልተለያት ወለተ ጴጥሮስ መዝራዕተ ክርስቶስ የተባለው ሰው ካቶሊክ ያልሆኑ ምእመናንን አስገድዶ የሚያስጠምቅበት ደብዳቤ ይዞ ወደ አካባቢው መምጣቱን ስለሰማች መነኰሳቱን መክራና አስተምራ ወደየበረሃው ከበተነች በኋላ እርሷም እንደገና ስደት ጀመረች፡፡ ተመልሳ ወደ ምጽሌ የመጣችው አገር ሲረጋጋ በ49 ዓመትዋ ነው፡፡

ከስደት ስትመለስ መኖሪያዋ ያደረገችው መንዞ የተባለውን ቦታ ነው፡፡ በዚያ ቦታ ላይ በጸሎትና በስግደት ተጠምዳ ኖረች፡፡ በምጽሌ ገዳም አብሯት የነበረው የደብረ ማርያም አበምኔት አባ ጸጋ ክርስቶስም መጽሐፈ ሐዊን ይተረጉምላት ነበር፡፡

አጼ ሱስንዮስ ምላሱ ተጉልጉሎ ከእግዚአብሔር ቅጣቱን ሲቀበልና የተዋሕዶ ሃይማኖት ስትመለስ አቡነ ማርቆስ ግብጻዊ ጵጵስና ተሾመው በ1636 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ከመንገድ ላይ ጠብቃ ቡራኬ ተቀበለች፡፡ ስለሃይማኖቷ ብላ ከባሏ መለያየቷ እስከ ግብጽ ድረስ መሰማቱን ጳጳሱ ነግረዋታል፡፡

ከዚያም ተመልሳ በመንዞ ገዳም በምግባረ ሠናይ ተቀመጠች፡፡ ያቋቋመችው ገዳም የወንዶችም የሴቶችም ነበር፡፡ ወንዶች መነኰሳት ሴት በወንዶች ላይ መምህርት መሆን የለባትም ብለው ተነሥተውባት ነበር፡፡ ነገር ግን አባ ፊትለ ሥላሴ የተባሉት አባት በነገሩ ገብተው ጠቡን አበረዱት፡፡

የተዋሕዶ ሃይማኖት ከተመለሰችና አጼ ፋሲል ከነገሡ በኋላ ንጉሡን ለማግኘትና ወንድሞቿንና ዘመዶቿን ለማየት ወደ ጐንደር ከተማ ወጣች፡፡ ንጉሡም በታላቅ ክብር ተቀበላት፡፡ በየቀኑም ሳያያት አይውልም ነበር፡፡ ወደርስዋ ሲገባም አደግድጎ ነበር፡፡ ይህም ስለሃይማኖቷ ክብር ነው፡፡

እምነ ወለተ ጴጥሮስ 24 ዓመት በዓለም፣ 26 ዓመት በምንኩስና ኖራ በ30 ዓመቷ በቆረቆረችው ገዳም ዐረፈች፡፡ መታሰቢያዋም ኅዳር 17 ቀን ይከበራል፡፡ የተከታይዋ ወለተ ክርስቶስ በዓል ደግሞ ኅዳር 7 ቀን ይውላል፡፡

በሃይማኖት ጸንቶ መጋደል ሴትና ወንድ አይልም፡፡ ቤተክርስቲያናችን እንደነ እምነ ወለተ ጴጥሮስ ያሉ አያሌ ልጆች አሏት፡፡ የዛሬዎቹ እኅቶችና እናቶችም በምግባር ታንጾ፣ በሃይማኖት ጸንቶ በእምነት መጋደልን ከነዚህ እናቶች ሊቀስሙ ይገባል፡፡ ጸሎትና በረከታቸው በሁላችን ላይ ይደር፡፡ አሜን፡፡

ምንጭ፡-ሥርግው ሀ/ሥላሴ/ዶ/ር

አማርኛ፣ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቅጽ8 ፤ ገጽ96–101 ፣1981

ለጋዜጣና ለመጽሔት ደንበኞቻችን በሙሉ

ለመጽሔትም ሆነ ለጋዜጣ ደንበኝነት ገንዘብ በባንክ ወይም በፖስታ ቤት በምትልኩልን ጊዜ መጽሔትና ጋዜጣው እንዲደርሳችሁ የከፈላችሁበትን የባንክ ደረሰኝ ወይም ሐዋላውን ከአድራሻችሁ ጋር እንድትልኩልን በትህትና እንጠይቃለን፡፡



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ለመወሰን እንድንችል ምን እናድርግ?

*ከጎርጎርዮስ ደጀኔ*

ባለፈው እትማችን ስለ ሰማያዊቷ ጥበብ ምንነት እና ስለ ምድራዊቷ ጥበብ ችግሮች እንዲሁም በውሳኔ ወቅት ድርሻ ስላላቸው ነገሮች በሰፊው ተመልክተናል:: በዚህ እትማችን ደግሞ ትዳርን በተመለከተ እንዴት መወሰን እንደሚገባን እንደሚከተለው ለመመልከት እንሞክራለን::

ትዳርን በተመለከተ ብዙ ሰዎች ለውሳኔ ሲቸገሩ እናያለን:: ቢወስኑም አንኳ በጣም እየፈሩና እየተጠራጠሩ በመንታ ልብ ነው:: የወሰኑትንም ከግብ ለማድረስ ያለው ችግር እንዲህ በቀላሉ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም:: በጋብቻ ጊዜ ያለው የድግሱና የጥሎሹ ጣጣ ያስደነግጣቸዋል:: ከጋብቻ በኋላም ከአቅም በላይ መኖር እና ሌላ ሌላውም የሚፈጥረው ጫና ምነው በቀረብኝ ኖሮ ያሰኛቸዋል:: ብዙ ሰዎች ትዳርን ከሩቁ እንዲፈሩትና እንደ ወኅኒ ቤትም እንዲቆጥሩት የሚያደርጋቸው ይኸው ነው:: ከዚህም የተነሣ «ምን በወጣኝ? ለምን ልታሰር?ይላሉ:: እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ማኅበራዊ ኑሮ ወይም ሰብአዊ ተፈጥሮ አስገድዷቸው ወደ ትዳሩ ዓለም ሊገቡ ይችላሉ ነገር ግን ይኸንኑ አመለካከታቸውን ይዘው ስለሆነ የሚገቡት ትዳራቸው ከበረዶ ይልቅ ይቀዘቅዛቸዋል:: እንደ አባ ጨጓሬም ይኰሰኩሳቸዋል::

አንዳንዶች ደግሞ የትዳር ግብ እንደምንም ተሟመተው ቤት መሥራት፣ የቤት ዕቃ ማሟላት፣ ድል ያለ ድግስ መደገስ፣ ወዘተ... ብቻ ስለሚመስላቸው የሚወስኑት ከዚህ አንፃር ነው:: የተቀሩት ደግሞ ምን አለው? ምን አላት? ተባብለው፣ ዘር ቆጥረው ወገን ለይተው፣ መልኩ ወይም መልኳ እንዴት ነው? ተባብለው ነው::

እምነት ላለው ሰው ግን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉ ከትዳር ዓላማ አንጻር ቅድሚያ የሚሰጣቸው አይደሉም:: ምክንያቱም የእምነት ሰዎች ምንጊዜም ቢሆን የሚያስቀድሙት መንግሥቱን እና ጽድቁን ነው:: የተቀረው ግን እንደ ጻረጐት እንደሚጨመርላቸው ያምናሉ:: ማቴ 6÷33:: ቤት ትዳራቸውን የሚመሠርቱት በዓለት ላይ ነው:: እንዲህ ዓይነቱንም ትዳር የሚያፈርሰው ዝናብ ጐርፍና ነፋስ የለም ማቴ 7÷24::

ስለሆነም ከዚህ ሁሉ አንጻር ወስነን ትዳር ከመመሥረታችን በፊት በትዳር ጓደኛ ምርጫ ላይ የሚከተሉትን መንገዶች ብንከተል የተሻለ ይሆናል::

1ኛ/ ከሁሉ አስቀድሞ ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቅ ይገባል:: ምክንያቱም ገና ከመጀመሪያው ወ:ድና ሴት አድርጎ የፈጠረ ቀጥሎም ሁለቱን አካል አንድ አካል ያደረገ እግዚአብሐር ነውና:: ዘፍ1÷27፣ ማቴ19÷4:: በዚህ መሠረት ትዳር ማለት ድንቅ በሆነ ምሥጢር ባልና ሚስት አንድ ሥጋ የሚሆኑበት ሕይወት ነው:: ኤፌ5÷31–32:: ይህም በእግዚአብሔር እንጂ በገንዘብ ብዛት፣ በመልክ ቀናነት፣ በዘመድ ብዛት፣ በሥጋ ዕውቀት፣ በሥልጣንና በጉልበት የሚሆን አይደለም:: ስለሆነም ገና ከመጀመሪያው እግዚአብሔርን ወደ ጐን መተው አይገባም፤ በዮሐንስ መልእክት «በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል:: የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውም ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን::» የተባለውን መርሳት እንዲኖርብንም ዮሐ5÷14:: ለወንዶቹ ሔዋናችን ለሴቱቹ አዳማቸውን የሚያውቅ እግዚአብሔር በመሆኑ ፈቃደ እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ያስፈልጋል::

2ኛ/ በልቡናችን «ትክክለኛ ሥራ ነው የሠራኛው?» እያልን ደጋግመን ራሳችንን መጠየቅ አለብን:: ምክንያቱም ዛሬ ትንሽ ቅር የሚለን ነገር ካለ በኋላ ላይ ከልቡና ዳኝነት ማምለጥ ስለማይቻል ነው:: አስተውላችሁ እንደሆነ ብዙ ሰዎች «ምን ያደርግ እሱ፤ ምን ታድርግ እሷ ጥፋቱ የእኔ ነው፤ ድሮውንም ይህን ሁሉ እያወቅሁ ነው ዓይኔን ጨፍኜ የገባሁበት፤ » እያሉ የሚያማርሩት ለዚህ ነው:: በዚህ ነገር ሲጨቃጨቁም «ወደሽ ነው፤ወደህ ነው፤ ያስገደደህ አለ? ያስገደደሽ አለ?» ሲባባሉ ይደመጣሉ:: ከዚህም የተነሣ ለትዳራቸው፣ ለቤተሰባቸው እና ለወገናቸው የማያስቡ ግድየለሾች ይሆናሉ:: ይህም እጅግ አስከፊ ሕይወት ነው:: ምክንያቱም «ስለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው:: ይላልና 1ኛ ጢሞ5÷8::

3ኛ/ በተሰጠን አእምሮ የውሳኔያችን ተፈጻሚነት እንዴት መሆን እንዳለበት ማቀድ አለብን:: ማለትም ትዳር ለመምሥረት ያለንን የገንዘብ አቅም እና ሌሎችም ይኸንን የተመለከቱ ጉዳዮችን በማውጣትና በማውረድ ውሳኔያችን «ትክክል ነው? ወይስ አይደለም?» እያልን ማሰላሰል ይጠበቅብናል:: ይህም በትዳር ጉዳና እንዴቅማችን እንድንጓዝ እና እንድንኖር ይረዳናል:: 1ኛጢሞ 6÷6፣ ፊል. 4÷11::

4ኛ/ በሁሉ ነገር ከትዳር ጓደኛችን ጋር መጣጣም አለብን ምክንያት ዛሬ እንደ ቀላል የቆጠርናቸው ነገር ግን የማንጣጣምባቸውና የማንስማማባቸው ነገሮች ይኖራሉ:: እነዚህም በምርጫችን ላይ ነቀፌታ እና ችግር እንዳያመጡብን በመረጥነው ሰው ሙሉ በሙሉ የተስማማን መሆናችንን ራሳችን ለራሳችን ማረጋገጥ ይገባናል::

5ኛ/ የመረጥናቸውን የትዳር ጓደኞቻችንን ሁኔታ ያለምንም ማጋነን መመርመር አለብን ምክንያቱም ነገ አብሮ መኖር ከተጀመረ በኋላ ዓይናችን ሲገለጥ ሌላ ችግር እዳይፈጥርብን ነው:: ብዙ ሰዎች የፈለጉት ሰው እጃቸው እስኪገባላቸው ድረስ ዐውቀውትም ይሁን ሳያውቁት በጣም ያጋንናሉ::





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

«አንተን የመሰለ ሰው አንቺንም የመሰለ ሰው የለም።» ይባባላሉ። ይሁን እንጂ የፈለጉትን ካገኙ ያለሙትንም ከፈቱ በኋላ ግን ያ የነበረው ማጋነን ሁሉ እንዳልነበረ ይሆናል። ቀጥሎም «እንደዚያ አድርጌ ያጋነንኩት ያገነንኳት ምን ሆኜ ነው?» ማለት ይከረላል። በመጨረሻም መቃቃርና አለመስማማት ይመጣል። «ድሮውንም ቢሆን እጅህ እስክታስገባኝ ነበር፤ እጅሽ እስክታስገቢኝ ነበር።» የሚለው ጭቅጭቅ ይነግሣል። ስለሆነም አጉል ማጋነንን ትቶ ደካማ ጉንን በመግለጥና በመተማመን መፍትሔውን ከአሁኑ መሻት ያስፈልጋል።

6ኛ/ ውሳኔያችን ከማኅበረሰባችን ባህል አለመውጣቱን ማረጋገጥ መልካም ነው። ለምሳሌ «ቤተሰብ ፈቀደ አልፈቀደ፣ሽማግሌ ተላከ አልተላከ፣ የምሥራች ተሄደ አልተሄደ፣ ጥሎሽ ተላከ አልተላከ ፣ወዘተ… ምንድነው?» ብለን ትዳር ለመመሥረት መነሣት አይገባም። ምክንያቱም ይዋል ይደር እንጂ በትዳር ውስጥ ጭቅጭቅና ንዝንዝ መፍጠሩ አይቀርም። በሌላ በኩልም ከክርስትናችን ጋር የማይጋጩ የሀገራችን ባህሎች የእኛነታችን ምልክቶች መሆናቸውንም መርሳት የለብንም።

7ኛ/ ከሁሉም በላይ ከሰው ፍጹምነት መጠበቅ የለብንም። ምክንያቱም እኛም ብንሆን ፍጹማን አይደለንምና። ፍጹምነትንም መጠበቅ በሃይማኖት ብቻ ነው። የቀረ ይቀራል እንጂ በሃይማኖቱ ሕጸጽ ያለበትን ሰው መምረጥ እና አብሮ ለመኖርም መወሰን አይገባም። ከምግባር ሕጸጽ ግን ማንም ቢሆን ነፃ ሊሆን ስለማይችል «ለምን ይሆናል?» ማለት የለብንም።

እነዚህን ከላይ የዘረዘርናቸውን ቁምነገሮች በማጤን የምንወስናቸው ውሳኔዎች መልካምነታቸው ለማንም የሚያጠራጥር አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ግን ነገሮችን ሳናመዛዝን አንዱን ወገን ብቻ በመከተል የምንወስናቸው ውሳኔዎች ትልቅ ችግር ሊያመጡብን ይችላሉ። እነዚህም:-

1ኛ/ የትዳር ጓደኞችን መንፈሳዊነት ብቻ ተመልክተን ሌሎች ወሳኝ ነገሮችን ሳናጤን ልንወስን እንችላለን። ይሁን እንጂ ዛሬ ትኩረት የነፈግናቸው እነዚህ ነገሮች ምበነገው ግንኙነታችን ላይ እንቅፋት ሊፈጥሩብን ይችላሉ። ለምሳሌ የዕድሜ መበላለጥ፣ የእውነተኛ ፍቅር አለመኖር፣ራስን ለማሸነፍ የገንዘብ አቅም ማነስ፣የጤና መታወክ፣ ወዘተ…ናቸው።

*ሀ. የዕድሜ መበላለጥ*

በዕድሜ መበላለጥን እንደ ቀላል የሚቆጥሩ ሰዎች አሉ፤ ይሁን እንጂ በዕድሜ በሚበላለጡ ሰዎች መካከል የአስተሳሰብ ልዩነቶች ይፈጠራሉ። ስለሆነም በአስተሳሰባቸውና በፍላጎታቸው ተግባብተውና አንድ ሆነው አብሮ ለመኗዝ በዕድሜ እንዲሁም በዕውቀት የመመጣጠኑ ጉዳይ እጅግ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ሥጋ ደካማ ስለሆነ ነገ ተነገ ወዲያ መናናቅ ሊመጣ ይችላልና። በነገሮች ካለመግባባት የተነሣም «አንተ ማይም፣አንቺ ማይም»መባባል ይነግሥና ትዳራቸውን ገሀነም ያደርገዋል።

*ለ የእውነተኛ ፍቅር አለመኖር*

የእውነተኛ ፍቅር አለመኖርም በራሱ ችግር ነው። ምክንያቱም በመካከላቸው እውነተኛ ፍቅር ሳይኖር በተለያዩ ተፅዕኖዎች ትዳር የሚመሠርቱ ሰዎች መተሳሰብ ይጐድላቸዋል። መተሳሰብ ሲጐድል ደግሞ መተማመን ይጠፋል። እውነተኛ ፍቅር ሲባልም ፈቃደ ሥጋ ከተፈጸመ በኋላ ወደ ጥላቻ የሚለወጥ አምኖናዊ ፍቅር ወይም ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ዝላይና ዝሙት አይደለም። መተሳሰብ ያለበት የአብርሃምና የሣራ፣ የሐናና የኢያቄም፣ የይስሐቅና የርብቃ፣ የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ፍቅር ነው።

*ሐ የአቅም ማነስ ?*

የሰው ልጅ ኑሮውን ለማሸነፍ ወጥቶ ወርዶ በወዙ የሚያገኘው ገንዘብ ያስፈልገዋል። ለዕለት ጉርስና ለዓመት ልብስ የሚሆነውን ጥሮ ማግኘት አለበት። ለቤት ኪራይ፣ ለውኃ፣ ለመብራት እና ለልጆች ማሳደጊያ የሚሆን የገንዘብ አቅም ለማግኘት ሥራን ሳይንቁ መጣጣር ይገባል። አለበለዚያ ግን በስንፍና ተጀቡነው ከሰማይ መና መጠበቅ የዋሕነት ነው። ከዚህ አንጻር ወደ ትዳር ዓለም ለመግባት የምናቅድ ሰዎች በቅድሚያ አቅማችንን ማወቅ አለብን። የመጨረሻ ውሳኔ ከመወሰናችን በፊትም ምንም ይሁን ምን እንደ አቅማችን መኖርን በጸጋ ለመቀበል የሚችል የተዘጋጀ ልብ ያስፈልገናል። አለበ ለዚያ ግን ከገባንበት በኋላ ከአቅም በላይ ለመኖር በምናደርገው ትግል የአቅም ማነስ ይገጥመንና ችግር ውስጥ እንወድቃለን።

*መ. የጤና መታወክ ከሁለቱ አንደኛው በሽተኛ ሊሆኑ ይችላሉ።*

በሽታውም በጠበልም ሆነ በሕክምና ሊድንም ላይድንም ይችላል። ታዲያ የሚድነውን ወጥቶ ወርዶ አስታምሞ ለማዳን፣ የማይድነውን ደግሞ ተሸክሞ ለመኖር መዘጋጀት ያስፈልጋል። አለበለዚያ ዛሬ በስሜት ከገቡበት በኋላ በሽታውን በሽታዋን መሰልቸት ይመጣና ችግር ይፈጠራል።

እንግዲህ ከመንፈሳዊነቱ ጋር ዕድሜውን፣ የፍቅሩን፣ የአቅሙንና የጤናውንም ነገር አብሮ መመልከት ያስፈልጋል። ስለሆነም «ይኸንን ሁሉ እችለዋለሁ? ወይስ አልችለውም?» ብለን እኛነታችንን መመዘን አለብን።« ኃይል በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችለዋለሁ።» ፊል 4÷13። የሚለውን እየጠቀስን የጥቅስ አንበሶች ብቻም ሆነን መገኘት የለብንም። «በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤» ይላልና።2ኛ ቆሮ 13÷5።

2ኛ/ በስሜት ተነድተን በዓይናችን ፊት መልካም መስሎ የታየን ብቻ እንፈጽማለን። መንፈሳዊና ማኅበረሰባዊ እሴቶችንም ዘንግተን በይድረስ ይድረስ እንወጥናለን። በኋላም በመንፈሳዊውም ሆነ በማኅበረሰባዊ አኗኗራችን እንቅፋት ያጋጥመናል። ለምሳሌ «እግዚአብሔርን እላታለሁ ወላሂ ትለኛለች አምናታለሁ፣ታምነኛለች» ብሎ የሃይማኖትን አንድነት ሳይጠብቁ የሚመሠረት ትዳር፤

3ኛ/ እንዳንዶቻችንም ትዳር ስንመሠርት ከላይ በመግቢያው ላይ ለመጠቆም እንደሞከርነው የምናገኘውን የገንዘብ ጥቅም ብቻ በማውጠንጠን ነው። ይህም ወደ ገንዘብ ድርድር ውስጥ ያገባንና ሕይወታችንን ገሃነም ያደርገዋል።

ስለሆነ ክርስቲያኖች በውሳኔ አሰጣጥ ወቅት ጥንቃቄ መውሰድ እንደሚገባን ከላይ ካቀረብነው ዝርዝር ለመረዳት ይቻላል። ለዚህም ራስን በጸሎት መወሰን ትልቅ ድርሻ አለው። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚሰጠን በሙሉ የሚበጀንና መልካም ነውና። ሮሜ 12÷2። በጸሎታችንም ጊዜ እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ አንዳች ለውጥ እንዲያመጣ ስንጠይቀው ሁሉን ለበጎ ያደርግልናል። ሮሜ 8÷28። ጠቢቡ ሰሎሞን «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤ እርሱም ጐዳናህን ያቀናልሃል።» ያለው ይኸንኑ የሚያጠይቅ ነው። ምሳ 3÷5። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን።





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



# «'ትንሽ' የሚባለውን ሥራ ያላከበረ 'ለትልቁ' አይበቃም......»

ከቀሲስ ኃ/ገብርኤል ዘሐና



ከአዳም ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ የነበሩ ሁሉ «በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ።» በተባለው ትእዛዝ መሠረት በእግዚአብሔር አጋዥነት የዕለት እንጀራቸውን ለማግኘት እንደየችሎታቸው ሲሠሩ ቆይተዋል፤ ዛሬም በመሥራት ላይ ይገኛሉ። ዘፍ3÷19። በተለይም ባለንበት ክ/ዘመን በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ሥራ ያለውን ታላቅ ድርሻ መግለጹ ለቀባሪ የማርዳት ያህል ነው።

ዛሬ ሁሉም ሥራ ይፈልጋል። ግን ምን ዓይነት ሥራ? ብዙዎችን በሥራ አጥነት ስንስለት ያሠረው ይህ ጥያቄ ነው። ማንም ቢሆን ለመኖር መሥራት እንዳለበት ያምናል፤ የሰው ዝንባሌም ብቻ ሳይሆን አምላካዊ ትእዛዝም ነው። ቅዱስ ጳውሎስም እያንዳንዱ ሰው መሥራት ግዴታው እንደሆነ «ሊሠራ የማይወድ አይብላ፤» በማለት ይገልጣል። እንዲሁም ቀድሞ የነበሩ አበው በሙሉ ምንም ቅሩብ እግዚአብሔር ቢሆኑም ጊዜአቸውን ያሣለፉት በሥራ ነው። መጽሐፍ «የእንቅልፍ ብዛት የተበጫጨቀ ልብስ ያስለብሳል።» እንዲል በንዋመ ሀኬት /በስንፍና እንቅልፍ/ ተይዘው ሥራ ፈት በመሆን በአእምሯቸው ክፉ ሐሳብ እንዳይመላለስ እራሳቸውን በሥራ ጠምደው ኖረዋል። ለዚህም የጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖትን ገድል መጥቀሱ በቂ ነው።

እውነታው ይኼ ከሆነ በአካባቢያችን ሊገኙ የሚችሉ ሥራዎችን መናቅና «መሥራት አለብኝ፣ ይገባኛል» የምንላቸውን ሥራዎች መወሰን ሥራ የማግኘት ዕድላችንን እንደሚያጠበው ማወቅ አለብን። ዋናው ቁምነገሩ የሥራው በሰዎች ዘንድ መናቅ ሳይሆን ከኃጢአት መንሥኤነት የራቀና ለኑሮአችን የሚያስፈልገንን ለሟሟላት መቻሉ ነው። ሊቀ ነቢያት ሙሴ በንጉሥ ቤት ማደጉን አስቦ ሥራን ሳይንቅ የዮቶርን በጐች መጠበቅን ወደደ። ዘጸ3÷1። የእሥራኤል ንጉሥ የነበረውና እግዚአብሔር «እንደልቤ» ብሎ የተናገረለት ቅዱስ ዳዊትም አስቀድሞ የበጐች እረኛ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል። 1ኛ ሳሙ 16÷11።

ዛሬ አንዳንዶች «የተናቀ» የሚሉትን ሥራ መሥራት ራሳቸውን ከክብራቸው ማዋረድ፣ ዕድላቸውን መስበር፣ የተማሩትን ከንቱ ማድረግ መስሎ ይታያቸዋል። ይህ አመለካከት ታላቅ ስህተት ነው። ከላይ የተመለከትናቸው አበው ታሪክ እንደሚያስተምረን ያገኙትን ሥራ ሳይንቁ መሥራታቸው ከታላቅነታቸው አላሳነሣቸውም። በዘመናችንም በጊዜያዊ ችግር ተገፋፍተው ለክፉ ድርጊት ሳይሰለፉ ማንኛውንም ዓይነት ሥራ እየሠሩ ከእግዚአብሔር ቤት ሳይርቁ እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩ ብዙ ወጣቶች ይገኛሉ። ከነዚህም በአዲስ አበባ ተወልዳ ያደገችው የ23 ዓመቷ ወ/ት ትዕግሥት አበበ እና በእንድብር ተወልዶ አዲስ አበባ ያደገው የ18 ዓመቱ ወጣት በረከት በረዳ የሚጠቀሱ ናቸው።

ትዕግሥት አበበ ከልጅነቷ ጀምሮ ሕመምተኛ እናቷን እያስታመመች ቤተሰቧን በማስተዳደር ያደገች ናት። ሴትነቷ ለችግር ሳያንበረክካት ቆሎ እየሸጠች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በ1985 ዓ.ም በኮከበ ጽባሕ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቅቃለች። ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ ጋዜጣ በማከፋፈልና በማዞር ለደንበኞችም በማደል በምታገኘው ገቢ ቤተሰቧን ታስተዳድራለች። ይህን ሥራ እንዴት እንደጀመረች ስናትናገር «እኔ ሥራ ላግኝ እንጂ ምንም የምንቀውና የምጠላው፣የወንድና የሴት ብዬም የምለየው የለኝም። በመሆኑም ኑሮን ለማሸነፍ ቀደም ሲል ቆሎ እሸጥ ነበር። ለቤተሰቤም ሆነ ለትምህርት ቤት ወጪ የማገኘው ከዚሁ ስለሆነ በብዛት እየቆላሁ ለአዟሪዎች እና ወደ ውጪ ለሚልኩ ሰዎች አቀርብ ነበር። የጋዜጣውንም ሥራ የጀመርኩት የግል ጋዜጦች መውጣት እንደጀመሩ ነው። ከቆሎ መሸጡ ይህ ይሻላል በማለት ጀመርኩት።ሌሊት 11:00 ወደ አዘጋጆቹ ሄጄ በብዛት እረከብና ለአዟሪዎች አከፋፍላለሁ። እግዚአብሔር ይመስገንና ቤተሰቤን ለማስተዳደር በቂ ነው ለማለት እችላለሁ» ትላለች።

ከዳር ሆነው ሲመለከቱት የትዕግሥት ሥራ ከባድ መስሎ ይታያል። ነገር ግን «ዛሬ ጉልበት እያለኝ ሠርቼ ራሴን ያልቻልኩ መቼ ልሠራ ነው?» በማለት የተነሣ የሚመጣው ጭንቀትና ተስፋ በመቁረጥ ራስን የኃጢአት ተገዥ ማድረጉ ነው። ሥራ በፊታ አእምሮ ብዙ ነገሮች እንደሚታሰቡእሙን ነውና። እግዚአብሔር ያልወቀሰውን ማንሣት ባይገባም። በትህትናውና በተነሣሒነቱ የሚታወቀው ቅዱስ ዳዊት በሐፀ ዝሙት ሊነደፍና በአንድ ጊዜ ተደራራቢ ብደልን በእግዚአብሔር ፊት ሊፈጽም የቻለው ቀድሞ ያደርግ የነበረውን መልካም ምግባር ትቶ ከታቦተ ጽዮንና ከሠራዊተ እሥራኤል ተለይቶ ቤት በመዋሉ ነው። /2ሳሙ 11÷2–27/። ራስን በሥራ ወስኖ እንደ እግዚአብሔር ቸርነት በመልካም ክርስቲያናዊ መንገድ መጓዝን የካዛንችሱ ሊስትሮ በረከት በረዳ ከልምዱ በመነሣት «እስከ ዛሬ ስምንት ዓመት ድረስ ምንም ችግር አልነበረብኝም።የሚያሳድጉኝ እናት ለዕለታዊ ፍላጎቴም ሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወቴ የሚያስፈልጉኝን ሁሉ ያሟሉልኝ ነበርና። ትምህርቴን እማራለሁ፣ ለቅዳሴም ሆነ ለሠርክ ጉባኤያት ቤተክርስቲያን ሲሄዱ አልለያቸውም ነበር። ይህ ለዛሬው እኔነቴ በብዙ ጠቅሞኛል። የዛሬ 8 ዓመት ቢያርፉም ተስፋ አልቆረጥኩም። ከእግዚአብሔር እና ቅዱሳኑ ቀጥሎ በሁሉ የሚደርስልኝ ሌላ ሳይሆን ራሴ መሆኔን ተገነዘብኩ። በአቅሜ መሥራት የምችለውን ሊስትሮነት





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ጀመርኩ:: ብዙዎች ሊስትሮነትን ይንቁታል:: በኔ አስተሳሰብ አንዳንዶች እንደሥራ ከያዙት ከሌብነት በቀር የሚናቅ ሥራ የለም:: «ለዕድሌም አላሰየው» በሚል ግብዝነት መለከፍ ለተስፋ መቁረጥና ለድህነት ይዳርጋል:: «ለከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ እና ራስን ለማሻሻል ጊዜን በሥራ ማሳለፍ ከኃጢአት ያርቃል:: ከተጉ ግን አንድ ቀን ካሰቡበት መድረስ ይቻላል::» በማለት ይናገራል:: በማኅበራዊ ሕይወትም በኩል አንድ ክርስቲያን ከሌላው ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት እንዲህ ይላል::

«ሰው ብቻውን አይኖርም፤ በተለያየ መንገድ ከሰዎች ጋር ይገናኛል:: እውነትን ካላወቀና ስለ እውነት ካልኖረ ሰዎችን ልምሰል በማለት ራሱን ሊጎዳ ይችላል:: ይህ ስህተት ነው:: ለምሳሌ ከኔ ጋር የሚውሉ የሥራ ጓደኞቼ በእምነት አይመስሉኝም፣በምግባርም እንለያያለን:: ሥራ ስላገናኘን የግድ በእምነት፣ በምግባርም ከሰው ላለመለየት ብዬ ራሴን መጉዳት የለብኝም:: ሥራ ፈትተው አላፊ አግዳሚውን የሚተናኰሉም ሞልተዋል፤ «ፋራ» ላለመባል ዘመኑ ያመጣውን ሁሉ መሥራት እንደማይገባኝ እረዳለሁ::»

ሥራ በመናቃቸው የተነሣ በችግር ተይዘው ከእምነታቸው የሚለዩ ወጣቶች የትዕግሥትና የበረከት ሕይወት አርአያ ሊሆናቸው ይገባል:: ከ1985ዓ.ም ጀምሮ የሠርክ ጉባኤያትን በኋላም በሰንበት ት/ቤትና በአካባቢዬ የሚገኙ የጽዋ ማኅበራት እየተሳተፍኩ ነው::

ሥራዬ ፋጫ የበዛበት በመሆኑ ሰፊ ጊዜ የለኝም:: ይህ በሰንበት ት/ቤት በስፋት ለማገልገል ባያስችለኝም በቅርቡ በቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በሚሰጡት ኮርሶች ላይ ከመሳተፍ አላገደኝም:: እንዲያውም ችግር ሲደርስብን ግራ መጋባትና ከቤተክርስቲያን መራቅ ሳይሆን የድሆች መጠጊያ ወደሆነችው ቤተክርስቲያን በመቅረብ ኃዘናችንን፣ መግለፅ እንደሚገባ ተምሬያለሁ፤ ትላለች ትዕግሥት::

በርግጥ በዓለም ስንኖር በየጊዜ የሚፈጠሩ ችግሮች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሊፈትኑን፣ ሊያስጨንቁን ይችላሉ:: ለዚህ ደግሞ መፍትሔ የሚገኘው ከምናምነው ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ነው:: አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርገው በርሱም የሚታመነው ኑሮው በተስተካከለበትና ያሰበውን ባገኘበት ወቅት ብቻ መሆን የለበትም:: በድሎቱ ጊዜ «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም፤» በማለት ሁሉን ቻይነቱን ይናገር የነበረ በመከራ ሰዓት ደግሞ «ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን?» /ኢዮ 1÷10/ ማለት ይገባዋል:: «የመጀመሪያው እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና::» /ዕብ3÷14/ እንደተባለውም ለሞት በሚያደርስ መከራ ብንያዝ እንኳን ከርትዕት ሃይማኖታችን ወደ ኋላ ልንል አያስፈልግም::

«ችግሬንና ሥራዬን ብቻ እያየሁ ከቤተክርስቲያን መራቅ እንደሌለብኝ አምናለሁ፤ ረድኤትን የማገኘው እግዚአብሔር ሥራዬን ከባረከልኝ እንጂ ከቤተክርስቲያን ርቄ ቀን ከሌሊት ስለደከምኩ ብቻ አይደለም:: ምንም እንኳን ደህና ገቢ የማገኘው ቅዳሜና እሑድ ቢሆንም በተቻለኝ መጠን ለቅዳሴ አለያም ለሠርክ ጉባኤ ወደ ቤተክርስቲያን እሄዳለሁ:: ሥራዬን፣ ኑሮዬን ምክንያት አድርገው ያዘኑልኝ በመምሰል የሚያባብሉኝ ብዙ መናፍቃን አሉ:: «ወደኛ ብትመጣ ሥራ እናስገባሃለን::» በማለት የሞት ግብዣ ያቀርቡልኛል:: እምነት እኮ የዘላለም ሕይወት፣ የምታስገኝ እንጂ በምድራዊ ክብርና ሀብት የምትለወጥ አይደለችም፤» የሚለውን የበረከት በረዳ ምክር ብዙ ነገር እንድናስተውል ያሳስበናል::

ሐዋርያው «ሥራ ከቶ ሳይሠሩ በሰው ነገር እየገቡ ያለሥርዓት ከናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለአንዳንዶች ሰምተናልና::... እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ::» ብሎ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በቃልም በግብርም አስተምሯል::/ተሰሎ3÷6–13/ አባቶቻችንን መምሰል ያለብን በሃይማኖት ብቻ ሳይሆን በምግባራቸውም ጭምር ነው:: «እንግዲህ እኔን የምትመስሉ ሁኑ ብዬ እለምናችኋለሁ::» /1ቆሮ 4÷16/ ተብለናልና::

ትዕግሥት «እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ራሴንና ቤተሰቤን በሚገባ ለማስተዳደር ያገኘሁትን እየሠራሁ ያለሁበትን የኑሮ ደረጃ ማሻሻልና በሚቻለኝ ሁሉ ቤተክርስቲያንን ማገልገል የወደፊት ዓላማዬ ነው::» ትላለች:: በረከትም በበኩሉ የወደፊት ዓላማው የተሻለ ሥራ ይዞ ቤተሰቦቹን ከአሁኑ በበለጠ መርዳት፣ ትምህርቱን መቀጠልና ስለ ሃይማኖቱ በስፋት ተምሮ ቤተክርስቲያንን ማገልገል እንደሆነ ገልጧል::

በመጨረሻም«'ትንሽ' የሚባለውን ሥራ ያላከበረ 'ለትልቁ' አይበቃም:: ሥራን በመናቅ በብዙ ድካም ሀብት፣ንብረቱንና ጉልበቱን ጨርሶ በአስተማሪ ወላጅ ላይ ሸክም ከመሆን ያገኙትን ሠርቶ ራስንም ሆነ ቤተሰብን መርዳት ታላቅነት ነው:: በተጨማሪም እያንዳንዱ ወጣት ወደቤተክርስቲያን ሄዶ ቢማር የሥራ ፍቅር ያድርበታል:: ምክንያቱም ቃለ እግዚአብሔር የሥራን ክቡርነት ያስገነ ዝባልና::» ሲል በረከት መልእክቱን ለወጣቶች ያስተላልፋል:: ትዕግሥት አበበ ደግሞ «ከኃጢአት በቀር ማንኛውንም ዓይነት ሥራ መሥራት ኃጢአት እንዳልሆነ ወጣቶች ዐውቀው ሥራን ባይንቁ መልካም ነው:: እንዲሁም አንዳንድ ወጣቶች ስንፍናቸውን በመንፈሳዊ ነታቸው እያመካኙ ለመንፈሳዊ ሕይወቴ ስለማይመች መሥራት አልችልም፤ በማለት ሥራ ሲያማርሩ ጡና ሲቸገሩ ይታያል:: ይህ ግን ትክክል አይደለም:: መንፈሳዊ መሆን የበለጠ ያተጋል እንጂ የስንፍና ምክንያት ሊሆን አይገባም:: በዚያ ላይ ደግሞ ተለፍቶ የሚገኝ ነገር ሁሉ ስለሚያረካ ቁጭ ብሎ ከመመኘት ከኃጢአት በቀር ያገኙትን ሠርቶ ራስን መቻል ያስደስታል:: ስለዚህ ወጣቶች ሥራ ቤታቸው ድረስ እንዲመጣላቸው መጠበቅ ሳይሆን እነርሱ ወደ ሥራ መሄድ እንዳለባቸው ሊያውቁ ይገባል::» በማለት አበክራ ትመክራለች::

«አንተ ታካች /ሰነፍ/ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ መንገዷንም ተመልክተህ ጠቢብ ሁን:: አለቃና አዛዥ ገዢም ሳይኖራት መብልዋን በበጋ ታሰናዳለች:: መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች:: አንተ ታካች እስከመቼ ትተኛለህ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ? ... እንግዲህ ድህነ ትህ እንደ ወንበዴ ችጋርህም ሰይፍ እንደታጠቀ ሰው ይመጣብሃል::» እንዳለ ጠቢቡ ለሥራ እንትጋ::

*የትጉኀን አምላክ እግዚአብሔር የሥራን ፍቅር ያሳድርብን::*





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መፍትሔ «ለመፍትሔ አልባው»

ከግርማ ወ/ሩፋኤል

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሰው ልጅ አንድም በራሱ አልፎ አልፎም በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ለተለያዩ ችግሮች ሲዳረግ ኖሯል። በተለይም ከፍተኛ እልቂት ከሚያደርሱ በትና ከባድ የታሪክ ጠባሳን ጥለውበት ከሚያልፉት መካከል ኤድስን የመሳሰሉ በየጊዜው በወረ ርሽኝ መልክ የሚ ነሡበት በሽታ ዎች ዋንኞቹ ናቸው።

በዘመናችንም የኤድስ ቫይረስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከታወቀበት ጊዜ አን ሥቶ እስከአሁን ድረስ በመላው ዓለም ከ20 ሚሊዮን የሚበልጥ ሕዝብ እንደለከፈና በጽኑ የታመሙትም ከ1.6 ሚሊዮን በላይ መሆናቸውን ዘገባዎች ያስረዳሉ። ከነዚህም ውስጥ ከግማሽ በላይ እንደሞቱ ይገመታል። በዚምባቡዌ ብቻ እንኳን በሳምንት እስከ 500 የሚደርሱ ሰዎች ይረግፋሉ። ከዚህም ሌላ የበሽታው ሰለባ የሆኑት ሕፃናት ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። የዚህ ዓመት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሪፖርት እንደሚያመለክተው በዓለማችን ከዘጠኝ ሚሊዮን የሚልቁ ሕፃናት በኤድስ ሰበብ ወላጅ አልባ ሆነዋል። ይህም እናት አልባ ከሆኑት ከፍተኛ ደረጃ ደርሻለሁ ባለችበት ዘመን መድኃኒት አልባ መሆኑ የሚጠቀሱ ናቸው። እንዲያውም የበሽታውን መዛመት ይቀንሳሉ ተብለው በየመገናኛ ብዙኀኑ የሚነገሩት የኮንዶምን ማስታወቂያ የመሳሰሉት ነገሮች በሽታውን የሚያባብሱት ሆነው መገኘታቸውም ሌላው ችግር ነው። ይህን ያህል ኤድስን በዓለም ሁሉ ተዛምቶ ለቁጥጥር አስቸጋሪ እስከመሆን ያደረሰውና መፍትሔ አልባ ያደርገውም የሰው ልጅ ራሱን በመግዛት ፈንታ ከሕገ እግዚአብሔር ርቆ ወደ ሌላ መፍትሔ ማድላቱ ነው። በመገናኛ ብዙኀን እንደሚሰጠው የትምህርት ብዛትና የማስታወቂያዎች ጋጋታ ቢሆን ኖሮ እስከ ዛሬ ድረስ ኤድስ ከዓለም በጠፋ ወይም ባለበት በቆመ፤ አለያም የመዛመት ፍጥነቱ በተገታ ነበር። ይባስብሎ በጆሮ ይተላለፍ ይመስል፤ የበለጠ ፍጥነቱን ጨምሯል። በተባበሩት መንግሥታት የቅርብ ጊዜ ሪፖርት መሠረትም ስርጭቱ በዓመት 18 በመቶ ማደጉ ይህንኑ ያመለክትል። ለዚህ መፍትሔ አልባ ለሆነው በሽታ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ከመበላሸቱ የተነሣ ከሀገርና ከወገን ፍቅር ይልቅ ለገንዘብ ፍቅር ተገዛ፤ ለራሱ የሆነውን ሁሉ እያንቋሸሸ በመጣል የሌሎችን ኑሮ መኖር ወደደ፤ በሀገሩ ሠርቶ ከመኖር ይልቅ ስደትንና ልመናን መረጠ፤ ጨዋነትና በሥርዓት መኖርም ቀርቶ ልቅነትና ሥርዓት አልበኝነት ተስፋፋ። በዚህም የኤድስ መናኸሪያ ለመሆን በቃን።

በመሆኑም በየመገናኛ ብዙኀኑ የኮንዶምን ጥቅም ከመስበክና፣ የኤድስ ቀን መታሰቢያ እያሉ ዳንስንና ዘፈንን አሳይቶ የወጣቱን ሥጋዊ ፍላጎት ከመቀስቀስ ይልቅ ሕዝቡ ባሕርይውን እንዲለውጥ ማስተማር ይበጃል። በተለይም ሕፃናትን ከሥር ጀምሮ በግብረ ገብ ትምህርት እየኰተኰቱ ማሳደግ ያስፈልጋል። ትውልዱ ተጣሞ ካደገ በኋላ ለማቃናት ከመቸገር፣ከቤተሰብ ጀምሮ በትምህርት ቤቶችና በመገናኛ ብዙኀንም ጭምር የግብረ ገብ ትምህርቶችን ማስጠት ይገባል። በሥነ ምግባር ታንጾ ያደገ ትውልድ የሀገርና የወገን ፍቅር ይኖረዋል፤ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሃይማኖቱንም አክባሪ ይሆናል። ለአልኮልና ዕፅ ሱሰኝነትም አይጋለጥም።

ጠቅላላ ሕፃናት መካከል 97% የሚሆነውን ይይዛል።

ኤድስ በሃገራችንም መኖሩ ከታወቀበት ከ15 ዓመታት ወዲህ እስከ ዛሬ ከተማን ከገጠር ሳይለይ እያዳረሰና በተለይም ወጣቱን በለጋ ዕድሜው እየቀጨው ይገኛል። ምንም እንኳን በትክክል መናገር ባይቻልም በኤድስ ቫይረስ /HIV/ የተለከፉት ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከአንድ ሚሊዮን እንደሚበልጥ ይገመታል። በ1994ዓ.ም እ.ኤ.አ የተደረገ አንድ ጥናትም አብዞኞቹ የቫይረሱ ተሸካሚዎች ለጋ ወጣቶች መሆናቸውን ያመለክታል። ከአጠቃላዩ ሕዝብ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዙት ከ20–29 የዕድሜ ክልል ያሉ ሲሆኑ፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከ30–39 ውስጥ ያሉት ናቸው።

ኤድስን ትናንትናና ከትናንት በስቲያ በወረርሽ መልክ ተከስተው ብዙ ሕዝብ ከፈጁት በሽታዎች ለየት የሚያደርጉት ብዙነገሮች አሉ። ከነዚህም መካከል የሰው ልጅ ከሕገ እግዚአብሔር ስለራቀ ራሱን መግዛት በተሳነው ዘመን መነሣቱ፣ ዋንኛው መዛመቻውም ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መሆኑ፣ የየሃገሮቹን አምራች ኃይል የበለጠ ማጥቃቱ እና ዓለም በሥልጣኔ

*1.ሕዝቡ የምግባር ለውጥ እንዲያመጣ ማስተማር*

ዓለም በተለያዩ ነገሮች ሊጠቃና ኤድስም ይህን ያህል ተስፋፍቶ ለቁጥጥርም አስቸጋሪ እስከመሆን የደረሰው በሰው ልጅ የሥነ ምግባር መበላሸትና ሥርዓት የለሽ መሆን የተነሣ ነው። የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር እየራቀና ለመንፈሳዊ ነገሮች ትኩረት እየነፈገ ሲሄድ የማይገቡ ሰይጣናዊ ሥራዎችን መፈጸሙ የማይቀር ነው። «እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤»ሮሜ 1÷28። በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ በተፈጠረ ክቡር ፍጡር ይፈጸማሉ ተብለው የማይታሰቡ ወንጀሎች ጋር በዓለማችን መበራከት፣ ዝሙትን ከእንስሳት ባልተሻለ ሁኔታ መፈጸም፣ በአልኮልና አደንዛዥ እጾች ሱሰኝነት ተጠምዶ የሚያደርጉትን አለማወቅ፣ ወዘተ... የዚህ ውጤቶች ናቸው።

በሀገረ እግዚአብሔርነቷ ትታወቅ የነበረችው ሀገራችንም ለነገረ እግዚአብሔር ትኩረት ባለመስጠቷ የዚህ አስከፊ ኑሮ ተቋዳሽ ለመሆን በቅታለች።ተሰሎ.4÷2–8። ትውልዱ ከቃለ እግዚአብሔር ከመራቁና በሥነ ምግባር ራሱን የገዛና ትዳሩንም አክባሪ በመሆን ከኤድስም ይጠበቃል።

በተለይም ቤተክርስቲያን ከሙዓለ ሕፃናት ጀምሮ የራሷ የሆኑ ትምህርት ቤቶች ቢኖሯትና የንስሐ አባቶችም ከወላጆች ጋር በመመካከር ለሕፃናት ትኩረት በመስጠት በሰንበት ት/ቤት ታቅፈው ቃለ እግዚአብሔርን እየተመገቡ የሚያድጉበትን መንገድ ቢያመቻቹ የወደፊቱን ትውልድ ከኤድስ መታደግ ይቻላል። እንዲሁም ለሕዝቡ በሥነ ምግባር መበላሸት ዋነኛ ምክንያት ከቅድስት ቤተክርስቲያን መራቅ እና የንስሐ አባቶችና የልጆቻቸው ግንኙነት መላላት መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ንስሐ አባቶች የልጆቻቸውን ክርስቲያናዊ ሕይወት በቅርበት በመከታተል ከቃለ እግዚአብሔር ከንስሐ ሳይርቁ በሥጋ ወደሙ ተወስነው እንዲኖሩ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ልጆችም ንስሐ አባቶቻቸውን በዓመት አንድ ጊዜ ለጸበል መርጨት ብቻ በመፈለግ ፈንታ ሊቀርቧቸውና በሀዘናቸው፣ በችግራቸውና በደስታቸው ጊዜ ሁሉ ማማከር ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ምእመናን በጸሎት፣ቅዱሳት መጻሕፍት በማንበብና በልዩ ልዩ የቤተክርስቲያን ሥራዎች ብንሳተፍ የተቀመጠን ኀሊና ኃጢአትን ከማሰብ በቢታነው ነበር።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

*2. ወጣቱን ለዝሙት ከሚገፋፉት ነገሮች መጠበቅ*

በዓለማችን ወጣቱን ለተለያዩ ችግሮች እንዲጋለጥና በኤድስም የበለጠ እንዲጠቃ ያደረገው ወደ ጥፋት በተለይም ወደ ዝሙት የሚገፋፉት ነገሮች መበራከታቸው ነው:: በመሆኑም ወጣቱን ለእንደዚህ ዓይነት ነገሮች እንዳይጋለጥ መታደግ ኤድስን ከምንጩ ማድረቅ ይሆናል::
ስለዚህም:–

*ሀ. ልቅ ወሲብን የሚያስፋፉ /Pornography/ ነገሮችን መቆጣጠር*

ወጣቶች በለጋ ዕድሜአቸው የሚመለከቷቸው፣ የሚሰሟቸውና የሚያነቡአቸው ነገሮች በሕይወታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድሩባቸዋል:: ያዩትን፣የሰሙትን ወይም ያነበቡትን ሁሉ ማድረግ ስለሚወዱና መሞከርም ስለሚፈልጉ ለችግሮች የመጋለጣቸው እድል የሰፋ ነው:: ከዚህ አንፃር ልቅ ወሲብን የሚያስፋፉ የቪዲዮ ካሴቶችና ፊልሞች፣መጻሕፍት፣መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ሥዕሎች፣ማስታወቂያዎች፣ ዝሙትን የሚቀሰቅሱየሙዚቃ ካሴቶች ፣ ወዘተ...ለኤድስ መስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው ማለት ይቻላል::

በተለይም በአንዳንድ አገሮች ልቅ ወሲብን የሚያስፋፉ ነገሮች /Pornograhpic Materials/ እንደነፃነትና የሥልጣኔም ምልክትነት መታየታቸውና ከፍተኛ የገቢ ምንጭም መሆናቸው የበለጠ እንዲስፋፉና ከቁጥጥርም በላይ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል:: በቅርቡ ከኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም በወጡ አገሮች ልቅ ወሲብን የሚያሳዩ ፊልሞች ብዛት እየጨመረ መምጣትም ይህንኑ ያመለክታል:: ለምሳሌ በሀንጋሪ ብቻ በየዓመቱ ከ150 በላይ የሚሆኑ ሕፃናት ጭምር የሚሳተፉባቸው የወሲብ ፊልሞች ይዘጋጃሉ:: ይህም ከአውሮፓ 10% ያህል መሆኑ ነው::

በሀገራችንም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሚታየው የቪድዮ ቤቶች መስፋፋትና የወሲብ ጋዜጦች መበርከት ወጣቱን ወደ ተለያዩ ወንጀሎችና አመንዝራነት እየገፋፋ ይገኛል:: በኤድስ የመለከፉንም እድል የዚያኑ ያህል አባብሶታል:: በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት ነገሮች የኤድስን መዛመት ፍጥነት ከመጨመራቸውም አልፎ ትውልድን እንደሚያጠፉ ታውቆ ከፍተኛ ቁጥጥር ሊደረግባቸው ያስፈልጋል:: እንደከዚህ በፊቱ በየአዳራሹ ለአንድ ሰሞን ብቻ የሚደረገው ማውገዝና ዘመቻ ምንም ዓይነት ለውጥ ሊያመጣ አይችልም:: ወላጆችም ለልጆቻቸው በቤት ውስጥ የሚያሳዩአቸው የቪድዮ ፊልሞች የተመረጡ ለወደፊቱ ሕይወታቸው የሚጠቅሟቸው ቢሆኑ ይመረጣል:: እንዲህ ዓይነት ነገሮችን እንዳይመለከቱ በጉልበት መከልከል ብቻ ዋጋ የለውም:: በሥነ ምግባር ታንፀው የሚያድጉበትን መንገድ ማመቻቸት እንጂ:: ለምሳሌ መንፈሳዊ ፊልሞችን፣ መዝሙሮችን፣ መጽሔትና ጋዜጦችን እንዲያዘወትሩ ማድረግ ውጤት ይኖረዋል::

*ለ. የአደንዛዥ ዕፆችን መስፋፋት መግታት*

ዓላማችንን እያሳሰበ የመጣውና ለአደገኛ ወንጀሎች መበራከትም ሆነ ለኤድስ መዛመት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለ ነገር ቢኖር ከአህጉር አህጉር እየተስፋፋ ያለው የአደንዛዥ ዕፆች ዝውውር ነው:: በተለይም በአሁኑ ሰዓት የአደገኛ ዕፆች ንግድ በፍጥነት እያደገ መምጣትና ገቢውም በዓመት እስከ 400 ቢሊዮን ዶላር መድረስና የአንዳንድ አገሮችና የታላላቅ ከበርቴዎች ዋነኛ የገቢ ምንጭ መሆን ቁጥጥሩን አስቸጋሪ አድርጎታል:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዕፅ ቁጥጥር ፕሮግራም ባወጣው ሪፓርት 5.9 ቢሊዮን ከሚሆነው የዓለም ሕዝብ መካከል 3.3–4.1 በመቶ ያህሉ መደበኛ የአደንዛዥ ዕፆች ተጠቃሚ መሆኑን አስታውቋል:: ከዚህ ውስጥ ለምሳሌ 140 ሚሊዮኑ ሕዝብ የሐሺሽ ተጠቂ ነው:: እንደገናም ከነዚህ ዕጽ ሱሰኞች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ወጣቶች ሲሆኑ የተቀሩትም ቢሆኑ በሱሱ የተጠመዱት ከወጣትነት ጊዜአቸው ጀምሮ ነው::

የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኞች እንደዚህ መብዛት ነፍስ ግድያ፣ዘረፋና አስገድዶ መድፈርን ለመሳሰሉት አደገኛ ወንጀሎች መበራከት ብሎም ለኤድስ በሽተኞች ቁጥር መጨመር ከፍተኛውን አስተዋጽኦ አድርጓል:: ለምሳሌ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሩስያ የኤዲስ በሽተኞች ቁጥር በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ከዚያ በፊት ከነበሩት ዘጠኝ ተከታታይ ዓመታት የበለጠ የሆነው የዕፅና አልኮል ሱሰኞች መብዛት የተነሣ በተፈጠረው ልቅ ወሲብ ነው::

በሀገራችንም የዕፅ ተጠቃሚ ወጣቶች ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ በመምጣቱ ዳንስ ቤቶች፣ በየመንደሩ ያሉ ቪድዮ ቤቶችና ትልልቅ ሆቴሎች ዋንኞች የመገበያያ ሥፍራ ሲሆኑ፣ ሻይ ቤቶች፣ የመንደር ኪዮስኮችና አንዳንድ ቡና ቤቶች ሳይቀሩ ለዚሁ ተግባር ውለዋል:: በዚህም ከሩቅ እንሰማ የነበረውን የአደገኛ ወንጀሎች ዓይነትና ልቅ የወሲብ ኑሮ በቅርቡ ለመመልከት በቅተናል:: በአንዳንድ የአገራችን ትልልቅ ከተሞች የሚታየው የኤድስ ቫይረስ ተሸካሚዎቹ ቁጥር መጨመርም ከዚህና ከሴተኛ አዳሪዎቹ መብዛት ጋር ይያያዛል::

በመሆኑም ትውልዱን ከኤድስ ለመታደግ የአደንዛዥ ዕፆችን መስፋፋት መግታት ያስፈልጋል:: አለበለዚያ በመገናኛ ብዙኃን ከኤድስ መጠበቅ እንዳለበት ብቻ ለወጣቱ ማስተማር ዋጋ የለውም:: በዕፅ የተመረዘ ትውልድ እንኳን ሌላው የሚነግረውን ሊያደርገው ራሱም የሚያስበውን አይተገብረውም:: እርሱ የሚመራው በዕፅ፣ የሚገዛውም ለዕፅ፣እንኳን የማስታወቂያ ማስፈራራት መድፍና መትረየስ ቢተኩስ ጉዳዩ አይደለም:: ስለዚህ ከኤድስ በፊት ዕፅን ለማጥፋት ተረባርቦ መታገሉ ዘላቂ መፍትሔ ይሆናል::

*ሐ. የዳንስ ምሽት ቤቶችን መቆጣጠር*

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገራችን ትናንሽ ከተሞች ሳይቀር እየበዙና በአንዳንዶች ዘንድም የሥልጣኔ ምልክትና የከተማነት መለኪያ እየሆኑ የመጡት የዳንስ ምሽት ቤቶች የዕፅና የልቅ ወሲብ ማስፋፊያ መድረኮች፣ የኤድስም መምረቻዎች ናቸው ማለት ይቻላል:: በተለይ ምንም ባለቤትና ተቆጣጣሪ የሌለ ይመስል በአዲስ አበባ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበሩት የዳንስ ቤቶች ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሕፃናትን ራቁታቸውን ለዝሙት የሚቸረችሩ ቦታዎች እስከመሆን ደርሰዋል:: ሰዎች ወደ እንስሳነት ተለውጠው ኅሊናም ጠፍቶ ዝሙት በየአደባባዩ እየተፈጸመ ምኑን ወጣቱ ከኤድስ እንዲጠበቅ ተመከረ! ባዶ ጩኸት ከንቱ ልፋት! «...ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእምሮው የጐደለ ነው፣ እንዲሁም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል:: ቁስልንና ውርደትን ያገኛል....» ምሳሌ 6÷32–33:: ይልቅስ ለዘለቄታው የኤድስን የመዛመት ፍጥነት ለመቀነስ ከተፈለገ ዳንስ ቤቶችንና ከባሕላችን ውጪ የሆኑ የፋሽን ውድድር ዝግጅትን የመሳሰሉ የዝሙት መድረኮችና ወጣቱንም ወደ ዝሙት የሚገፉፉ ቦታዎችን በመረባረብ ማስወገዱ ይመረጣል::

*3. በፍጹም መተማመን ላይ የተመሠረተ ትዳር*

ለኤድስ መፍትሔ እንዲሆኑ ከሚታመንባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የአንድ ለአንድ ትዳር ነው:: «የአንድ ለአንድ ትዳር» የሚለው ብቻ ከተወሰደ ከዓለም ሕዝቦች ብዙዎቹ ይስማሙበታል፤ አንድ ለአንድ ትዳርም መሥርተው ይኖራሉ:: ነገር ግን ስንቶቹ ለትዳራቸው ታማኞች ናቸው? እርሱ ከእርሷ፣እርሷም ከእርሱ ውጭ ሳይሄዱ የሚኖሩት ምን ያህሉ ናቸው? ስንል እጅግ በጣም ጥቂት ሆነው ይገኛሉ:: የአንድ ለአንድ ትዳሩ በስምና በሕግ አለ፤ በእውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሠረተ ትዳርና መተማመኑ ግን የለም:: ለዚህም ይመስላል ኤድስ





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

«የአንድ ለአንድ» ትዳር መሥርተው የተቀመጡትንም ሳይቀር ለመድፈር የተገደደው:: «ከባለትዳሮች» ውስጥ በኤድስ የተለከፉ መገኘታቸውም ለዚህ ማረጋገጫ ነው::

ስለዚህ የኤድስን መዛመቻ ፍጥነት ለመግታት መፍትሔው በወረቀት ላይ የተቀመጠው «የአንድ ለአንድ» ትዳር ሳይሆን በፍጹም መተማመን ላይ የተመሠረተ በሕገ እግዚአብሔር የጸና ትዳር ሊኖር ያስፈልጋል:: በክርስቲያናዊ ፍቅርና መተማመን ላይ የተመሠረተን ትዳር የቦታ ርቀት፣ የጊዜ ርዝመት፣ማግኘትና ማጣት አይበግረውም፤ ለአምላኩ የሚታመን ክርስቲያን ለትዳሩ መታመን አያቅተውምና!

ሌላው ችግር ከክርስትናው ውጭ ባሉትና በስመ ክርስትና ቢኖሩም የሌሎችን ባሕል በወረሱት ዘንድ ያለው የአንድ ለአንድ ትዳርን መመሥረት አለመቻል ነው:: ሦስትና አራት ከዚያም በላይ የሚያገቡት /Polygamy/ በየጊዜው እያገቡ የሚፈቱት፣ በየሄዱበት ቅምጥ የሚያስቀምጡ ሰዎች የዚህ በሽታ ተጠቂዎች ናቸው::

በሕገ ቤተክርስቲያን ተኰትኩተው ባላደጉት ወጣቶች የተለመደውና ከጋብቻ በፊት የሚፈጸመው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለኤድስ መዛመት አስተዋጽኦ አድርጓል:: አንደኛው ተጠንቶ አልሆን ሲል ወደ ሌላው ሲኬድ ፣በሽታውን የማስተላለፍ ወይም በበሽታው የመያዝ እድሉ የሰፋ ይሆናል:: በተለይም በአሁኑ ሰዓት ያለው ለጋብቻ የመዘግየቱና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም የመቻኰሉ ሁኔታ ያባብሰዋል:: ለምሳሌ በከተማው አካባቢ ያሉ ሰዎች ትዳር መመሥረቻ ዕድሜያቸው ከ30–35 ሲሆን በአንፃሩ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የሚጀምሩት በአማካይ ከ15 ዓመታቸው ጀምሮ ነው:: በእነዚህ ሁሉ ዓመታት የትዳር ጓደኛን ለማግኘት «ለማጥናት» ወይም ራስን ካለመግዛት ከአንዱ ወደ ሌላው ሲሄዱ በበሽታው ሊለከፉ ይችላሉ:: በ1994ዓ.ም እ.ኤ.አ በተደረገው ጥናት በቫይረሱ ከተያዙት መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ከ15–34 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች የሆኑትም በዚሁ ምክንያት ነው:: ለዚህ አማራጭ የሌለው መፍትሔ እንደቤተክርስቲያናችን ሥርዓት የጊዜውን ብቻ ማሰብን ትቶ ራስን በመግዛት ከጋብቻ በፊት ግንኙነት አለመፈጸም ነው:: ይህ ሁኔታ አንድም ወጣቶችን የትዳር መመሥረቻ ጊዜአቸውን በአልባሌ እንዳያሳልፉና በዕድሜአቸው እንዲያገቡ ያደርጋል፤ አለያም በለጋ ዕድሜአቸው የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ጀምረው ኤድስን በመሳሰሉ በሽታዎች እንዳይያዙና ለተለያዩ ችግሮች እንዳይጋለጡ ይጠብቃል:: የመንፈሳዊነትም ጥቅሙ እዚህ ላይ ነው፤ ራሱን ገዝቶ ሥጋን ጠብቆ ነፍስን ለክብር ማብቃት!

*4 ሴተኛ አዳሪነትን ለማጥፋት መሞከር*

በሌሎች የአፍሪካ አገሮችም ሆነ በአገራችን ለኤድስ መስፋፋት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ እያደረገ ያለው የሴተኛ አዳሪዎቹ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት ነው:: በሀገራችን በቫይረሱ ከተለከፉት መካከልም አብዛኞቹ ሴተኛ አዳሪዎችና የእነርሱ ደምበኞች መሆናቸው ይህንኑ ያመለክታል:: ለምሳሌ በ1988ዓ.ም /እ.አ.አ/ በ23 ከተሞች አካባቢ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው ደማቸውን ለናሙና ከሰጡት ሰዎች መካከል 16.9 % ሴተኛ አዳሪዎች፣ 13.0% የከባድ መኪና ሹፌሮች፣ 3.7% ናቸው:: እንደገናም በ1989 ዓ.ም እ.ኤ.አ በ8 ከተሞች ብቻ በተደረገ ሌላ ጥናት ይህ ሁኔታ 60% በላይ እንደጨመረ ለማወቅ ተችሏል::

ስለዚህ የኤድስን በፍጥነት መዛመት ስናስብ የሴተኛ አዳሪዎች መብዛትም የበለጠ ሊያስጨንቀን ይገባል:: በተለይም በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን በትልልቅም ሆኑ በአነስተኛ ከተሞች የሴተኛ አዳሪዎች ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ ነው:: ይህንኑ የሴተኛ አዳሪዎችን ብዛት ለማወቅ በተለያዩ ጊዜያት ሙከራ ቢደረግም አብዛኞቹ ራሳቸውን ደብቀው ለሚኖሩ ትክክለኛውን ቁጥር ለማወቅ ያስቸግራል:: ለምሳሌ በ1973 ዓ.ም በ22 ከተሞች በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በተደረገው ጥናት መሠረት 37,000 ሴተኛ አዳሪዎች እንደነበሩ ሲታወቅ፤ በ1974 ዓ.ም በአርባናይዜሽን ፕሮጀክት የተደረው ጥናት ደግሞ በአዲስ አበባ ብቻ 80,000 ሴተኛ አዳሪዎች እንደነበሩ ያመለክታል:: ሌላውን ሁሉ ትተን በአሁን ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ 100,000 በላይ ሴተኛ አዳሪዎች እንዲሉ ይገመታል::

ከዚህ እንደምንረዳው ችግሩ በየዕለቱ እየጨመረ እንጂ ምንም የመቀነስም ሆነ በአለበት የመቆም ሁኔታ አይታይበትም:: እንደዚህም ከቀጠለ በየጊዜው በኤድስ ቫይረስ የሚከፉት ሰዎች ቁጥር በበለጠ ፍጥነት እንደሚጨምር ለመገመት አያዳግትም::

በመሆኑም የኤድስን መስፋፋት ለመግታት ዋነኛው መፍትሔ የሴተኛ አዳሪዎችን ቁጥር በተቻለ መጠን መቀነስ ሲሆን፣ለዚህም ለሴተኛ አዳሪነት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ማስወገዱ አማራጭ የለውም::

<u>ለምሳሌ:-</u> ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሴተኛ አዳሪነት ከተሰማሩት ውስጥ75 ከመቶ የሚሆኑት ከገጠር ባሎቻቸውን ፈትተው ወደ ከተማ የኮበለሉት ናቸው:: ትዳራቸውም የፈረሰው በወላጆቻቸው አስገዳጅነት በሕፃንነታቸው ለማያውቋቸውና በዕድሜ ከእነርሱ ለሚበልጡ ሰዎች በመዳራቸው ነው:: በተለይም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከ7–11 ዓመት ያሉትን ሕፃናት ለታላላቆቻቸውና አያቶቻቸው ሊሆኑ ለሚችሉ ሰዎች መዳር የተለመደ ነው:: በዚህ የተነሣ ሕፃናቱ ኰብልለው ወደ ከተማ በመግባት አማራጭ በማጣት በሴተኛ አዳሪነት ኑሮ ይሠማራሉ:: በጐንደር፣ በትግራይ፣ በወሎና በጐጃም ከተሞች የተደረገ አንድ ጥናትም እንደሚያመለክተው ከ10 ዓመት በላይ ከሚሆኑት ሴቶች መካከል 32% የሚሆኑት ፈቶች ሲሆኑ፤ ከነዚህም ውስጥ ብዙዎቹ ሴተኛ አዳሪዎች ሆነዋል::

ስለዚህ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሕፃናትን ያለፈቃዳቸው በዕድሜ ለማይመጥኗቸው ሰዎች የመዳሩን ሁኔታ ለማስወገድ ከቤተክርስቲያን ከፍተኛ ጥረት ይጠበቃል:: በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ለመፈጸም የግድ ሴቷ ለአቅመ ሄዋን /ቢያንስ 15 ዓመት/ ወንዱ ደግሞ ለአቅመ አዳም /ቢያንስ 18 ዓመት/ መድረስ ይኖርባቸዋል:: ይህ ሥርዓት በአግባቡ እንዲፈጸም ካህናት የንስሐ ልጆቻቸውን ማስተማር እና ፍቺም በየምክንያቱ እንዳይፈፀም የምክር አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል::

ከዚህም ሌላ ለሴተኛ አዳሪነት ምክንያት ከሚሆኑት ነገሮች መካከል ሥራ አጥነት አንዱ ነው:: በየጊዜው በተለያዩ ምክንያቶች የሥራ አጦች ቁጥር እየጨመረ መምጣት በተዘዋዋሪ መንገድ የሴተኛ አዳሪዎችና ብሎም የኤድስ በሽተኖችን ቁጥር እንዲጨምር አስተዋጽኦ ያደርጋል:: በተለይም መሥራት ሲችሉ የሥራ እድል ካለማግኘታቸውና አማራጭ ከማጣታቸው የተነሣ ብዙ እኅቶቻችን ለዚህ አስከፊ ኑሮ ተዳርገዋል:: ስለዚህ ኤድስን ለመከላከል ከሚደረገው ጥረት ጐን ለብዙ ችግሮች ምክንያት የሚሆነውን ሥራ አጥነትን ማጥፋት ያስፈልጋል:: ለሴተኛ አዳሪነት ከተዳረጉት መካከል 82% የሚሆኑት ከ15 እስከ 39 የዕድሜ ክልል በመሆናቸው የሙያ ሥልጠና ቢሰጣቸው በቀላሉ ወደ ሥራ ሊሰማሩ ይችላሉ:: እንደገናም 75% የሚሆኑት ሴተኛ አዳሪዎች ሌላ ሥራ የመሥራት ዝንባሌ እንዳላቸውና ከዚህ ኑሮ መገላገል መፈለጋቸው ትኩረት ቢሰጠው ችግሩን የበለጠ ቀላል ያደርገዋል:: ስለዚህ ሥራ አጥተው ለሴተኛ አዳሪነት የተዳረጉትን ወገኖቻችንን ከኤድስ ለመታደግ የገንዘብ አቅሙ ያላቸው ምእመናን፣ የተቻላቸውን ሊያደርጉ ያስፈልጋል::





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በሌላም በኩል የተማሪ ዝሙት አዳሪዎች መብዛት ለኤድስ መዛመት ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው:: በጊዚያዊ ጥቅም በመደለልና በሌሎች ሰዎች በመገፋፋት እየተማሩ በዝሙት አዳሪነት የተሰማሩ ወጣቶች ቁጥር ቀላል አይደለም:: ለዚህም የጾታና ግብረ ገብ ትምህርቶችን በትምህርት ቤቶች እንዲሰጡ ፣ተማሪዎችም ተመሳሳይ ልብስ /Uniform/ እንዲለብሱ ቢደረግ መልካም ነው:: የሞራልም መጥፋት ለሴተኛ አዳሪዎች መበራከት ምክንያት ሊሆን ይችላል:: ለዚህም ነው ምንም ዓይነት የኑሮ ችግር ሳይኖርባቸው ወደዚህ አሳፋሪ ሕይወት የተሰማሩ ሴቶች ቁጥር ከፍተኛ የሆነው:: በቀድሞ ጊዜ ያሳፍር የነበረው ዝሙት አዳሪነት እያደር እንደ አንድ የተከበረ ሥራ እየተቆጠረ መጥቶ በግላጭ እስከ መፈጸም ደርሷል:: ለዚህ ደግሞ ከቤተክርስቲያን መምህራን ብዙ ይጠበቃል:: ግብሩ ወደ እንስሳት በመለወጥ ላይ ያለውን ትውልድ በቃለ እግዚአብሔር አስተካክሎ ራሱን እንዲገዛ ማድረግ ያስፈልጋልና::

በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ በኤድስ ምክንያት የሰው ልጅ እርስ በርሱ እየተጨካከነ ነው ማለት ይቻላል:: ኤድስ በምን እንደሚተላለፍ ካለማወቅ በፍርሃትና ለራስ ብቻ ከማሰብ የተነሣ የኤድስ በሽተኞችን በመርዳት ፈንታ ይሸሻቸዋል፣ ያገልላቸዋልም:: እንዲሁም በኤድስ ወላጆቻቸውን ላጡትና ለተለያዩ ችግሮች ለተጋለጡት ሕፃናትና ወጣቶች ትኩረት ባለመስጠት ችግሩን እየሰማ እንዳልሰማ፣ እያየም እንዳላየ በመሆን ችላ ብሏቸዋል:: ርዳታ ቢደረግላቸውም በጣም አነስተኛና በውጭ ሰዎች ነው:: እኛመ ለራሳችን ለወገናችን ካልሆንን ከሌሎች ብቻ በሚደረግ እርዳታ ብዙም ለውጥ ማምጣት አይቻልም::

ስለዚህ እንደክርስቲያንነታችን ለሌሎች በሽተኞች እንደምናደርገው የኤድስ በሽተኞችን ተጸይፈን ከሩቅ ሳንሸሽ ቀርበን እንከባከባቸው በቃለ እግዚአብሔርም እናጽናናቸው:: ወላጆቻቸውን በበሽታው ያጡትን ሕፃናትም በመተባበር ልንረዳቸው፣ ልንከባከባቸውና ፍቅራችንን ልናሳያቸው ይገባል:: በዚህም ከእያንዳንዱ ምእመን በተናጠልና ከቤተክርስቲያንም ከፍተኛ ሥራ ይጠበቃል:: በተለይ ካህናትና ሰባኪያነ-ወንጌል ምእመኑን ከኤድስ እንዲጠብቅ ከማስተማር ጀምሮ የታመሙትን በማጽናናት፣ በጸሎት በማሰብ ትልቅ ለውጥ ማምጣትና መፍትሔ ለሌለውም መፍትሔ ማግኘት ይቻላል::

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው የኤድስን መዛመት ለዘለቄታው ለመቀነስ ብሎም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለማጥፋት የአንድ ሰሞን ስብሰባዎች፣ማድረግ ብቻ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ለሕገ ... ያስፈልጋል:: ለሕገ እግዚአብሔር የሚገዛ ሕዝብ ራሱን በመግዛት ከዝሙት ይርቃል፣ በትዳሩ ይታመናል፣ በየምክንያቱ ለአልኮልና ለዕፅ አይገዛም:: ከኤድስም ይጠበቃል:: ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን::

ምንጭ:-

- -ቴሌ ነጋሪት፣ ቅጽ 32፣ ቁጥር 1,1987 ዓ.ም
- - አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ 56ኛ ዓመት፣ ቁጥር 207 ዓርብ ግንቦት 8፣1989 ዓ.ም
- -. አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣56ኛ ዓመት፣ ቁጥር 241 ሐሙስ፣ ሰኔ 1989 ዓ.ም
- - አዲስ ዘመን ጋዜጣ ፣ 56ኛ ዓመት ፣ ቁጥር 242,ዓርብ ሰኔ 20,1989 ዓ.ም
- -አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ 56ኛ ዓመት፣ ቁጥር 253 ሐሙስ፣ ሐምሌ 3 ፣1989 ዓ.ም
- -እፎይታ መጽሔት፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 2 መጋቢት፣ 1984 ዓ.ም
- -እፎይታ መጽሔት፣ 5ኛ ዓመት፣ ቁጥር 3፣ግንቦት 1989 ዓ.ም
- -Addis Tribune, No 223. Friday, January 10, 1997
- -Addis Tribune, N0 221, Friday, Dec. 27, 1997
- -Addis Tribune, N0 222. Friday, January 3, 1997
- -International Herald Tribune, London ,N035,524, Monday May19,1997
- -The Guardian, Vol 156, No12 Week ending, March 23,1997
- -TIME, Vol 149, No 12, March,24,1997
- -Weekly Epidimological Report ,Vol 65, Page 337 /1990/

## ምንተ ንግበር?
### ምን እናድርግ?

ጥያቄ 1- የ22 ዓመት ወጣት ስሆን ከሦስት ዓመታት በፊት ጀምሮ በሄድኩበት ሁሉ በሰንበት ት/ቤቶች እየተሳተፍኩና እያገለገልኩ እገኛለሁ:: በዘንድሮ ዓመት እንኳን ምንም ሰንበት ት/ቤት በሌለበት አካባቢ ብመደብም ከወንድሞቼ ጋር ሆነን አቋቁመን እያገለገልኩ ነው:: እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ ባገለግለው ደስ ይለኛል:: ነገር ግን አንድ ነገር እፈራለሁ:: ከዚህ በፊት የማውቃቸው እኅቶቼ ብዙዎቹ ትዳር ከመሠረቱ በኋላ አገልግሎታቸውን አቁመዋል:: እንድያውም ሰንበት ት/ቤታቸውን ለአንዲት ቀን እንኳን ዘወር ብለው ያላዩም አሉ:: ምክንያቱን ስጠይቃቸው የልጆች እናት ስለሆኑ እንደሆነ ይነግሩኛል:: ታዲያ እኔም ከሁለት ዓመት በፊት ቃል ኪዳን የገባሁለት እጮኛ አለኝ:: የሠርጋችንንም ዕለት እየጠበቅን ነው:: ቢሆንም ያገቡትን እኅቶቼን ሕይወት በመመልከት ትዳርን እየፈራሁት ነውና ምን ይሻለኛል? መንፈሳዊ አገልግሎቴስ የግድ እስከ ጋብቻ ዕለት ብቻ ሊሆን ነው ማለት ነው? ተጨንቄአለሁና ምክራችሁን ለግሱኝ::

መልስ:-እኅታችን እንዳስተዋልሽው አንዳንድ ወጣቶች በሰንበት ት/ቤት ሲያገለግሉ ያድጉና ካገቡ በኋላ ከአገልግሎት ይለያሉ:: ይህ የሚሆነው የሚያገለግሉበትን ዓላማ ባለማወቅና ከድካም የተነሣ ነው:: ማንን፣ ለምንና እስከ መቼ ማገልገል እንዳለበት የማያውቅ አንድ ወጣት በየምክንያቱ አገልግሎቱን ቢያቆም አያስደንቅም:: ለዚህ ነው ብዙ ወጣቶች ሥራ ማግኘታቸውን፣ አካባቢ መቀየራቸውንና ትዳር መመሥረታቸውን የአገልግሎታቸው መጨረሻ የሚያደርጉት::

እኅታችን እስከመቼ እግዚአብሔርን ማገልገል እንዳለብሽ ከተረዳሽ ትዳርን መፍራት የለብሽም:: ትዳር በራሱ ከአገልግሎት አይለይምና:: መፍራትስ ትዳርን ሳይሆን የራስን ልብ ነው:: እንደ ኤልሳቤጥና ዘካርያስ ላሉት ትዳር የአገልግሎት ማጠንከሪያ እንጂ ማብቂያ አይሆንባቸውም:: ስለዚህ ዓላማሽ የዘላለምን ሕይወት መውረስ ከሆነ ምንም ነገር ከአገልግሎት ሊለይሽ አይችልም:: «ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም፤» እንደሚባለው፣ ትዳርን አትፍሪ፣ ትዳር በትዳርነቱ የአገልግሎት እንቅፋት ሊሆን አይችልምና:: ከአያያዙ ጉደለት እንጂ:: በመሆኑም ይህ ችግር ለወደፊቱ እንዳይፈጠርብሽ ከእጮኛሽ ጋር ሆናችሁ በወደፊቱ ክርስቲያናዊ ሕይወታችሁ ውስጥ ስለሚኖራችሁ የአገልግሎት ተሳትፎ በሰፊውና በግልጽነት ተወያዩ:: ለሁሉም እግዚአብሔር የጀመርሽውን አገልግሎት እስከመጨረሻው ያጽናልሽ::

ጥያቄ 2- ሃይማኖቴን በሰፊው ካወቅሁኝ ጊዜ ጀምሮ የጸሎት መጻሕፍን /ቢያንስ የዘወትር ጸሎትን/ ቤተክርስቲያን በማልሄድበት ጊዜ እንኳን ቢሆን ቤቴ ሆኜ ጸሎት አደርስ ነበር:: ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን በምጸልይበት ጊዜ የተለያዩ ሐሳቦች እየመጡብኝ ተቸገርኩኝ:: እንብቤ ስጨርስም ዳግም እንዳነብ ይገፋፋኛል:: በዚህም ምክንያት ቤት ውስጥ አደርስ የነበረውን ጸሎት ተውኩት:: ይህ ሐሳብ እንዲርቅልኝ እየጸለይኩና ቤተክርስቲያንም እየሄድኩ ነው:: ነገር ግን በተጨማሪ እንድህ ዓይነቱ ሐሳብ ፈጽሞ እንደተወኝ ምን ላድርግ?

አዜብ/አ.አ/

መልስ:- እኅታችን አዜብ የገጠመዎ ነገር ፈተና መሆኑን ዐውቀው የበለጠ በመጸለይዎና ቤተክርስቲያን መሄድዎንም ባለማቋረጥዎ መልካም አድርገዋል:: ዲያብሎስ እርሱን የምንቃወምበትና የምናሸንፍበትን ታላቅ ኃይል የምናገኘው በጸሎት መሆኑን ስለሚያውቅ ይህንኑ ትጥቃችንን ሊያስፈታን

ወደ ገጽ 31 ዞሯል





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ

ባለፈው እትማችን ስለ ኬልቄዶን ጉባኤ መግለጻችን ይታወሳል:: በዚህ እትማችን ደግሞ ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ስላለው ነገር በሰፊው እንመለከታለን::

መለያየት ከሰይጣን እንደ ሆነ የታወቀ ነው:: በመሆኑም የኬልቄዶን ጉባኤ በአንዲቱ ቤተክርስቲያን ላይ መለያየትን አምጥቷል:: ጉባኤው የነገሥታት ፈቃድ የተንጸባረቀበት የሥልጣን ሽኩቻ የታየበት እንደነበር ታሪክ ከትቦት አልፏል:: የንጥስሮስን የክህደት ትምህርት በያዘው ጦማር /ደብዳቤ/ላይ የተመሠረተው የኬልቄዶን ጉባኤ ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ የሚለውን የሚቃወም በመሆኑ ለመለያየት ምክንያት ሆኗል:: ይህም ጉባኤ ዛሬ በዘመናችን እንደ አሸን ፈልተው ለሚታዩት፣የእምነት ድርጅቶች ፈር ቀዳጅ መሆኑ አሌ አይባልም::

ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ለ150 ዓመታት ያህል የነገሡት የቁጥስጥንጥንያ ነገሥታት ቤተክርስቲያንን አንድ ለማድረግ ብዙ ጥረት አድርገዋል:: ለምሳሌ ከ417-491 ዓ.ም የነገሠው ዘይኑን፣ከ491-518 ዓ.ም የነገሠው አናስታሲዮስ በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ የሚለውን የተዋሕዳ እምነት ተቀብለው፣ ቤተ ክርስቲያን በሰላም የምትመራበትን መንገድ ለመፈለግ ተነስተው ነበር:: ለዚህም በጎ ፈቃድ መሰናከሉ የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔና የልዮን ጦማር መኾኑን በመገንዘብ የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ አባ አጋግዮስ እና ንጉሡ ዘይኑን ተስማምተው ይህን ለመሰረዝና ቤተክርስቲያንንም ወደ ጥንታዊ የተዋሕዶ እምነቷ ለመመለስ ከአንጾኪያውና ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ጋር ውይይት ጀመሩ::

በዚህ የአጋግዮስ የዕርቅ ድርድር የእስክንድርያውም የአንጾኪያው ፓትርያርኮች ተስማምተው ፈርመዋል:: በዚህ ጊዜ የሮማው ፓፓ እኔ ሳልጠየቅ ይህ እንዴት ይሆናል በማለት ተቆጥቶ ሊቀ ጳጳሱን አጋግዮስንና ንጉሡን ዘይኑንን አወገዛቸው:: በዚህ ምክንያት የሮምና የቁስጥንጥንያ አብያተ ክርስቲያናት ለ30 ዓመታት ያህል ተኳርፈዋል:: በነዚህ 30 ዓመታት ውስጥ በሶርያና በአንጾኪያ የቄርሎስን ትምህርት የተቀበሉ፣ በቤተክርስቲያን ትምህርት የበሰሉ፣ ለተዋሕዶ ሃይማኖት ተቆርቋሪዎች የሆኑ እነ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያና እነፊልክስዩስ ዘሶርያ ለተዋሕዶ እምነት ለመመስከር በቆራጥነት ተነሡ:

ለ30 ዓመታት ያህል ተኳርፈው የነበሩትን የግሪክንና የሮማን አብያተ ክርስቲያናት ያስማማው ጁስቲን ነው:: ጁስቲን የግሪኮች ንጉሥ ይሁን እንጂ ላቲን ከሚናገሩ ሮማውያን የተወለደ በሮማዊነቱ የሚያምን ነበር:: ከእርሱ በፊት የነበረውን የዕርቅ መሠረት ሁሉ አፍርሶ

## የቤተክርስቲያን ታሪክ /ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ/

ከብርሃኑ ጎበና

የቄርሎስን ትምህርት የተቀበሉትን ሁሉ የተዋሕዶ እምነታቸውን ትተው የልዮንን ጦማር እንዲቀበሉ በተቻለው ሁሉ ጥረት ጀምሮ ነበር:: ነገር ግን ሳይሳካለት ሞት ቀደመው::

ከጁስቲን ሞት በኋላ ወራሾቹ የተዋሕዶን እምነት ከገጸ ምድር ለማጥፋት ብዙ ሞክረዋል:: ግን አልሆነላቸውም:: በዚያ ዘመን መለካውያን የነገሥታትን ፈቃድ ፈጻሚዎች የወቅቱ ሥልጣናቸውን ተጠቅመው በግብጽ በሶርያና በሌሎችም ቦታዎች የሚገኙትን የተዋሕዶ ምእመናንን ለማጥፋት ዘመቻ ጀመሩ:: ብዙዎችን ሰየፉ፤ አብያተ ክርስቲያናትንም አቃጠሉ:: እንዲያውም "ጀግና የሚወለደው በጦር ሜዳ ነው" እንደሚባለው በዚህ ዘመን ነበር በምሥራቅ ቤተክርስቲያን ታሪክ ያጥቢያ ኮከብ የሆነው ያዕቆብ ዘእልበረዲ የተነሣው:: ያዕቆብ ዘእልበረዲ ሶርያዊ መነኩሴ ሲሆን የተወለደው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው:: «እልበረዲ» /የቅጽል ስሙ ነው/ በአረብኛ እንደ በቅሎ የሚሰግር ፈጣን ማለት ነው::

ያዕቆብ የተዋሕዶ እምነት አርበኛ ስለነበር በዘመኑ ከነበሩት የፓለቲካና የሁለት ባሕርይ መለካውያን መሪዎች እየተደበቀ ድሪቶ ለብሶ፣አልባሌ መስሎ የአባቶቹን የእነ አትናቴዎስን፣ የቄርሎስንና የዲዮስቆሮስን እምነት ያስተምር ነበር:: የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቴዎዶስዮስ በንጉሡ በጁስቲኒያን ትእዛዝ ተይዞ በቁስጥንጥንያ በቁም እስር ላይ ይገኝ ነበር::

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ያዕቆብ ዘእልበረዲና ፓትርያርክ ቴዎዶስዮስ በዚያች ከተማ ተገናኙ:: ያዕቆብ ለተዋሕዶ እምነት የሚያደርገውን ተጋድሎ በመገንዘብ ፓትርያርኩ በቁም እስር ላይ እንዳለ እሱንና አባ ቴዎድሮስ የተባለ ጓደኛውን በሶርያ ለሚገኙ ሁለት ሀገረ ስብከቶች ኤጲስ ቆጳሳት አድርጎ ሾማቸው:: ያዕቆብ ወዲያው እንደ ተሾመ ከእምነት ወንድሙ ጋር ሆኖ ምድረ ሶርያን እየዞረ የተዋሕዶን እምነት ማስተማር ጀመረ:: ከትምህርቱና ከምሳሌነቱም የተነሣ ተዳክሞ የነበረው የተዋሕዶ ሃይማኖት እንደገና አንሰራራ፣ በዚህ አኳኋን ሶርያንና ግብጽን ለአርባ ዓመታት ያህል እየተዘዋወረ አስተምሯል:: በጉዞውም አብረውት የሚዞሩና የሚረዱት ኮኖብና ኤብጊኖስ የሚባሉ ሁለት መነኰሳት ነበሩ::

ምእመናን እየበዙ ትምህርቱ እንደገና እየተስፋፋ በመሄዱ ካህናትና ኤጲስ ቆጳሳትም በብዛት ስለ አስፈለጉት ለእነዚህ ሁለት መነኰሳት የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ እንዲሰጥለት በግዞት ላይ ወደሚገኘው ወደ ፓትርያርክ ቴዎዶስዮስ ላካቸው:: እነሱም ኤጲስ ቆጳሳት ሆነው ከመጡለት በኋላ ከነሱ ጋር ሆኖ 27 ጳጳሳትና ከአንድ ሺህ በላይ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሹመዋል::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያዕቆብ ዘእልበረዲ አባት ነቱ ለተዋሕዶ ልጆች ሁሉ መሆኑ ቢታወቅም ብዙ የተጋደለው በመለካውያን ዘመቻ መንምና በነበረችው በሶርያ ነው:: ይህ ሁሉ ሲሆን ያዕቆብ የሶርያን መንበረ ፓትርያርክ ልያዝ አላለም:: ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ በመለካውያን ተንኮል ተሰዶ በግብጽ ሲሞት ያዕቆብ ከሌሎች ጳጳሳት ጋር በመሆን ስርግዮስ የተባለውን መንኩሴ ፓትርያርክነት ሾሙት:: ስርግዮስም ሦስት ዓመት ቆይቶ ዐረፈ:: በመንበሩም በተባሕትዎውና በትሩፋቱ የታወቀው አባ ጳውሊ ተተካ:: ያዕቆብ ዘእልበረዲ ሐዋርያዊ ተልዕኮውን በብዙ ተጋድሎ ባለመሰልቸት ከፈጸመ በኋላ በ578 ዓ.ም ዐረፈ::

ጥንጥንያ ያሉትን ተዋሕዶዎች እየለቃቀሙ ፈጇቸው::

ተዋሕዶዎቹ በዚህ ስቃይ እንዳሉ የፋርስ ጦር መጥቶ ግብጽን ወረራት:: በኋላም በ639 ዓ.ም እስላም ዐረቦች መጡ:: በዚህ ጊዜ የሮም ነገሥታት ያገዛዝ ቀንበር ያስቀቃቸው ተዋሕዶዎች በራቸውን ከፍተው ጦሩን ተቀበሉ::

ግሪኮችና ላቲኖች በሃይማኖት ስም የዘርና የሥልጣን ትግላቸውን ሲያካሂዱ ብዙ ዘመን ቆይተዋል:: በ1014 ዓ.ም የሮማው ፓፓ ቤኔዲክቶስ ስምንተኛ በቀኖና ሃይማኖት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ «ከአብም ከወልድም የሠረጸ ነው» የሚለውን ሥርዋጽ አስገባ::



ያዕቆብ ዘእልበረዲ /ሶርያዊ/

መለካውያን ከኬልቄዶን ውሳኔ በኋላ የርስ በርስ ንትርክና አለመግባባት አጋጥሟቸዋል:: በተለይም በኬልቄዶን ውሳኔ ቀኖና 28 ላይ የሠፈረውን ልዮን አላጸድቅ ላቸው በማለቱ ግሪኮች የልዮንን ጦማር በመደገፋቸው እጅጉን ተጸጽተዋል:: ቀኖና 28ም ለግሪኮች የእስክንድርያ መንበር እንደሚሰጣቸው የሚናገር ነበር:: የሮም መንግሥት ምዕራቡና ምሥራቁ ባንድ ሆኖ በተዋሕዶዎች ላይ መከራ ሲያጸና የነበረውን ያህል ብድራትን የማያስቀር እግዚአብሔር በሮማውያን ላይ የመከራ በትር ማሳረፍ ጀመረ::

በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሮም ግዛት ምዕራቡ ክፍል እንደወደቀ ምሥራቁ ክፍል ደግሞ በሰባተኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ በፋርስ ተወረረ:: የሮም ንጉሥ ከፋርሶች ጋር ተዋግቶ ስለተሸነፋ በጦርነቱ አልረዳችሁኝም በሚል ሰበብ በፍልስጥኤምና በቁስ

በዚያን ጊዜ የግሪክ ቤተክርስቲያን ተቃውሞ አላሰማችም፣ ከአርባ ዓመት በኋላ በ1054 ዓ.ም ግን ይስጠናል ብለው የጠበቁት ከሮማ መንበር ሁለተኛ የመሆን ሥልጣን ስለቀረባቸው ሥርዋጹን ምክንያት አድርገው የግሪክና የሮማ አብያተክርስቲያናት በውግዘት ተለያዩ:: ከዚያም በኋላ ሁለቱም የየራሳቸውን ቤተሰቦች ይዘው ለብቻቸው በመሆኑ አንዱ ሌላውን መናፍቅ በሚል ስም ይጠራ ጀመር::

ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ በቤተክርስቲያን ላይ የኑፋቄ እንክርዳድ በመዝራት እውነተኛዋን የክርስቶስ እርሻ ለማበላሸት የጣሩ አያሌ ናቸው:: በተለይ ለመለያየቱ ምክንያት የሆነችው የሮም ቤተክርስቲያን ቀድሞም የተመሰረተችው በአሸዋ ላይ ነበርና ለብዙ መናፍቃን መፈልፈል ምክንያት ሆናለች::

ይቀጥላል

ከገጽ 29 የዞረ

የተለያዩ መሰናክሎችን ይደረድርብናል:: ሁኔታዎች እንዳይመቻቹልንና በሥራ እንድንጠመድ በማድረግ፣ በእርስዎም እንደደረሰው እእምሮአችንን እንዳንሰበስብ በማድረግ፣ወዘተ... ይፈታተነናል:: አእምሮአችንን መረበሽና በጸሎት ሰዓት የተለያዩ ነገሮች እንድናስብ፣ ተስፋ እንድንቆርጥ ማድረግ ዋነኛዓላማው ነው:: ለምሳሌ እርስዎን የቤቱን ጸሎት አስተዎት:: ይህ ለእርሱ ትልቅ ድል ነው:: ቀስ በቀስ ደግሞ ከቤተክርስቲያንም ሊያስቀርዎ ይችላልና ክፍተት መስጠት አያስፈልግም፤ የጀመሩትን ጠበቅ አድርጎ መያዝ እንጂ! ስለዚህ ፈተናው ምንም ያህል ቢበዛ የበለጠ መትጋት እንጂ ውደኋላ ማፈግፈግ የለብዎትም:: «ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል:: ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል::» ያዕ4÷8::

ከዚህም ሌላ ይህ ሐሳብ እንዲተዎ:-

1 ከመጸለይዎ በፊት አእምሮዎን ለመሰብሰብ እንዲረዳዎ ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከሌሎች ቅዱሳት መጽሐፍ ጥቂት ማንበብና የሚችሉ ከሆነ መዝሙር መዘመር ወይም ማዳመጥ፤
2 በአጠገብዎ የሚረብሹት ሰው ከሌለ ድምጽዎን ከፍ አድርገው ጸሎት መጽሐፍዎን መድገም ወይም በቃል መጸለይ:: ድምጽን ከፍ አድርጎ በመጸለይ ሌላ የሚረብሽ ነገር ከመስማት ይልቅ የራስን ጸሎት መስማት ይቻላል፤ ሰይጣንንም ያርቃል:: ስለዚህ ድምጽን ከፍ አድርጎ መጸለይ ጠቃሚ ነው::
3 ሲጸልዩ በማማተብ ይጀምሩ:: በቅዱሳን ወይም በጌታ ሥነ-ሥዕልም ፊት ይቁሙ
4 ከጸሎት ሰዓትዎ በፊት የሚያነቡአቸው፣የሚያዳምጧቸውና የሚመለከቷቸው ነገሮች ተጽዕኖ ሊያሳድሩብዎ ስለሚችሉ የተመረጡ ይሁኑ::
5 ቀጠሮ ይዘው ወይም በወቅቱ የጀመሩትን ሥራ ሳይጨርሱ ወደ ጸሎት አይሂዱ::

በመጨረሻም ይህን ፈተና በአንድ ሳምንት ወይም ለአንድ ሁለት ዓመት ብቻ ተብሎ በጊዜ ተገድቦ የሚያበቃ ሳይሆን ለረዥም ጊዜ ሊፈታተንዎ ስለሚችል፤ሳይታክቱ ዘወትር ይጸልዩ:: ቢቻል ከጾምና ከስግደት ጋር ያድርጉት::

እግዚአብሔር ይርዳዎት::





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ትምህርተ ልሳነ ግእዝ

/በመምህር በትረወርቅ/

/ተ/ ተባዕታይ፣ /አ/ አንስታይ

| መራሕያን | ቃለ ግእዝ | ዐማርኛ |
|---|---|---|
| 1. | ገጽ | ፊት |
| አነ | ገጽየ | ፊቴ |
| ንሕነ | ገጽነ | ፊታችን |
| አንተ | ገጽከ | ፊትህ |
| አንትሙ | ገጽክሙ | ፊታችኹ /ተ/ |
| ውእቱ | ገጹ | ፊቱ |
| ውእቶሙ | ገጾሙ | ፊታቸው/ተ/ |
| አንቲ | ገጽኪ | ፊትሽ |
| አንትን | ገጽክን | ፊታችኍ /አ/ |
| ይእቲ | ገጻ | ፊቷ |
| ውእቶን | ገጾን | ፊታቸው/አ/ |
| 2. | ክሣድ | ዐንገት |
| አነ | ክሣድየ | ዐንገቴ |
| ንሕነ | ክሣድነ | ዐንገታችን |
| አንተ | ክሣድከ | ዐንገትህ |
| አንትሙ | ክሣድክሙ | ዐንገታችኍ /ተ/ |
| ውእቱ | ክሣዱ | ዐንገቱ |
| ውእቶሙ | ክሣዶሙ | ዐንገታቸው/ተ/ |
| አንቲ | ክሣድኪ | ዐንገትሽ |
| አንትን | ክሣድክን | ዐንገታችኍ /አ/ |
| ይእቲ | ክሣዳ | ዐንገቷ |
| ውእቶን | ክሣዶን | ዐንገታቸው /አ/ |
| 3. | እዝን | ጕሮ |
| አነ | እዝንየ | ጕሮዬ |
| ንሕነ | እዝንነ | ጕሯችን |
| አንተ | እዝንከ | ጕሮህ |
| አንትሙ | አዝንክሙ | ጕሯችኍ /ተ/ |
| ውእቱ | እዝኑ | ጕሮው |
| ውእቶሙ | አዝኖሙ | ጕሯቸው /ተ/ |
| አንቲ | እዝንኪ | ጕሮሽ |
| አንትን | እዝንክን | ጕሯችኍ /አ/ |
| ይእቲ | እዝና | ጕሮዋ |
| ውእቶን | እዝኖን | ጕራቸው /አ/ |

እንግዲህ በስም ጊዜ ለመራሕያን የሚስማሙትን ፊደላት እስከ አኹን በዘረዘርናቸው 6 ቃላት ሳንረዳቸው አንቀርም ለማጠናከር ያኸል

| | |
|---|---|
| አነ | የ |
| ንሕነ | ነ |
| አንተ | ከ |
| አንትሙ | ክሙ |
| ውእቱ | ካዕብ ፊደልን |
| ውእቶሙ | ሳብዕና ካዕብን |
| አንቲ | ኪ |
| አንትን | ክን |
| ይእቲ | ራብዕ ፊደል |
| ውእቶን | ሳብዕና ሳድስ |

ቀለምን ይስማማሉ::

ማስታወሻውን እንጠቀም::

## ትምህርት 5፤

*ስመ ክፍላተ ሕዋስ /የሰውነት ክፍሎች ስም/*

| በነጠላ | ዐማርኛ | በብዙ |
|---|---|---|
| 1 ርእ[ወ]ስ | ራስ | አርእስ[ወ]ት |
| 2. ሥዕ[ወ]ርት | ጠጉር | ሥዕር[ወ]ታት |
| 3. ገጽ[ወ] | ፊት | ገጻ[ወ]ት |
| 4. እዝ[ወ]ን | ጕሮ | አእዛ[ወ]ን/እዝን/ |
| 5. ዐይ[ወ]ን | ዐይን | አዕይ[ወ]ንት |
| 6. ቅርን[ወ]ብ | ቅንድብ | ቀራን[ወ]ብት |
| 7. አን[ወ]ፍ | አፍንጫ | አእና[ወ]ፍ |
| 8. አ[ወ]ፍ | አፍ | አፈው፣አፎት አፈ[ወ]ዋት |
| 9. መልታ[ወ]ሕት፡ጕንጭ | | መላት[ወ]ሕ |
| 10. ከንፈ[ወ]ር | ከንፈር | ከናፍ[ወ]ር |
| 11. ስን[ወ] | ጥርስ | ስነን/ አስ[ወ]ናን |
| 12. ክሣ[ወ]ድ | ዐንገት | ክሣዳት /ክሣ[ወ]ውድ/ |
| 13. ጒር[ወ]ዔ | ጉረሮ | ጎራዒ[ወ]ት |
| 14. እንግ[ወ]ድዓ | ደረት | እንግድ[ወ]ዓት |
| 15. ጥብ[ወ] | ጡት | አጥ[ወ]ባት |
| 16. መትከ[ወ]ፍት | ትካሻ | መታክ[ወ]ፍት |
| 17. ኩርናዕ | የእጅ ጉልበት ሹሉ | ኩርናዓት |
| 18. እመ[ወ]ት | ክንድ | እመ[ወ]ታት |
| 19. እራ[ወ]ኅ | ማኸል እጅ መዳፍ ወስጡ | እራ[ወ]ኃት |
| 20. አጽባ[ወ]ዕት | ጣት | አጻብ[ወ]ዕ /ዓት/ |
| 21. ጽፍ[ወ]ር | ጥፍር አፍአዊ ዐጥንት | አጽ[ወ]ፋር /ጽፍ[ወ]ራት/ |
| 22. ከር[ወ]ሥ | የምግብ ቋት | |
| 23. እማዑ[ወ]ት | አንዠት | ንዋየ ውስጥ |
| 24. ል[ወ]ብ | ልብ | አልባ[ወ]ብ |
| 25. ኩሊ[ወ]ት | ኩላሊት | ኩልያ[ወ]ት |
| 26. ዘባ[ወ]ን | ዠርባ | ዘባና[ወ]ት |
| 27. ገ[ወ]ቦ | ጐን | ገበ[ወ]ዋት |
| 28. ሐ[ወ]ቌ | ወገብ | ሐቌ[ወ]ት |
| 29. አ[ወ]ንጕዕ | አንጓ፣ቅልጥም | አና[ወ]ጕዕ |
| 30. ብር[ወ]ክ | ጉልበት | አብራ[ወ]ክ |
| 31. /ሰኮና/ሰኰ[ወ]ና | መርገጫ ወስጥ እግር | ሰኳ[ወ]ንው |

ከ1–31 የተገለጹት ቃላት በወደቃ ንባብ ይነበቡ ማለት በዐማርኛ ለማ፣በቀል፣ሀገር፣መሬት፣ እንደ ማለት ነው::

ወ=ወዲቅ ማለት የሚሰበር እቃን በጥንቃቄ እንደማስቀመ[illegible] ለሰስ ወይም ለዘብ በማድረግ ማንበብ ማለት ነው::





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ዝክር በሥርዓቱ

በዚህ ሰሞን በአንድ የሠፈራችን ጸበል ጸዲቅ ላይ ተጠርቼ ያየሁት ነገር ስላስገረመኝና በዚሁ ከቀጠለ የጸበል ጸዲቅ ሥርዓቱን እንዳያበላሸው ስለፈ ራሁ ልጽፍላችሁ ተነሣሁ::

- *በጣም ጥሩ ይቀጥሉ:-*

ነገሩ እንዲህ ነው:: ጸበል ጸዲቁን ለመቅመስ ወደ ቤቱ ጐራ እንዳልን እንኳንስ በቤተክርስቲያናችን በመገናኛ ብዙኃን ሳይቀር ሲወገዝ የኖረ የዝሙት ዘፈን እስከ ላንቃው ተከፍቶ ቤቱን ዝክረ ቅዱሳን የሚዘከርበት መሆኑ ቀርቶ ዳንስ ቤት አስመስሎታል:: ምነው ብንል በዓል ስለሆነ ለደስታ ነው ተባልን::

*ፍሬሠናይ ጸጋዬ*
*ከጐሐ ጽዮን ቅ/ማርያም*
*ሰ/ት/ቤት ሰላሌ*

## ተናጋሪውን ወይስ አናጋሪውን?

አንዳንድ ሰዎች ለምን ቤተ እግዚአብሔር እንደሚመጡ እንኳን አያውቁም ማለት ይቻላል:: ይኸውም በሠርክ ጉባኤ ወይም በሰንበት ት/ቤት አንደበተ ርቱዕ የሆነ አስተማሪ ሲኖር ይመጣሉ፤ ሌላ የማያውቁትና ቀስ ብሎ የሚናገረው በሚያስተምርበት ጊዜ ደግሞ ወደ ቤተክርስቲያን አካባቢም ዝር አይሉም:: እንዲያውም አንዳንዶቹ የሚያውቋቸው መምህራን በሚያስተምሩባቸው ጉባኤያት እየዞሩ የሚማሩም አሉ:: ራሳቸውንም የኒያ ሰባኪ ተከታይ አድርገው በመቁጠር «እኔ የእገሌ ተከታይ ነኝ» እያሉም እስከ መመጻደቅ የደረሱም አጋጥመውኛል:: ለመሆኑ ተናጋሪውን ወይስ አናጋሪውን የምንመለከተው? ትክክል አይመስለኝምና አናጋሪውን ብቻ ተመልክተን ሰውን ከሰው ባናማርጥ መልካም ነው:: እርሱ ከወደደ እንኳን ሰውን ግዑዙንም ፍጥረት ማናገር ይችላልና! *በላይ በቀለ /ሊሙ ገነት/*

## እድለኞች ነን

ከጥቂት ዓመታት በፊት በገበያ ላይ ፈጽሞ የማናገኛቸውንና መኖራቸውን ብቻ በዝና እንሰማ የነበሩትን የቤተክርስቲያን መጻሕፍት በቤተክርስቲያናችን የኅትመት ክፍል እንደገና እየታተሙልን ማግኘት ጀምረናል:: ይህም እጅግ የሚያስደስትና ለትውልዱ የሚጠቅም ሥራ ነው:: ተቀድቶ የማያልቀውንና በሊቃውንት አባቶቻችን የተላለፈልንን የቤተክርስቲያናችንን ትምህርት በቅርቡ ለማግኘት በመብቃታችን እድለኞች ነን:: ወደፊትም ያልተተረጐሙት ተተረጕመው፣አዳዲሶችም ተጽፈውና ገና ብዙ እናገኛለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: አባቶቻችን ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ወጣቱን ትውልድ ከዘመኑ ፈተና መታደግ የሚቻለው በመጻሕፍት መሆኑን ዐውቃችሁ የበለጠ በርቱልን፤ እግዚአብሔርም ረጅም ዕድሜን ሰጥቶ እናንተን ያቆይልን::

*ጥላሁን መለሰ*
*/ምዕራብ ወለጋ–መነሲቡ/*

## የኦሪቱን በሐዲስ?

እኔ በነበርኩበት በአርሲ ዞን አስኮ ወረዳ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ግራ የሚያጋባ ሥርዓት ይፈጸማል:: ይኸውም በክብረ በዓላት ጊዜ ምእመናንም ሆኑ ካህናቱ የተሳሉት ስእለት ወይፈን፣ጊደር ወይም ፍየልና በግ ከሆነ ታቦቱ ከግቢው ወጥቶ ሲመለስ በር ላይ የሚታየው ትርምስ በጣም ያስገርማል:: ለስእለት ይዘው የመጡትን እንስሳ አርደው ደሙን ታቦቱን የተሸከመው ካህን ረግጦላቸው እንዲገባ ይገፋፋሉ:: ትክክለኛው የስእለት ሥርዓትም ስለሚመስላቸው ይህንን እድል ካላገኙ ይበሳጫሉ፤ እኔ ልቅደም እኔ ቅደም በሚል ሰበብ በጩቤ እስከ መዋጋት የተደረሰበትም አጋጣሚ እንደነበር አስታውሳለሁ:: በዚህ ብቻም አይበቃም ዐዋቂ የሚባሉት ካህናቱም በታረዱት እንስሳት ደም ከታቦቱ መሸፈኛ ጀምሮ ንዋያተ ቅድሳቱን በመሉ ነክረው ይገባሉ:: ለምን እንደዚህ ታደርጋላችሁ ሲባል ሥርዓት ነው ይሉናል:: ይህ የመስዋዕት ሥርዓት ግን የኦሪት ሥርዓት ወይም ከባዕድ አምልኮ ጋር የተገናኘ ይመሥለኛል:: ስለዚህ የሐዲስ ኪዳን መስዋዕት በመስቀል ላይ የተሠዋልን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ መሆኑ ታውቆ ከቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ውጭ የሆነው አዲስ ሥርዓት እንዲታርም አስፈላጊው ትምህርት ቢሰጥ መልካም ነው::

*ተማሪ መኰንን ኃይሉ*
*/ኮተቤ መምህራን ት/ኰሌጅ/*

## ባጭሩ ካልተቀጨ..

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በክርስትና መንገድ ሲጓዙ ትንሽ መከራ፣ጥቂትስቃይ እንኳ እንዲነካቸው አይወዱም::

- *እንዴት እንዲህ ሊሉ በቁ?*

በአንድ ቤተ ክርስቲያን ያየሁት ነገር አስደንቆኝ ነዋ!

- *ምን አዩ?*


ድሮ ድሮ በወሬ ስሰማ አላምንም ነበር:: አንድቀን የጐረቤቴ ልጅ ክርስትና ሊነሣ ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሄድን:: በማጥመቂያ ቤቱ ቆመን ሳለን «ሃብታሞች» ናቸው የተባሉ ሰዎች መጡ:: ከዚያም ልጃችንን ብርድ ይመታዋል አሉና ውኃው እንዲሞቅላቸው አደረጉ::

- ጉድ ነው!

እንዲያውም ባይገርማችሁ ለውኃው ማሞቂያ የኤሌክትሪክ ሽቦ ይዞ የጠበቃቸው ዲያቆኑ ነበር:: ይህች ነገር በአጭሩ ካልተቀጨች ነገ ሌላ ጣጣ ይዛ ትመጣለችና የቤተክርስቲያን አባቶች አንድ በሏት::

*ይበልጣል ሽመልስ /አዲስ አበባ/*

©ማኅበረ ቅዱሳን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፤እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡